**COVER PAGE**

ዓላማ፤ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ዓላማ የትምህርት ክልሉ ጿጋዎች ለሁሉም ርትኣዊ በሆነ መንገድ መዳረሳቸውን፣ ሁኔታዎች የፈጠሩት ክፍተት (ኦፖርቱኒቲ ጋፐ) መዘጋቱን እና ለሁሉም የትምህርት ክልሉ ተማሪዎች ምርጥ የሆነ ትምህርት በእኩል መዳረሱን ማረጋገጥ ነው።

ራኢይ፤ እያንዳንዱ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ተማሪ ከፍተኛ ደረጃ ያለው፣ የ21ኛ ክፍለ ዘመን ትምህርት ተሰጥቶት ለኮሌጅ፣ ለሙያ እና ሂወት ዝግጁ ሆኖ እንዲመረቅ ማድረግ ነው።

**ማውጫ**


| | |
|---|---|
| መግቢያ | **2** |
| የተማሪ መብቶች | **5** |
| የተማሪ ግዴታዎች | **6** |
| የትምህርት ቤት ግዴታዎች | **6** |
| የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሓላፊነቶች | **9** |
| የተማሪዎች ባህሪያት ወይም (ኣስቀድሞ በ የተማሪዎች የስነስርዓት ድንጋጌ ይታወቕ የነበር) | **10** |
| የስነስርዓት እርምጃን ይግባኝ የማለት መብቶች | **10** |
| ኣባሪ ጽሑፍ ሀ: የቃላት ኣተረጓገም | **26** |
| ኣባሪ ጽሑፍ ለ: ናሙና የእጽ እና ኣልከሆል የሚመለከት ጉዳይ ሽምግልና ፎርም | **40** |
| ኣባሪ ጽሑፍ ሐ: ናሙና የሽምግልና ፎርም | **43** |


**የፍትሓዊነት እና የታዛዥነት ፖሊሲ:**

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ (SPS) ለሁሉም እኩል እና ርትዓዊ የትምህርት እና የስራ ዕድል ይሰጣል። እንዲሁም በሁሉም ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ ያለምንም የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ ዕድሜ፣ የትውልድ ኣገር፣ ሃብት እና ገንዘብ፣ ስንክልና፣ ጾታዊ ዝንባሌ ማለት የሆነ ሰው የሚጠራበት ጾታ ወይም መለያ፣ እርግዝና፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ኣካላዊ ቅርጽ፣ የሆነ የኣእምሮ ወይም የኣካል ስንክልና ወይም በክብር የተሸኙ ወታደሮች እና ኣርበኝነት፣ ወታደር መሆን ወይም የሰለጠነ መሪ ውሻ ወይም ሌላ እንስሳ በመጠቀም ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ሰው እኩል ዕድል ይሰጣል። SPS ለሁሉም የተመደቡሉት ወይም ተወክለው የመጡ እንደ ቦይ ስካውት እና ሌሎች የወጣቶች ማህበራት እኩል ዕድል ይሰጣል። የሲያትል ፐብሊክ ስኩልስ ለተምሪዎች እና ለሁሉም የማህበረሰብ ኣባላት የሚከተሉት የትምህርት ክልሉ ሰራተኛች ኣድልዎን የሚመለከት ጥያቄዎችን ሊመልሱ እና የሆነ ዓይነት የኣድልዎ ደብል ክስ እንዲሰሙ የተመደቡ ናቸው። በደብዳቤ በሚከተለው እድራሻ ልታገኙዋቸው ትችልላላችሁ፤ Seattle Public Schools MS 32-149, PO Box 34165, Seattle, WA 98124-1166 ወይም በስልክ ቁጥር ወይም ኢሜል ቀጥሎ ለየጉዳዩ በተዘረዘረው መሰረት ልታገኙዋቸው ትችላላችሁ።

- *ጾታዊ ልዩነት የሚመለከት ጉዳይ፣ ጾታዊ በደል ጨምሮ (ሴክሽዋል ሃራስመንት) የታይትል IX ኣቤቱታ ኣወሃሃጅ፣ በኢሜል* title.ix@seattleschools.org
- ስንክልና ያላቸው እና ልዩ እገዛ ለሚያስፈልጋቸው የADA/*504 ተማሪዎ በደለ ጉዳይ ይግባኝ (ኣቤቱታ) ሰሚ ኣወሃሃጅ፣ በኢሜል* accessibility@seattleschools.org
- *ለሁሉም ሌላ ልዩነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች እባካችሁ የተማሪዎች ሰብኣዊ መብት ጉዳይ ሰሚ ባለስልጣኙ* በኢሜል oscr@seattleschools.org

ስክልና ስላቸው ተማሪዎች ስለሚሰጥ ኣገልግሎ ወይም ስለሚደረግ ልዩነት ጾታዊ በደልን ጨምሮ በሰራተኞች በኩል የሚነሳ ቅሬታ፡ የትምህርት ክልሉ ረዳት ሁማን ሪሶርስስ: Seattle Public Schools, Mailstop 33-157, PO Box 34165, Seattle WA, 98124-1166 ወይም (206) 252-0024 ወይም በኢሜል hreeoc@seattleschools.org

## ኣወንታዊ እምነት፣ ኣወንታዊ ዝምድና፣ ኣወንታዊ የትምህርት ሂደት እና ኣወንታዊ ሽርክና በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ

ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚፈጠረው ደህንነቱ በተጠበቀ፣ ኣወንታዊ፣ ቀጣይነት ያለው እና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ የትምህርት ኣከባቢ ሲፈጠር ብቻ ነው። የባህላዊ ብስለት፣ ደህንነት፣ መከባበር፣ ቅንነት፣ ተጠያቂነት እና ርትዓዊ መሰረት ሓሳቦች መላው ስርዓት ውስጥ ሲሰርጹ መተማመን የሞላበት ዝምድና ይፈጠራል። ይህ ደግሞ ለያንዳንዱ ተማሪ ምርጥ የሆነ ትምህርት ለማደረስ ያስችላል።

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ በትምህርት ክልሉ ውስጥ እና በያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ብዙህነትን የሚያከብር እና ለብዙህነት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ ባህላዊ ብስለትን (ካልቸራል ኢንተለጀንስ) ለማስፋፋት ቃል ገብቷል። ይህ ደግሞ ርትዓዊ እና መልካም ኣያያዝ ለሁሉም እንዲኖር ወሳኝ መምሪያ ሆኖ ያገለግላል።

መልካም (ኣወንታዊ) የትምህርት ቤት ኣከባቢ መኖር እያንዳንዱ ተማሪ የባለቤትነት ስሜት እንሰማው እና ምርጥ ትምህርት ለሆሉም ለማዳረስ እና ለማስፋፋት ያስችላል። መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- የጋር እምነት፣ እሴት፣ ኣምልኮ እና የባህሉ ኣካል ሆኖ ኣብሮ የሚያድገው ታሪክ ላይ የተመረኮሰ የሩቅ ራኢ፣
- ተማሪዎች፣ ወላጆች እና የትምህርት ቤት ባልደረቦች መካከል ያጋር ትብብር ላይ የተመረኮሰ ዝምድና እና መከባበር ላይ የተመረኮሰ ግንኙነት፣
- ሁሉንም ባህሎች የሚያከብር እና ዋጋ የሚሰጥ ኣግባብ ያለው እና ሁሉንም በንኣንድ ዓይን የሚያይ ኣያያዝ፣
- ሁሉንም በመልካም ሁኔታ የሚቀበል፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለሁሉም ክፍት የሆነ የስራ ኣከባቢ እና
- መደበኛ የሆነ በተማሪዎች፣ በቤተሰቦች፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኣካላት የሚካሄድ የትምህርት ቤት ሁኔታን የሚያጠና ግምገማ እና ዳግመ ጥናት።

ከመልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ መፍጠር በተጨማሪ ተማሪዎች ከስሜታቸው እና ኣካላዊ ሁኔታ የሚያስጨንቁ ነገሮች ጋር የተሳሰረ የሚያስጨንቅ ነገር ሲያጋጥማቸው እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው ይገባናል። እንደዚህ ባሉ ግዜያት ተማሪዎች የሚያስጨንቃቸውን ነገር ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚያምኑት ኣዋቂ ማካፈል በተጨማሪም ለሌሎች የትምህርት ቤት ባልደረቦች ማካፈል ይችላሉ። ምክንያቱም ሁሉም የትምህርት ቤት ባልደረቦች ሁሉንም ተማሪዎች ጥሩ ተሰምቷቸው ትምህርትታቸውን እንዲከታተሉ የማገዝ ሓላፊነት ስላላቸው ማገዝ ይችላሉ።

ይህ *የተማሪዎች ሓላፊነት እና መብቶች* ዶክመንት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የተማሪዎች ስነስርዓት ኣስመልክቶ ያስቀመጣቸውን ሕጎች እና መመሪያዎች ያዘለ ነው። ይህ ዶክመንት የተዘጋጀው ከዋሽንግተን ስቴት መመሪያዎች እና የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ስትራቴጅያዊ ውጥን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው። የዋሽንግተን ስቴት የመስተዳድር ሕግ (ዋሽንግተን ስቴት ኣድሚኒስትሬቲቭ ኮድ (WAC)) ላይ የሰፈሩትን ለምሳሌ ስነስርዓት፣ መታገድ እና መባረር ኣስመልክተው የሰፈሩትን የማረሚያ እርምጃዎች መሰረት ያደረገ ነው።

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የስነስርዓት እምጃ ፖሊሲ መሰረቱ ሁሉንም ያካተተ መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ መፈጠር ነው። ይህ መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ ሁሉም ማለት ተማሪዎች፣ ቤተሰብ፣ ኣስተማሪዎች፣ ኣስተዳዳሪዎች፣ በጎ ፈቃደኞች እና ሌሎች የትምህርት ቤት ባልደረቦች ሚገባቸው እና የሚጠበቅበት ያሚያውቁት የስነስርኣት ሁኔታ (ማለት እንደ ኣወንታዊ የጠባይ እገዛ እና ማገላገያ መዋቅር ስር (Positive Behavior Interventions and Supports (PBIS) በማዋቀር ነው። ይህ የስነስርዓት ርምጃ ዓላማው የትምህርት ግዜ ከንቱ ማባከንን እና ከትምህርት ቤት ውጪ ያሚያደርግ ያስነስርዓት ኣርምጃ ማጉደል ላይ ያተኮሩ የስነስርዓት ኣፈጻጸሞች እና መከላከያ መንገዶች ማቆም ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ደኩሜት ሁሉም ተማሪዎች ላይ እኩል ይተገበራል። በተጨማሪ ይህ ደኩሜንት ሁሉንም የትምህርት ማህበረሰብ ኣባላት ከትምህርት ጋር የተሳሰሩ ሕጎች፣ መመሪያዎች እና የሕግ ኣፈጻጸም ቅጦችን ለማስተማር ዓልሞ የተዘጋጀ ነው። ቤተሰቦች ይህን የተማሪዎች መብት እና ሓላፊነቶች የሚለውን ዶኩሜንት ከልጆቻቸው ጋር ሆነው እንዲያነቡት እንድጠይቃለን። ዶክሜንቱ ትምህርት ቤት ከተማሪዎች የሚጠብቅባቸውን እና ተማሪዎች ትምህርት ቤት ካሉ የትምህርት ቤት ሰራተኞች መጠበቅ ያለባቸውን ነገሮች ያብራራል።

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ይህን የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መሰረታዊ ሕጎች “The Basic Rules of Seattle Public Schools” በበራሪ ጽሑፍ መልክ ኣትሞ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ያከፋፍላል።

ይህን *የተማሪዎች መብት እና ሓላፊነቶች* የሚል ዶክምመንንት የሚመለከት ጥያቄ ወደ ስነስርዓት ጽሕፈት ቤት (ዲሲፕሊን ኦፊስ) በኢሜል: discipline@seattleschools.org ወይም በስልክ ቁጥር (206) 252-0820 በመደወል ወይ በፖስታ

Seattle Public Schools
MS 31-177
P.O. Box 34165
Seattle, WA 98124-1165

መላክ ትችላላችሁ።

ጥያቄዎቻችሁ በቀጥታ ይመልስሏችኋል ወይም ወደ ሚመለከታቸው ኣስተዳዳሪዎች ይላካሉ። እዚህ ዶክመንት ውስጥ የተጠቀሱት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች የሚከተለው የኢንተርኔት ኣድራሻ ላይ https://www.seattleschools.org/district/board_nav/policies_and_procedures ይገኛሉ።

.

# የተማሪዎች መብቶች

የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ኣሏቸው፤

- ስርዓትን የጠበቀ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍል እና ትምህርት ቤት፤
- የተማሪዎችን ባህል ግምት ውስጥ ያስገባ ተገቢ እገዛ ያለው እና እያንዳንዱ ተማሪ ላይ ከፍተኛ ተስፋ የሚጥል ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት፤
- ኣክብሮ ያለው እና ትህትና የሞላው ኣያያዝ፤
- መደመጥና ሓሳባቸው መግለጽ፤
- ከሁሉም እኩል ትምህርት፣ ኣገልግሎቶች፣ የትምህርት መሳሪያ እና እንደ ኣስፈላጊነቱ ከትምህርት ስዓት ውጪ የሚዘጋጅ እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ፤
- ትምህርት ቤት መኖራቸው መታወቅ እና በእንክብካቤ መያዝ፤
- ከስህተታቸው ተምርው እንድያርሙ እድል መስጠት እና
- የተበላሸ ዝምድናን እንዴት መጠገን እንደሚችሉ እና ተጠያቂነትን ማስተማር ላይ ያተኮረ እገዛ መግኘት።

በተጨማሪ ተማሪዎች ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን ህገ መንግስታዊ መብት ኣላቸው። ስለዚህ ትምህርት ቤት ያለምክንያት መብታቸውን መጋፋት ኣይችልም። ሆኖም ግን ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማር ሓላፊነታቸው እንዲወጡ እነዚህን መብቶች ገደብ ሊያደርግባቸው ይችላል። ተማሪዎች የሚከተሉ መብቶች ኣሏቸው፤

- የመናገር ነጻነት
- የመሰብሰብ
- የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ
- የመገናኛ ብዙሃን
- ምክንያት የሌለው ፍተሻ እና መታሰር የሌለበት[1]
- እኩል የትምህርት እድል[2]
- የእምነት[3]

---

[1] ተማሪዎች ምክንያት ከሌለው ፍተሻ እና እስር ነጻ መሆን ኣለባቸው። ሆኖም ግን የሁሉንም ደህንነት ለመጠበቅ የሚከተሉት ህጎች ተግባር ላይ ይውላሉ፤

- ኣጠቃላይ የሆነ የንብረት ፍተሻ ማለት የተማሪውን ዴስክ እና ቁምሳጥን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር በሆነ ግዜ (ተማሪውን ኣስቀድሞ ሳያሳውቁ) ሊካሄድ ይችላል።
- የሚከተሉት ነገሮች እንደ ጠበንጃ ሌሎች መሳሪያዎች፣ ሪችት ወይም የሆነ ነገር ለደህንነት ያሰጋል የሚባል ነገር ወይም ጸጥታን ይነካል የሚባል ነገር ወይም የትምህርት ሂደትን ይረብሻል የሚባል ነገር ሊወረስ እና ከተማሪ እጅ (ንብረትነት) ሊወረስ ይችላል።
- ባጠቃላይ የተማሪ (የተማሪን የኣካላት ፍተሻ ሳይጨምር (ስትሪፕ ሰርች)) ወይም የንብረቱ ፍተሻ ኮንትሮባንድ ወይም ሌላ የስነስርዓት መተላለፍ ኣለ የሚል በቂ ጥርጣሬ ካለ፤ ፍተሻው ኣግባብ ያለው፣ ዓላማውን የጠበቀ እና ፍተሻው ከልክ ያላለፈ እና የተማሪን ዕድሜ እና ጾታ፣ የተፈጸው ዓይነት በደል እና ፍተሻው እንዲካሄድ የገፋፋው መረጃ ላይ የተመረኮሰ እና ግምት ውስጥ ያስገባ እስከሆነ ድረስ ሊካሄድ ይችላል።
  - o የዋሽንግተን ሕግ (RCW 28A.600.230(3)) የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች ወይም በነሱ ስር ያሉ ግለሰቦች የተማሪ ኣካላት ፍተሻ (ስትሪፕ ሰርች) እንዳያደርጉ ይከለክላል። “የተማሪን ኣካላት ፍተሻ (ስትሪፕ ሰርች)” ኣንደሚከተለው በሰፊው ይተረጎማል፤ “ኣንድን ግለሰብ ልብሱን እንዲያወልቅ ወይም በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ልብሱን ወይም ልብሷን በማውለቅ ብልቱን/ብልቷን፣ መቀመጫውን/ዋን ወይም የውስጥ ልብሱን ወይም ለሴቶች ጡታቸውን መፈተሽ።”

[2] ተማሪዎች ከህግ ውጭ በሆነ መንገድ በትውልድ ኣገራቸው፣ የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ ሃይማኖት፣ ሃብት እና ገንዘብ፣ ስንክልና፣ ጾታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ እራስቸውን በሚገልጹበት ወይም የሚለዩበት ጾታ፣ እርግዝና፣ ኣስቀድሞ በመያዝ ወይ በመታሰር፣ የካል ወይም የኣእምሮ ስንክልና ወይም ያርበኘነት እና የውትድርና ያላግባብ ኣድልዎ ሊካሂድባቸው ኣይገባም። እንደዚህ ያሉ ልዩነቶች የተማሪውን ዓቅም ለመወሰን ወይም የተማሪውን ችሎታ ኣስቀድሞ ለመወሰን መመዘኛ ሊሆኑ ኣይገባም።

[3] WAC 392-400-227 እና የትምህርት ቦርዱ ፖሊሲ ቁጥር 3240።

## የተማሪዎች ሓላፊነቶች

የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በግል ሓፊነት መውሰድ ኣለባቸው፤

- ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያምኑት ኣዋቂ ሰው ጋር ኣእምሮኣቸውን፡ ስሜታቸውን እና ኣካላቸውን የሚጎዳና የሚያስጨንቃቸው ነገር ካለ ስለዚህ ጉዳይ መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት ማማከር ይችላሉ።
- ትምህርታቸውን፣ የባህላቸውን፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ሁኔታቸውን የሚመለከቱ ነገሮች ለማስከበር መጣበቅ።
- ከሌሎች ተማሪዎች እና የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት ጋር እርስ በርስ መከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መፍጠር።
- ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ስነስርዓት ሳያሟሉ ሲቀሩ እና ከስተታቸው እንዲማሩ የተሰጣቸውን እድል ባግባብ ሳይጠቀሙበት ሲቀሩ ተመጣጣኝ የሆነ መቀጮ እንደሚወሰንባቸው ማወቅና ላጠፉት ጥፋት ሓላፊነት መውሰድ እና የተበላሸ ዝምድናን የመጠገን ሓላፊነት እንዳለባቸው ማወቅ።
- ትምህርት ቤት በመደበኛ ሁኔታ መከታተል እና ወደ ሁሉም ክፍል እኩል መዘጋጀት።
- ደህንነቱ የተጠበቀ እና ኣወንታዊ የትምህርት ኣከባቢ መፈጠር ላይ መሳተፍ።
- የሌች ቡድኖች እና ሰዎች መብት ማክበር እና እነሱም መብት እንዳላቸው ግምት ውስጥ ማስገባት።
- “የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መሰረታዊ ሕጎች እና መመሪያዎች” እና የያንዳንዱ ትምህርት ቤት መመሪያ ማወቅ እና ማክበር።
- ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ የደህንነት እና የጤና ችግር በማያስከትል መንገድ ባግባብ መልበስ።
- ለትምህርት ቤት ባልደረቦች ሲጠየቁ መልለስ መስጠት እና ማንነታቸው መግለጽ። መመሪያቸውን መከተል እና ማክበር፤ እና
- የሌሎችን እና የትምህርት ቤት ንብረት ማክበር።[4]

## የትምህርት ቤት ሓላፊነቶች

የትምህርት ቤት ባልደረቦች የሚከተሉት ሓላፊነቶች ኣሏቸው፤

- ደህነቱ የተጠበቀ እና መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ መፍጠር፤
- ተማሪዎችን ማወቅ፣ መንከባከብ እና መልካም ዝምድና መመስረት፣
- እያንዳንዱ ተማሪ ላይ በእኩል በከፍተኛ ተስፋ ማኖር እና ጥራት ያለው ኣና ውጤታማ ትምህርት ማቅረብ፣
- ትህትና እና ኣክብሮት የትሞላበት ኣያያዝ ማሳየት፣
- የትማሪዎች ድምጽ እንዲሰማ የተለያዩ እድሎች ማቅረብ፣
- ትምህርት ቤት ያሉ ችግሮ ኣፈታት ላይ ቤተሰቦች እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- የሚፈጠሩ ችግሮችን ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲፈቱ ማበረታታት፣ እና
- የምህርት ግዜ ማባከንና ከትምህት ቤት ውጪ የሚሰጥ ቅጣት ማጉደል እና ብሎም ማስወገድ።
- የስነስርዓት እርምጃ ዓላማ የጠባይ መሻሻልን ለማገዝ እንጂ ለመቅጣት ኣለመሆኑን መረዳት፤ እና
- ሓላፊነት መውሰድን የሚያስተምር እና የተበላሸን ዝምድና ማቃናት ላይ ያተኮረ የስነስርዓት እርምጃ መስጠት።

[4] ማስታወሻ: RCW 28A.635.060 የሆነ ተማሪ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ንብረት የሆነ፣ ሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የተኮናተረው ሰው ንብረት፣ የሰራተኛ ወይም የሌላ ተማሪ ንብረት በፈቃዱ ካጠፋ ወይም ከቆረጠ፣ ምስል ካበላሸ ወይም ከጎዳ የትማሪው ወላጆች ወይም ኣሳዳጊዎች የጥፋትን ዋጋ እስኪከፍሉ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የተማሪውን ውጤት፣ ሰርቲፊኬት እና ትራንስክሪፕት የመያዝ መብት ኣለው። ተማሪው እና ወላጆቹ ወይም ኣሳዳጊዎቹ ለተፈጠረው ጥፋት መክፈል ካልቻሉ፤ ተማሪው ያጠፋውን ንብረት ዋጋ መጠን ለማካካስ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የበጎ ፍቃድ ስራ ኣዘጋጅቶ ተማሪው ኣንዲሰራ ያደርጋል። ተማሪው የበጎ ፈቃድ ስራውን ካጠናቀቀ ቡኋላ፤ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የተማሪውን ውጤት፣ ሰርቲፊኬት እና ትራንስክሪፕት ይሰጠዋል።

የሆነ እላይ የተጠቀሰው ማእቀብ ያልተቀበል ተማሪ፣ ወላጅ ወይ ኣሳዳጊ የስነስሮኣት ውሳኔ ይግባኝ ኣፈጻጸም (WAC 392-400-240) በሚያዘው መሰረት በሕግ የመሰማት መብት ኣላቸው።

# የተማሪዎች ስነስርዓት[5]

ሁሉም ተማሪዎች የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች እና ሕጎች የማክበር ሓላፊነት ኣለባቸው። የነዚህ ተጽፈው ያሉ ሕጎች ዓላማ በጎ ዓላማ ላይ የተመሰረቱ እና ሁሉም ላይ በእኩል፣ በኣንድ ዓይን እና ፍትሓዊ በሆነ መንገድ የሚተገበሩ ኣወንታዊ የስነስርዓት እና ኣራሚ እርምጃዎች መደንገግ ነው። ተማሪዎች እነዚህ የተደነገጉ ሕጎችን እና መመሪያዎች ትምህርት ቤት ባሉበት ወቅት፣ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ የትምህርት ክልሉ ባዘጋጀው መጓጓዣ ወይም የትምህርት ክልሉ ባዘጋጀው በዓል ላይ በሚተላለፉበት ወቅት ኣራሚ የስነስርዓት እርምጃ ይወሰድባቸዋል። ተማሪዎች ከነዚህ የሆኑ የተደነገጉ ሕጎችን እና መመሪያዎች ኣንዱን በሆነ ኣጋጣሚ ከሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ስራ ጋር ሙሉ ወይ መጠነኛ ግንኙነት ያለው ኣጋጣሚ ለምሳሌ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ (በነዚህ ብቻ ግን የተወሰነ ኣይደለም) የተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ደህንነት ማስከበር እና የትምህርት ሂደትን ደህንነት ማስከብር የሚነካ ነገር ከተሳተፉ ኣራሚ የስነስርዓት እርምጃ ይወሰድባቸዋል። እነዚህ በጽሑፍ የሰፈሩ መመሪያዎች እና ደንቦችን ከልክ በላይ መተላለፍ የሚከተሉትን የስነስርዓት እርምጃዎች ለምሳሌ የትምህርት ክልሉ በሚያዘጋጃቸው በዓላት ላይ ከመሳተፍ መታገድ፣ የትምህርት ክልሉ በሚያዘጋጃቸው መጓጓዣ መከልከል ወይም ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም መባረር።

ጉዳዩ ገለልተኛ በሆነ ሶስተኛ ኣኻል እንዲታይ ለማስቻል እና ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የተወሰደው የስነስርዓት እርምጃ ቅኑነት ኣምነው ኣንዲቀበሉ ለማስቻል የይግባኝ መብት እና የይግባኝ ኣፈጻጸም ኣቋመናል።

### የትምህርት ክልሉ ሰራተኞች ስልጣን

ተማሪዎችን ስነስርዓት እንዲያከብሩ የማድረግ ሓላፊነት ያላቸው ግለሰቦች:[6]

1. የትምህርት ቦርዱ ሰርተፊኬት ላላቸው ኣስተማሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች፣ የኣውቶቡስ ሹፌሮች እና ሌሎች የሆኑ የትምህርት ክልሉ ባልደረቦች ተምሪዎች የተደነገጉትን የትምህርት ክልሉ መመሪያዎች እና ሕጎች በሚተላለፉበት ግዜ የስነስርዓት እርምጃ እንዲወስዱባቸው መብት ይሰጣል። እነዚህ ግለሰቦች በተጨማሪ ስርዓት የተላለፉ ተማሪዎችን ከሆነ ክፍል፣ የትምህርት ዓይነት ወይ እንቅስቃሴ ሊያስወግዱ ይችላሉ።

2. የትምህርት ቦርዱ የትምህርት ሂደንትን ያደናቀፉ ወይም የረበሹ ተማሪዎችን ከክፍል ለተቀረው የትምህርት ክፍለ ግዜ ወይም የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪ እና ምምህሩ ስለጉዳዩ እስኪነጋገሩበት ድረስ (የትኛውም ቀድሞ ይምጣ) ኣስተማሪዎች የማባረር መብት ኣላቸው። ያደጋ ግዜ ኣጋጣሚ ካልሆነ በስተቀ ኣስተማሪው ተማሪውን ከማባረሩ በፊት ኣንድ ወይ ሁለት የተለየ ዓይነት የስነስርዓት እርምጃ መሞከር ኣለበት። በምንም ዓይነት ሁኔታ ካስተማሪው ፍቃድ ሳያገኝ ተማሪው ተመልሶ ክፍል እንዲገባ ኣይፈቀድለትም።

3. የትምህርት ቦርዱ የትምህርት ቤት ርእሰ መምህር፣ ረዳት ርእሰ መምህር እና የነሱ ወኪል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ቅታት፣ ትምህርት ቤት ወስጥ መታገዶች፣ ለእጭር ግዜ መታገዶች፣ ለረጅም ግዜ መታገዶች፣ ያደጋ ግዜ ማባረሮች እና ጠቅላላ መባረር ውሳኔዎችን እንዲወስኑ መብት ይሰጣል።

### ለስነስርዓት እርምጃ ለመውሰድ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች እና ገደቦች [7]

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሕግ እና መመሪያዎች የተላለፉ ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የስነስርዓት እምጃ ኣካላዊ ቕጣትን ኣያጠቃልልም።

ኣካላዊ ቅጣት የሚከተሉትን ኣያክካትትም፤

ሀ. በትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች፣ መማህራን፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በጎፍቃደኞች ስነስርዓት ለማስከበር ወይም ተማሪዎች እራሳቸውን፣ ሌሎች ተማሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች ወይም ንብረት እንዳይጎዱ ለመከላከል ምክንያት ያለው ኣካላዊ ሓይል መጠቀም።

ለ. ተማሪው በፈቃዱ የተሳተፈበት ከባድ ትሬኒንግ ወይም ኣትሌቲካዊ ውድድር ወይም መዝናኛ ፕሮግራም ላይ ከመሳተፍ የሚመጣ የተማሪው ላይ ኣካላዊ ሕመም የሚያስከት ወይም ምቾት የሚነሳ ሁኔታ።

---

[5] WAC 392-400-210
[6] WAC 392-400-230
[7] WAC 392-400-235

ሐ. በሁሉም ተመሪዎች የሚካሄድ ኣስተማሪ ያዘዘው እንቅስቃሴ ላይ በመሳተፍ የሚከተሉትን ያሚያጠቃልል በነዚህ ግን ያልተወሰነ ለምሳሌ የስፖርት ትምህርት እንቅስቃሴ፣ የመስክ ጉዞ ወይም የሙያ ትምህርት ፕሮጀክት ላይ በመሳተፍ የሚመጣ አካላዊ ድካም። ወይም

መ. ተማሪውን ግልጽ ከሆነ እደገኛ ኣደጋ ሊያስከትል የሚችል የሚታይ ሁኔታን ለመከላከል እና በትምህርት ክልሉ እና በስቴት መመሪያ መሰረት የተካሄደ ምክንያታዊ ኣጥብቆ መያዝ ወይም መለየት።

## ሕጋዊ ማሳሰቢያ

ይህ ዶኩሜንት ላንዳንድ ሰዎች ኣፀያፊ ወይም ስሜትን ሊነኩ የሚችሉ ቃላት እና ትርጉሞችን ይዟል። ወላጆች/ሞጉዚቶች ልጆቻቸው ይህን ዶኩሜንት ያለምንም ክትትል ወይ ቁጥጥር እንዲያነቡ መፍቀድ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ኣለባቸው።

ይህ ዶኩሜንት ዓላማው የተማሪዎችን ጠባይ እና ስነስርዓት በተመለከተ መረጃ ማቅረብ ነው። የትምህርት ቤት ሰራተኞች ጠባይ እና ስነስርዓት በተመለከተ ብዙ ዶክሜንቶች እንደ ትምህርት ቦርድ ፖሊሲ እና ኣሰራር እና ተግባራዊ የሆኑ የጋራ መደራደሪያ ስምምነቶች ላይ ይገኛል። ኣንዳንድ የት/ቤት ሰራተኞች ተግባራት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ካልዎ እባክዎ የሰራተኛውን ሓላፊ ያነጋግሩ።

# የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሓላፊነቶች

*ያሉትን የእድል ክፍተቶች ማስወገድ እና ጥራቱ ከፍ ያለ ትምህርት ለሁሉም እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ማዳረስ የግዜያችን ኣብይ ጉዳይ ነው።*

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ እውቅና ይሰጣል፤

- ትምህርት ክልሉ ውስጥ ዘር ላይ የተመረኮሰ እጅግ በጣም የተዛባ የስነስርዓት እርምጃ መኖሩን፤
- እያንዳንዱ የስነስርዓት እርምጃ የሚያስከትል የስነስርዓት መጓደል የትምህርት ክልሉ ሰራተኞች ሊረዷቸው የሚገቡ የተማሪ የስነስርዓት መጉኣደል ጠንቆች በጣም የተወሳሰቡ እና ጥልቅ ርጂ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን፤
- የስነስርዓት እርምጃ ኣወሳሰድ ሂደቱ ላይ ጉዳዩን የሚያሻሽሉ እና የሚያባብሱ ነገሮች ውሳኔ ውስጥ መካተት እንዳለባቸው፤ እና
- የማግለል እርምጃ ሁሌም መጠቀም ጠንቅ እንዳለው።

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ባልደረቦች የሚከተሉት ሓላፊነቶች ኣሏቸው፤

- ተማሪዎችን ማወቅ፣ መንከባከብ እና ኣወንታዊ የሆነ መልካም ዝምድና መመስረት፣
- ተማሪውን በሁሉም መልኩ መረዳት፣
- እያንዳንዱ ተማሪ ላይ በእኩል በከፍተኛ ተስፋ ማኖር እና ጥራት ያለው ኣና ውጤታማ ትምህርት ማቅረብ፣
- ተማሪዎች ላይ መልካም የሆኑ የማህበራዊ፣ የስነልቦናዊ እና የጠባይ ችሎታዎችን ማስተማር እና ማዳበር ፣
- ኣንዴ ጉዳቱ ከደረሰ ወይም ጥፋቱ ከተፈጸመ ቡኋላ ተማሪውን በማግለል ፋንታ ጠባዩን ለማረም የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም፣
- የተማሪውን እና የትምህርት ቤት ዝምድና በተቻለ መጠን የማይጎዳ እና የተማሪውን የትምህርት ግዜ በተቻለ መጠን የማያባክን የስነስርዓት እርምጃ መውሰድ፣
- የስነስርዓት እርምጃ በሚወሰድበት ወቅት ከወላጆች፣ ሌሎች የትምህርት ቤት ሰራተኞች እና የማህበረሰብ ማሕበራት ጋር ዝምድናን በመፍጠር ቢጋር መወሰን፣ እና
- ተማሪዎቻችንን ትምህርት ላይ ውጤታማ ማድረግ  ዓላማ ላይ ያተኮረ ከባህላቸው ጋር የሚስማማ ተገቢ የሆነ መልስ የሚሰጥ፣ የተማሪውን ሁኔታ ያገናዘበ ነገሮችን በውይይት ማብረድ ችሎታ ላይ ያተኮረ የትምህርት ኣከባቢ ለመፍጠር በሚሰሩበት ወቅት፤ በውስጣቸው ያለውን የማይገለጽ (ኣብሯቸው ያደገ) ኣድልዎ መመርመር።

`

# የተማሪዎች ጠባይ

**Arson / ሆን ብሎ እሳት ማቃጠል**
*ሆን ብሎ እሳት ማቃጠል ወይም ፍንዳታ ማስስከተል።*

**Assault / ድብድብ** (እባካችሁ የነገሩ ክብደት በምትወስኑበት ወቅት መምታት ወይም አካላዊ ጉዳት ማድረስ የሚለውን ክፍል እዩ)።
*ቁጣን ወይም ጥላቻን የሚያነሳሳ መነካካት ላይ መሳተፍ ወይም መጠመድ። ይህ ስራዬ ብሎ ኣውቆ ተማሪዎች እንዲደባደቡ ማድረግ ወይም በፍቃድ እንደዚህ ያለ ኣስቀድሞ የታሰበበት ተደባደቢዎቹ ላይ ኣደኛ አካላዊ ጉዳትና መቁሰል የሚያደርስ ድብደብ ላይ መሳተፍ ያጠቃልላ።*

**(Physical) Aggression / መምታት ወይም ኣካላዊ ጉዳት ማድረስ**
*መደባደብ ወይም በእጅ መምታት፣ ሃይል መጠቀም ወይም ኣውቆ ለመደብደብ ማሰብ እና በቅጽበት ሌላ ሰውን መደብደብ ወይም ምምታት ያጠቃልላል።*

ይህ ሕግ ተግባራዊ የሚሆነው እንደዚህ ያለ ጥፋት ወይም የስነስርዓት መተላለፍ የሚያስጠይቅ መሆኑን ሊረዱ ለሚችሉ እና በቂ ብስለት እና ስሜት የመቆጣተር ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ነው።

**Bullying, Intimidation, or Harassment / መወትወት/መነዝነዝ (ቡሊንግ)፣ ወከባ ና ጥቃት**[8]
የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ሆንብሎ ተደጋጋሚ እና ኣስቆጪ ተግባራት በጽሑፍ፣ በቃላት፣ በኤሌክትሮኒካዊ መሳሪያዎች ወይም በኣካል መወትወት/መነዝነዝ ማስፈራራት ወይም ማጥቃት የመሳሰሉ ተግባራት የሚያጠቃልል በነዚህ ግን ያልተወሰነ፤

- ኣንድን ሰው የማሳፈር ወይም የማዋረድ ዓላማ ያለው
- ኣንድ ሰው ላይ ኣካላዊ ኣና የንብረት ጥፋት የሚያደርስ ተግባራት
- የደረሰው ጥፉ የማይጠፉ እና ኣደገኛ ወይም ሁሉም ላይ ፍርሃት የሚፈጥር ሲሆን ወይም የትምህርት ኣከባቢው ላይ ፍርሃት ከፈጠረ፣
- የተማሪውን ጤናማ የትምህርት ኣከባቢ ላይ ጣልቃ ከገባ እና ሰራተኞችን የማስተማር ወይም ተማሪዎችን የማስተዳደር መብታቸው ከነካ ወይም
- የትምህርት ቤቱን ስነስርዓት የትሞለባት እለታዊ ተግባራት ካደናቀፈ።

*(በተጨማሪ ክፋት ላይ የተመረኮሰ ማጎሳቆል ተመለከት) የትምህርት ክልሉ ከትምህርት ቤት ውጪ በተማሪዎች የሚደረጉ ንግግሮች ትምህርት ቤት ውስጥ ከፍተኛ ረብሻ የሚያደርሱ ከሆኑ እና ተማሪዎችን በሰላም ትምህርታቸውን ኣንዳያገኙ እና ኣዲረበሹ የሚያደርጉ ንግግሮች ላይ ትምህርት ቤቱ እርማጃ ይወስዳል። ግምት ውስጥ የሚገባ መረበሽ የሚከተሉትን ያጠቃልላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም፤ ትምህርት ላይ፣ የትምህርት እንቅስቃሴ ወይም የትምህርት ቤት የስራ ሂደት መረበሽ እና ተማሪዎች መሃል ዓመጽ የተሞላበት የኣካልና ሃይለ ቃል መለዋወጥ ያካተተ ወይም የትምህርት ሂደትን የሚያቛርጥ ኣከባቢ መፍጠር። መወትወት/መነዝነዝ፣ ማስፈራራት ወይም ማጥቃት የመሳሰሉ ተግባራት ወይም ባሕሪያት እንደዚህ ያለ ባህሪ ከሚያሳይ ሰብ ብቻ እንዲመጣ መጠበቅ የለብንም።*

*ይህ የህግ መጣስ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያጠቃልላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም፤*

- ኤሌክትሮኒክስ ተጠቅሞ መወትወት/መነዝነዝ (ቡሊንግ)፣ ማስፈራራት እና ማስጨነቅ ይህ ከሚከተሉት ተግባራት ኣንዳንዱን ያጠቃልላል፤ ሳይበር ቡሊንግ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ግዜ፣ የትምህርት ቤት ኣውቶቡስ ላይ ወይም በመደበኛ የትምህርት ግዜ።
- ተማሪዎች በትምህርት ቤት፣ በቡድን፣ በትምህርት ደረጃ ወይም ጽህፈት ቤት ኣሰባስቦ ቢጋራ በመፍረድ፣ በማስፈራራት ወይም ሓይል በመጠቀም ማሕበራዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ጉዳት ማስከተል ወይም ሊያስከትል የሚችል ተግባር መፈጸም። (ኣስቀድሞ D-210 ኣዋርዶ መመልመል)

*ማንም ሰው ቢሆን ሌሎችን ለመወትወት/መነዝነዝ (ቡሊንግ)፣ ወከባና ለማጥቃት ምንም ዓይነት መግለጫ የሚገኝለት ምክንያት የለውም።*

---

[8] **ሆን ብሎ ለመጉዳት በክፋት ማጎሳቆል** የተለየ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ደረጃ ላይ ተመስርቶ ማዋከብ እና ማስፈራራት ባህሪያት ተመልከት። በተጨማሪም RCW 28A.300.285 ተመልከት።

**Burglary / ቤት ሰብሮ መዝረፍ**
*ይህ በደል በሃይል ሰብሮ መግባት ወይም ያለፈቃድ ትምህርት ቤት ህንጻ ውስጥ መቆየት፣ የትምህርት ክልሉ ህንጻ ወይም ክፍል ውስጥ ንብረት ለመውሰድ ወይም ለመስረቅ ተደብቆ መቆየት።*[9]

**Computer Trespass, Tampering, and Misuse / የሌላ ሰው ንብረት የሆነ ኮምፒተር ውስጥ ያለፍቃድ መግባት ፣ ይዘት መቀየር እና ያላግባብ መጠቀም**[10]
*የትምህርት ቤት ወይም የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የኮምፒተር ስርዓት (ሲስተም) ወይም የኮምፒተር መረጃ(ዳታቤዝ) ኢያወቁ መጣስ*

**Dangerous Weapons / ኣደጋኛ መሳሪያዎች**[11]
*ኣደጋኛ መሳሪያዎችንሪያዎች ወደ ትምህርት ቤት ወይም ኣደጋኛ መሳሪያዎችንሪያዎች ወድ ትምህርት ቤት ንብረት፣ ትምህርት ቤት የሚያቀርበው መጓጓዣ፣ እንደ ትምህርት ክልሉ ንብረት ሆኖ የሚያገለግል ቦታ ወይም ትምህርት ቤት ባዘጋጀው የሆነ ኣጋጣሚ ይዞ መገኘትን ያጠቃልላል።*

**Disobedience (Not an exclusionary action for K-5 students) / ትእዛዝ ኣለመቀበል (ከመዋለህጻናት እስከ 5 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ለይቶ የማያይ ጉዳይ)**
*የሆነ የሚሰጥ መመሪያን ኢያወቁ ግልጽ እና ኣስነዋሪ በሆነ መንገድ፣ ሆንብ ተብሎ ወይም ተደጋጋሚ የመማህራን እና ሌላ ትምህርት ቤት ሰራተኞች ትእዛዝ ኣለመቀበል።*

**Disruptive Conduct (Not an exclusionary action for K-5 students) / መረበሽ (ከመዋለህጻናት እስከ 5 ክፍል ላሉ ተማሪዎች ለይቶ የማያይ ጉዳይ)**
*ኣስነዋሪ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ክፍል ውስጥ፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወይም ከትምህርት ጋር ያልተሳሰሩ ሌላ ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚደረግ የመማር ማስተማር ሂደት የሚያደናቅፍ።*

**Distributing Alcoholic Beverages / የኣልኮል መጠጦችን ማከፋፈል**
*ኣልኮል ወይም የሆነ ኣልኮሆልነት ያለው መጠጥ ማከፋፈል፣ መካፈል፣ ማዞር ወይም ማስተላለፍ ያጠቃልላል።*

**Distributing Illegal Drugs, Controlled Substances, Prescription or Over-the-Counter Drugs / ሕጋዊ ያልሆኑ ኣደገኛ ዕጾች፣ ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች እና በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱቅ ማርከት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች ማከፋፈል ወይም መሸጥ**
*ኣደንዛዥ ወይም ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች: በሓኪም መታዘዝ የሚገባቸው መድሃኒቶች ወይም ከመድሃኒት ቤት የሚገዙ መድሃኒቶች እና ሕጋዊ ያልሆኑ ዕጾች ተቀላቅሎበት የተሰራ ምግብ እና የኤሌክትሪክ ሲጋራ ወይም ውስጡ ህጋዊ ያልሆኑ ኣደንዛዥ ዕጾች የተሞላ የኤሌትሪክ ማጨሻ መሳሪያ እና ሌሎችንም መሸጥ፣ ለመሸጥ ማሰብ እና ማከፋፈልያጠቃልላል።*

**Distributing Marijuana / ሓሽሽ (ማሪዋና) መሸጥ**
*የሆነ ዓይነት ሓሽሽ (ማሪዋና) ማከፋፈል፣ ማካፈል እና ማዞር፡ የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ግን በነዚህ ብቻ ግን ያተወሰነ፣ ለመድሃኒትነት በሓኪም የታዘዘ፣ እቤት የበቀለ፣ ከሱቅ የተገዛ ወይም ከመንገድ የተገዛ ሓሽሽ፣ የሆነ ሓሽሽ ያለው ምግብ እና የኤሌክትሪክ ሲጋራ ወይም ውስጡ ሓሽሽ የሞላ የኤሌትሪክ ማጨሻ መሳሪያ መሸጥ ወይም ለመሸጥ መሞከር ያጠቃልላል።*

**Extortion, Blackmail, Coercion / ማስፈራራት፣ ያለውዴታ የሆነ ነገር እንዲፈጽም ማስገደድ፣ በጉልበት መቀማት**
*ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ዋጋ ያለው ነገር በማስፈራራት መውሰድ ወይም ሌላ ሰው ከፍቃዱ ውጪ ያለውዴታ የሆ ነገር በሃይል በማስፈራራት እዲፈጽም ማድረግ።*

**False Alarm / የውሸት ያደጋ ምልክት/ጥሪ**
*የእሳት ኣደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል ወይም የ 911 ስልክ ደወሉ ወይም ስልኩ ከተመደበበት ዓላማ ውጪ መደወል።*

**False Reporting / በውሸት ያልተደረገ ነገር ሪፖርት ማድረግ**
*ኢያወቁ እና በከፋት በውሸት መወንጀል ወይም የሌሎችን ሰዎች ባልሰሩት ስማቸውን ማጥፋት ይህ ማለት ክፍል ወይም ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ የትምህርት ቤት መጓጓዣ ወይም ትምህርት ቤት ባዘጋጀው በዓል ላይ ሆን ብሎ ለመጉዳት ሃሜታ ማሰራጨት።*

---

[9] **የሌላ ሰው ንብረት ውስጥ ያለፍቃድ መግባት** የትምህርት ክልሉ ንብረት ወይም ህንጻ ውስጥ የለፍቃድ መግባትን በተመለከት ተመልከት።
[10] **ረባሽ ባህሪያት** ከኮምፒተር ጋር የተያያዘ ሳይታሰብ የተፈጸመ ወንጀል ወይም ከኮምፒተር ሕግ መጣስ ጋር እኩል ለማይሆን ወንጀል ተመልከት።
[11] **የመጫወቻ ሽጉጦችና መጫወቻ** የሚመስሉ መሳሪያ ዎች ተመልከት።

**False Threats / በውሸት ማስፈራራት**

*የትምህርት ቤት ህንጻ ወይም ተቋም፣ የትምህርት ቤት ግቢ፣ የትምህርት ቤት መጓጓዥ ወይም ትምህርት ቤት ባዘጋጀው በዓል ላይ በውሸት ቦምብ ወይም ጠመንዣ የያዘ ሰው ኣለ ብሎ ማስፈራራት።*

**Fighting / ድብድብ**

*ቁጣን ወይም ጥላቻን የሚያነሳሳ መነካካት ላይ መሳተፍ ወይም መጠመድ። ይህ ስራዬ ብሎ ኣውቆ ተማሪዎች እንዲደባደቡ ማድረግ ወይም በፍቃድ እንደዚህ ያለ ኣስቀድሞ የታሰበበት ተደባደቢዎቹ ላይ ኣደኛ ኣካላዊ ጉዳትና መቁሰል የሚያደርስ ድብደብ ላይ መሳተፍ ያጠቃልላ።*

**Firearms / ጠመንዣ [12]**

*ጠመንጃ ወደ ትምህርት ቤት ወይም ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ የትምህርት ቤት ንብረት፣ ትምህርት ቤት ያቀረበው መጓጓዥ፣ የትምህርት ክልሉ ያዘጋጀው በዓል ወይም የትምህርት እንቅስቃሴ መጠቀሚያ ቦታ ይዞ መምጣት ወይም መገኘት።*

**Fireworks, Explosives, Chemicals, and Incendiary Devices / ርቺቶች፣ ፈንጂዎች ፣ ኬሚካሎች እና የሚቃጠሉ ነገሮች**

*ርቺቶች ወይም ፈንጂዎች፣ ኬሚካል ወይም ተቀጣጣይ ነገሮች የትምህርት ቤት ንብረት፣ ትምህርት ቤት ያቀረበው መጓጓዥ፣ የትምህርት ክልሉ ንብረት፣ ትምህርት ቤት ያዘጋጀው በዓል ወይም የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ መያዝ ወይም መጠቀም።*

**Gambling** / **መቋመር**

*በገንዘብ ወይም ሌላ ዋጋ ያለው ነገር ካርታ፣ ዳይ (ጠጠር) ወይም ሌላ ጨዋታዎች መጫወት።*

**Gang/Hate Group Activity / የወረበሎች/የጥላቻ ቡድን እንቅስቃሴ[13]**

*የተደራጀ የወረበሎች ቡድን፣ የጥላቻ ቡድን ወይም ተመሳሳይ ማህበር ወይም ቡድን እና እያወቁ ኣባል መሆን እና የወረበሎች/ የኣመጻኞች ቡድን እንቅስቃሴ ወይም ተግባር ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም የሆነ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ወይም ተግባራት ላይ የረብሻ እና የጥላቻ እንቅስቃሴ ማካሄድ።*

**Grafitti / የግድግዳ ስእል (ግራፊቲ)[14]**

*በሆነ የትምህርት ክልሉ ንብረት ወይም የትምህርት ቤት ንብረት ላይ እያወቁ መጻፍ፣ መቀባት፣ መሳል፣ መጫር ወይም የሆነ ሌላ ምልክት መጻፍ፣ ስእል ወይም የሆነ ምልክት የትምህርት ቤት ስራተኞች ወይም ተማሪ ንብረት ላይ ከትምህርት ኣስተዳዳሪዎች ወይም ከትምህርት ቤት ስራተኞች ፍቃድ ሳያገኙ ማድረግ።*

**Hazing / ኣዋርዶ ወይም ኣሳፍሮ መመልመል (ሄዚንግ)[15]**

*ተቀባይነት የሌለው ሕገወጥ ተርጉም ኣልቦ የሆነ ደጋግሞ በማስጨነቅ ወይም በመገፋፋት ኣስቸጋሪ፣ ኣደገኛ ወይም የሚያሳፍር ተግባራት ሆንብሎ በማዘጋጀት ተማሪውን ወደ ኣንድ ማህበር ወይም ቡድን እንዲገባ ማድረግ ብሎም ለጸብ እና ለኣደጋ በሚጋለጥ የኣካል መቁሰል[16] ወይም ሌላ ኣደጋ ማስከተል።*

---

[12] ስክልና ላላቸው ግለሰቦች የሚመለከት ኣንቀጽ (Individuals with Disabilities Education Act ...." 20 U.S.C. § 7151(c)) በሚስማማ መሰረት ኣስገዳጅ የኣንድ ዓመት መባረር ይወሰንበታል።

[13] የደህንነት እና ጸጥታ ክፍል ስለዚህ ወንጀል መጠቀም ኣለባት። ኣስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሲያትል ፖሊስ ሊጠቀም ይገባል።

[14] **ንብረት ላይ ጥፋት ማድረስ ወይ ማውደም** ለማጽዳቱ ከ$100 በለይ የሚያወጣ የግድግዳ ስእል ተመልከት።

[15] **መወትወት/መነዝነዝ** (ቡሊንግ)፣ **ማስፈራራት እና ጥቃት** ትንሽ ቀለል ላሉ ጥፋቶች *ተመለከት።*

[16] **ዓመጽ ወይ ኣካል ላይ ጥቃት ማውረድ** የሚለውን ኣካላዊ ጥቃት ያካተተ ባህሪያት ኣዋርዶ መመልመል ተመልከት።

**Inappropriate Language** (previously Verbal Assault) **/ ኣግባብ የሌለው ቃላት** (ኣስቀድሞ የቃላት ማጥቃት)[17]

*የሚከነክን፣ ጎጂ፣ ኣዋራጅ፣ ሃይለቃል ወይም ኣሳፋሪ ቃላት መጠቀም በተጨማሪም እንደ ብልግና፣ ስድ እና ኣጸያፊ ቃላት መጠቀም።*

**Inappropriate Sexual Conduct / ተገቢ ያልሆነ ጾታዊ ባህሪያት**

*ተገቢ ያልሆነ በባህሪው ጾታዊ ሁኔታዎችን የሚያመላክት የትምህርት ሂደትን የሚረብሽ ተገቢመነካካት። (በተጨማሪ ተገቢ ያልሆነ መነካካት፣ ባለጌ ወይም ኣጸያፊ ተግባር፣ ጾታዊ ጥቃት እና ጾታዊ በደል የሚሉትን ክሎች እዩ)።*

**Inappropriate Touching / ተገቢ ያልሆነ መነካካት**[18]

*የሌላ ሰውን ኣካል ባላስፈላጊ ወይም ተገኒ ባልሆነ መንገድ መንካት በተለይ ተነኪው ተግባሩ ከረበሸው።*

**Interference with School Authorities / የት/ቤት ባለስልጣናትን ማስፈራራት እና ስራቸው ላይ ጣልቃ መግባት**

*የትምህርት ክልሉ ወይም የትምህርት ቤት ስራተኞች ተግቢ የስራ ግዴታቸው በመወጣት ላይ እያሉ በሚከተለው መልኩ ጣልቃ መግባት፡*

- *ኣስቀድሞ ያልታሰበበት እና የትምህርት ቤት ስራተኞች ላይ ያላተኮረ ሃይል መጠቀም ወይም ጸብ መጫር ለምሳሌ ትምህርት ቤት ስራተኞች ጸብን ለማስታረቅ በሚጥሩበት ወቅት ጸቡን መቀጠል ወይም ሳያውቁ ስራተኛውን መምታት፤ ወይም*
- *የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እንዲወጣ ወይም እንዲለቁ በሚጠይቁበት ወቅት ትእዛዝ ኣለማክበር፤ ወይም*
- *የትምህርት ቤት ባለስላጣናት ተገቢ ስራቸውን የትምህርት ክልሉ ሕግ፣ ስርዓት እና ተገቢ ኣካሄድ ተከትለው እየሰሩ እያሉ ስርዓት እንዳያስከብሩ እና ስራቸውን እንዳያጠናቅቁ ጣልቃ መግባት፣ መረበሽ እና ማዋከብ። ይህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም፡*
    - o *የትምህርት ቤት ስራተኞች ላይ ጎጂ ወይም ኣፀያፊ ቃላትን በተደጋጋሚ*[19] *መጠቀም፣ ወይም*
    - o *ኤሌክትሮኒካዊ መንገዶች በመጠቀም (ለምሳሌ፤ ካሜራ፣ የሞባይል ካሜራ፣ ቪድዮ ወይም ሌላ መቅጃ መሳሪያዎች) ትምህርት ቤት ስራተኞች ሊያሳፍሩ፣ የሚያዋርዱ እና ክብር የሚያሳጡ ነገሮች ማፈጸም።*

    *ወይም*

    - o *የትምህርት ቤት ስራተኞች እንድን ጉዳይ በሚመረምሩበት ወቅት እያወቁ በመዋሸት ስራውን ማደናቀፍ ይህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም ኣልፈተሸም ማለት ወይም ማቅማማት ወይም ለተጠየቁት ትያቄ መልስ ኣልሰጥም ማለት ወይም ስለ ጉዳዩ ጭብጦች ሌሎች እያወቁ እንዲዋሹ ማበረታታት ወይም መገፋፋት።*

**Intimidation of School Authorities** / **የትምህርት ቤት ባለስልጣናትን ማስፈራራት**

*የትምህርት ቤት ሰራተኞች መደበኛ ስራቸውን በሚሰሩበት ወቅት ቀጥተኛ፣ እያወቁ ወይም ለይተው ሃይል እጠቀማለሁ ወይም ዓመጽ እፈጽማለሁ ብሎ በማፈራራት ሰራተኛው ደህንነቱ ወይም ንብረቱ ኣደጋ ላይ የወደቀ ሆኖ እስኪሰማው ማደርግ እና ማቋረጥ ወይ ጣልቃ መግባት ወይም ለማቋረጥ ወይ ጣልቃ ለመግባት መሞከር ።*

**Lewd Conduct / ባለጌ ወይም ኣጸያፊ ተግባራት**[20]

*ተገቢ ያልሆነ ወይም ኣጸያፊ የሆነ ጾታዊ ወይም ማህበራዊ ጸባይ ወይም ተግባር ላይ መሳተፍ ለምሳሌ ጾታዊ ተግባራት ለብቻ ወይም ከሌላ ሰው ጋር በስምምነት መፈጸም፤ ጥቂት ምሳሌ ለመጥቀስ ጾታዊ ግንኙነት፣ የኣፍ ጾታዊ ግንኙነት፣ ጾታዊ መነካካት፣ ግልጽ የሆነ ጾታዊ ግንኙነት ወይም ተግባራት መፈጸም ወይም ከጾታዊ ግንኙነት ጋር የተሳሰሩ ነገሮችን ተደብቆ ማየት ይስጠቃልላል። (በተጨማሪ ተገቢ ያልሆነ ጾታዊ ባህሪያት፣ ተገቢ ያለሆነ መንከት፣ ወሲብ የሚያመላክት መነካካት፣ ጾታዊ በደል፣ ጾታዊ ጥቃት ተመልከቱ)።*

---

[17] **ድብድብ ወይም የዓመጽ ማስፈራራቶች** ለተጨባጭ እና ኣንድ ሰው ላይ ያተኮረ የዓመጽ ማስፈራራቶች ተመልከት።
[18] **ጾታዊ ዓመጽ** ለከፋ የስነስርዓት ጉድለት ወይም በትልቅ ተማሪዎች ተገቢ ላልሆነ መነካካት ባህሪያ ተመልከት።
[19] **ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ** ኣንዳንድ ግዜ መጠቀም በተመለከተ D-340 ተመልከቱ።
[20] **ጾታዊ ዓመጽ** ሃይል በመጠቀም ወይም ኣካላዊ ጉዳት በማድረስ ለተፈጸም ተመለከት። በተጨማሪ **ኣጸያፊ ጾታዊ ባህሪያት** ተገቢ ያልሆነ ጾታዊ ተግባራት ላይ ያተኮረ ባህሪያት ተመልከት።

## Malicious Harassment / ተንኮል ላይ የተመረኮሰ ማዋከብ[21]

*ሆን ብሎ ኣንድን ግለሰብ በዘሩ፣ የቆዳ ቀለም፣ ሃይማኖት፣ በትውልድ ኣገሩ፣ ጾታው፣ ጾታዊ ዝንባሌው፣ ጾታዊ መለያው ወይም የኣእምሮ ወይም ኣካላዊ ስንክልና ላይ ተመኩሶ ሆን ብሎ ለመጉዳት እና እያወቁ ማዋከብ።*

- *ተጠቂው ላይ ወይም ሌላ ግለብ ላይ ኣካላዊ ጉዳት ማድረስ።*
- *የተጠቂው ወይም የሌላ ግለሰብ ንብረት ላይ ጥፋት ማድረስ ወይም ማውደም።*
- *ማስፈራራት ኣንድ ግለሰብ ወይም ሌሎች ሰዎች ላይ ወይም የተወሰኑ ግለሰቦች ላይ በሂወታቸው እና ንብረታቸው ኣደጋ እንዳይደርስባቸው እንዲሰጉ ማድረግ። ይህ የመማር መብታቸው ወይም ትምህርት ቤት ግቢ የሚኖራቸው ደህንነት ኣደጋ ላይ መጣል ያጠቃልላል።*

*የትምህርት ክልሉ ከትምህርት ቤት ውጪ በተማሪዎች የሚደረጉ ንግግሮች ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ከፍተኛ ረብሻ የሚያመጣ ከሆነ ወይም ተመሪዎች ዋስትናቸው ተጠብቆ ትምህርታቸውን እንዳያገኙ የሚያደናቅፍ ከሆነ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል። ከፍተኛ ረብሻ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም፤ ተማሪዎች መሃከል የተፈጠረ ኣካላዊ ዓመጽ ወይም የቃላት መለዋወጥ ወይም ጥላቻ የተሞላበት ኣከባቢ ትምህርትን ሲያደናቅፍ፣ የትምህርት ቤት ስራ ሲረበሽ ወይም ትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ሲደናቀፉ እና ትምህርት ሲደናቀፍ።*

*ይህ ጥፋት መፈጸም በስቴቱ ጉዳት የሚያደርስ ጥቃት ተብሎ የሰፈረውን ጥፋት ጋር እኩል መሆን ኣለበት።*

*ጉዳት የሚያደርስ ጥቃት ግለሰብ ላይ ያተኮነ ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል፤ ባብዛኛው ግን ግለሰቡ የኣንድ ቡድን ኣባል በመሆኑ የሚፈጸም ነው። ላይ RCW 9A.36.080 የሚለውን ተመልከት (በተጨማሪ መወትወት/መነዝነዝ (ቡሊንግ)፣ ማስፈራራት እና ጥቃት የሚለውን ክፍል ተመልከቱ)።*

## Malicious Property Damage / ሆን ብሎ በክፋት ንብረት ማውደም (ኣስቀድሞ በየተንኮልና ክፋት ተግባር መፈጸም ይታወቅ የነበረ)

*ይህ በደል እያወቁ የትምህርት ቤት ንብረት፣ ትምህርት ቤት ሰራተኞች ንብረት ወይም ተማሪዎች ወይም ትምህርት ቤት ኣውቶቡሶች ላይ ጥፋት ማድረስ። በተጨማሪ ትምህርት ቤት ንብረት፣ ትምህርት ቤት ሰራተኞች ንብረት ወይም ትምህርት ቤት ኣውቶቡስ መፃፍ፣ መቀባት፣ መሳል ወይም ሌላ ነገር እንደ የግድግዳ ስእል (ግራፊቲ) መሳል በተለይ ይህ ከልክ ኣልፎ መሰወገኛው $100 የሚበልጥ ከሆነ[22]።*

## Misrepresentation / ማንነትን መደበቅ (ያልሆኑትን ሆኖ መቅረብ)

- *የወላጆች፣ የሞግዚት/ኣሳዳጊዎች ወይም የሆነ ሌላ ሰው ፊርማ ወደ ትምህርት ቤት የተላከ ደብዳቤ፣ የሆነ የትምህርት ቤት ዶኩሜንት ወይም ፎርም ወይም ትምህርት ቤቱ የሚሰራበት የሆነ ሌላ ዶኩሜንት ወይም ፎርም ላይ ኣስመስሎ መፈረም።*
- *የትምህርት ክልሉ ሕጋዊ ፎርም ላይ ከትምህርት ቤት ባለስልጣናት ፍቃድ ውጪ የትምህርት ውጤትን ወይም ኣቴንዳንስ ለሆነ ተማሪ ለምሳሌ የኣቴንዳንስ ፎርም እና የውጤት መዝገብ መቀየር።*
- *ትምህርት ቤት ባለስልጣናት ማንነትን በሚጠይቁበት ወቅት የተሳሳተ ስም መስጠት።*
- *ለትምህርት ቤት ሰራተኞች የተሳሳተ የውሸት መረጃ መስጠት ወይም የተሳሳተ ወይም ኣደናጋሪ መረጃ ለመስጠት፣ የተማሪው ትምህርት ቤት መምጣት ወይም መቅረት ለምሳሌ ከትምህርት ቤት ለመቅረት የውሸት ምክንያት ማቅረብ ወይም ተማሪው ከትምህርት ቤት ቶሎ እንዲለቀቅ የውሸት ምክንያት ለማቅረብ በቃላት ወይም በጽሑፍ ሌላ ሰውን ማስመሰል።*

## Misuse of Computers / ኮምፒተር ካግባብ ውጪ መጠቀም[23]

*የትምህርት ቤት ኮምፒተሮች ያለኣግባብ መጠቀም ሆን ብሎ ለማበላሸት መነካካት።*

---

[21] **መወትወት/መነዝነዝ (ቡሊንግ)፣ ማስፈራራት እና ጥቃት** ጥቃቱ የተማሪው ጠባይ ወይ ማህበራዊ ሁኔታ ላይ ተሞርኩሶ ካልተፈጸመ ተመልከት።

[22] ቅጣትን መክፈል ወይም ማቃለል የሚመለከት ይግባኝ፣ መቀጫዎች፣ ካሳ እና ተያዝ የሚመልከት ጉዳይ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ቁጥር D83.00 ተመልከቱ።.

[23] **የሌላ ሰው ንብረት የሆነ ኮምፒተር ውስጥ ያለፍቃድ መግባት ፣ ይዘት መቀየር እና ያላግባብ መጠቀም** ለየት ላለ ከኮምፒተር ጋር የተያያዘ ወንጀል ተመለከት።

**ሌሎች ልዩ የስነስርዓት መተላለፍ**

*በከተማ፣ በስቴት ወይም በፌደራል ሕግ መሰረት ትልቅ ወንጀል እንደ ነፍሰ ማጥፋት፣ ትንሽ ወንጀል ወይም የሆነ ወንጀል መፈጸምን ያጠቃልላል።*

*ይህ ማንኛውም ብስለቱ ወይም ስሜቱን የመቆጣጠር ሁኔታው የስነስርዓት መተላለፍ ሊያስከትለው የሚችለውን ነገር መረዳት የሚችል ተማሪ ሁሉ ይመለከታል።*

**የሌላ ሰው ጽሑፍ መስረቅ ወይም ኣስመስሎ መጻፍ**

*ማታለል ወይም የሌላ ሰው ስራ መኮረጅ ወይም የሌላ ሰው ጽሑፍ፣ ፕሮጀክት፣ የኮምፒተር ፕሮግራሞች ወዘተ… የግል ስራ ኣስመስሎ ማስረከብ*

**የተሰረቀ ንብረት ይዞ መገኘት**

*የተሰረቀ ንብረትን እያወቁ መቀበል፣ ማስቀመጥ፣ መያዝ፣ መደበቅ ወይም መስወር።*

**የኣልኮል መጠጦች መያዝ ወይም መጠቀም**

*የኣልኮል ተጽኖ ስር መውደቅ ወይም መስከር እና የሆነ ኣልኮሆልነት ያለው መጠጥ መያዝ ወይም መጠቀም ያጠቃልላል።*

**ሕጋዊ ያልሆኑ ኣደገኛ ዕጾች መጠቀም እና ይዞ መገኘት፣ ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች እና በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱፐር ማርከት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች (ሓሽሽን በተመለከተ ሕግን Mአጣ የሚመለከት E-133 ተመልከት) ማከፋፈል ወይም መሸጥ**

*ሕጋዊ ያልሆኑ ዕጾችን ይዞ መገኘት፣ መውሰድ ወይም ወስዶ መገኘት፣ ኣደንዛዥ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች ወይም ህጋዊ ያልሆኑ ዕጾች ተቀላቅሎበት የተሰራ ምግብ፣ የዕጽ መጠቀሚያ መሳሪያ መያዝ ወይም መጠቀም እና የኤሌክትሪክ ሲጋራ ወይም ውስጡ ኣደንዛዥ ዕጾች ወይ ቁጥጥር የሚደረግባኣቸው ነገሮች የተሞላ የማጨሻ ቱቦ ወይ በእጅ የተሰራ መሳሪያ ያጠቃልላል።*

**ሓሽሽ ይዞ ወይም ሲያጨሱ መገኘት**

*ሓሽሽ ይዞ ወይም ሲያጨሱ ወይም ኣጭሶ ወይም ተጽኖ ስር ሆኖ መገኘት ለምሳሌ (በነዚህ ብቻ ግን የተወሰነ ኣይደለም) በሓኪም የታዘዘ ይሁን፣ እቤት ያበቀሉት ወይም ከመንገድ የተገዛ ሓሽሽ፣ የሆነ ሓሽሽ ያለው ምግብ እና የኤሌክትሪክ ሲጋራ ወይም ውስጡ ሓሽሽ የሞላ የኤሌትሪክ ማጨሻ ወይም የኤሌክትሪክ ተን መሳሪያ፣ ቱቦ እና በእጅ የተሰሩ ለዚህ የሚያገለግሎ ነገሮችን ያጠቃልላል።*

**ቤት ሰብሮ መዝረፍ**

*የሌላ ሰው ንብረት ብሃል ወይም ሃይል እጠቃማለሁ ብሎ በማስፈራርት መውሰድ።*

**መመሪያ መተላለፍ (ይህ ከመዋለህጻናት እስከ 5 ክፍል ያሉትን ተማሪዎችም ያጠቃልላ)**

*የተወሰነ የተጻፈ የትምህርት ቤት መመሪያ መተላለፍ። ይህ የትምህርት ቤት ኣውቶቡስ ሕግ እና የተወሰነ የደህንነት እና የስነስርዓት ሕግ መጣስ ያጠቃልላል።*

**የኣልኮል መጠጦች መሸጥ**

*የኣልኮል መጠጦች ወይም የሆነ ኣልኮሆልነት ያለው ነገር መሸጥ ወይም ለመሸጥ ማሰብ ያጠቃልላል።*

**ሕጋዊ ያልሆኑ ኣደገኛ ዕጾች፣ ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች እና በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱፐር ማርከት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች መሸጥ**

*ኣደንዛዥ ወይም ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች ለምሳሌ በሓኪም መታዘዝ የሚገባቸው መድሃኒቶች ወይም ከመድሃኒት ቤት የሚገዙ መድሃኒቶች፣ ሕጋዊ ያልሆኑ ዕጾች የተጨመሩባቸው ምግቦች መሸጥ ወይም ለመሸጥ ማሰብ እና የኤሌክትሪክ ሲጋራ ወይም ውስጡ ሕጋዊ ያልሆኑ መድሓኒቶች እና ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች የሞላ የኤሌትሪክ ማጨሻ መሳሪያ እና ሌሎችንም ያጠቃልላል።*

**ሓሽሽ (ማሪዋና) መሸጥ**

*የሆነ ዓይነት ሓሽሽ (ማሪዋና) ለመሸጥ ማሰብ የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ግን በነዚህ ብቻ ግን ያተወሰነ ለምሳሌ ለመድሃኒትነት በሓኪም የታዘዘ፣ እቤት የበቀለ፣ ከሱቅ የተገዛ ወይም ከመንገድ የተገዛ ሓሽሽ፣ የሆነ ሓሽሽ ያለው ምግብ እና የኤሌክትሪክ ሲጋራ ወይም ውስጡ ሓሽሽ የሞላ የኤሌትሪክ ማጨሻ መሳሪያ መሸጥ ወይም ለመሸጥ መሞከር ያጠቃልላል።*

**ጾታዊ ጥቃት**
*ጾታዊ ጥቃት ወይም ከሌላ ሰው ጋር የሚደረግ ስነስርዓት የሌለው ጋጠወጥ ጾታው ተግባር። (በተጨማሪ ተገቢ ያልሆነ ጾታዊ ባህሪያት፣ ተገቢ ያለሆነ መንከት፣ ባለጌ ወይም ኣጸያፊ ተግባራት፣ ጾታዊ በደል ተመልከቱ)።*

**ጾታዊ በደል**[24]
*ሌላ ሰውን ተቀባይነት ወደሌለው ጾታዊ ባህሪ ያለው ነገር መገፋፋት። እንደዚህ ያለ ጠባይ እንደ ሆን ብሎ ሌላ ሰውን ከጾታዊ ነገር ጋር በተሳሰረ መንገድ መበደል ወይም ጾታዊ በሆነ መንገድ ኣላስፈላጊ ኣተኩሮ መስጠት፣ መካት ወይም ቃላት ማስፈራራት እና ይህ ተግባር ተጠቂውን ግለሰብ ሰላም ሲነሳው፣ ሲያስፈራው ወይም ብሁኔታው ዋስትና ሳይሰማው ሲቀር የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም። (በተጨማሪ ተገቢ ያልሆነ ጾታዊ ባህሪያት፣ ተገቢ ያልሆነ መነካካት ወይም ጾታዊ ጥቃት የሚለውን ክፍል ተመለከቱ።)*

## ትንንሽ የሚታጠፉ ቢላዎች[25]

*ትንሽ የሚታጠፍ ቢላዋ ቁመቱ ከ2-1/2 ኢንች ወይም ያነሰ እና የስለቱ ስፋት ከ½-ኢንች ወይም ያነሰ ወደ ት/ቤት፣ የሆነ የት/ቤት ንብረት፣ ት/ቤት መጓጓዥ፣ የትምህርት ክልሉ የሚጠቀምባቸው ቦታዎች ወይም ተቋማት ለምሳሌ የትምህርት ክልሉ ወይም ት/ቤቱ ያዘጋጀው በዓል ወይም የትምህርት እንቅስቃሴ ይዞ መምጣት ወይም ይዞ መገኘት።*

**መስረቅ**

*የትምህርት ክልሉ ንብረት ወይም የት/ቤት ሰራተኛ፣ ተማሪ ወይም ትምህርት ቤት ሊጠይቁ የመጡ እንግዶች ንብረት መስረቅ።*

***ሁከት/ብጥብጥ እፈጥራለሁ ብሎ ማስፈራራት***

*ኣንድን ተማሪ ወይም ተማሪዎችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የኣካል፣ የቃላት፣ የጽሑፍ፣ የቴሌፎን ወይም ኤሌክትሮኒክ መንገድ ተጠቅሞ ሁከት/ብጥብጥ እፈጥራለሁ ወይም እጎዳሃለሁ ብሎ በግልጽ መናገር ወይም ኣንድ ሰው ላይ ያተኮረ ማስፈራራቶች ማሰማት፤ ይህ ማስፈራራት ሌላው ሰው ለሂወቱ፣ ጠቅላላ ደህንነቱ ወይም ንብረቱ ላይ ኣደጋ የሚጥል ወይም ሌላ ጉዳዩን የሚሰማ ሰው የሌላው ሰው ሂወት፣ ደህንነት ወይም ንብረት ኣደጋ ላይ ወድቋል ወይም ለድብድብ እና ሁከት/ብጥብጥ ተጋልጧል ብለው ካመኑ። የሚባል ያለውን ማስፈራርት ጉዳዩ የሚመለከት ሰው እንዲሰማው የግድ ኣያስፈልግም።*

*ሌላ ዓይነት መቀጮዎች ቢወሰኑበትም ለውጥ ኣያመጣም ብሎ ኣሳማኝ ምክንያት ካምነ ትምህርት ቤቱ ለመጀመሪያ ጥፋት ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የተማሪዎች የስነስርዓት መቀጮ ግምት ውስጥ ሳያስገባ ተማሪ በቀጥታ ሊያባረር ይችላል።*

*ሌላ ዓይነት ኣራሚ እርምጃዎች ኣይሰሩም ብሎ ለማመን የሚስችሉ በቂ ምክንያቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፤*

- *እገድልሃለሁ ብሎ የትምህርት ቤት ሰራተኛን ማስፈራራት። የትምህርት ቤት ሰራተኞች ይሁኑ ሌላ ሰው ማስፈራራት በሌለበት እና ደህንነቱ በተጠበቀ የትምህርት ቤት ኣከባቢ የመስራት መብት ኣላቸው። የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቤት ሰራተኞች ይሁን ሌላ ሰው በሚያስፈራሩ ተማሪዎች ላይ ትግስት የለውም። ተማሪው ከትምህርት ቤት ከማባረሩ በፊት የትምህርት ቤት መስተዳድሩ የደህንነት እና ማስፈራራት ጥናት ቡድን (Safety እና Threat Assessment Team (STAT)) ጉዳዩን እንዲያጠናው እና የሚባል ያለው ወሬ እውነት መሆኑን እና ኣለመሆኑን ሰራተኛውን ብውነት ያሰጋዋል ወይ ብለው እንዲያጠኑት ያደርጋል። ቀጥታዊ፣ ድብቅ ወይም ኣንዳንድ የመግደል ማስፈራራቶች ወይም የሆነ ዓይነት ኣደጋ በትምህርት ክልሉ ተጠንቶ ከማሃከለኛ እስከ ከፍተኛ ኣደጋ ሰራተኛው ላይ ያደርሳል ብሎ ካመነ ተማሪው ከትምህርት ቤት ጠቅላላ ይባረራል[26]።*

**የመጫወቻ ሽጉጦችና መጫወቻ የሚመስሉ መሳሪያ ዎች**

---

[24] **ከፋት ላይ የተመሰረት ማጎሳቆል ወይ ማዋከብ** የሚለውን ተመልከት።

[24] *የቦርድ ፖሊሲ ቁጥር* 3208 – ጾታዊ በደል እና የሱፐርኢተንዳንቱን መምሪያ ቁጥር 3208SP ተመለከት።

[25] **የመጫወቻ ሽጉጦችና መጫወቻ የሚመስሉ መሳሪያ ዎች** የእውነት ቢላ የሚመስሉ ግን የእውነት ያልሆኑ መጫወቻዎች በተመለከት ተመልከት።

[26] የትምህርት ቤት መስተዳድሩ የደህንነት እና ማስፈራራት ጥናት ቡድን (Safety and Threat Assessment Team (STAT)) ሙሉ ትርጉም ኣባሪ ጽሑፍ ሀ ተመልከት።

*የመጫወቻ ሽጉጥ*[27] *ወይም ሌላ መጫወቻ መሳሪያ ሲታይ የእውነት መሳሪያ የማይመስል ወይም የእውነት መሳሪያ የሚመስል ኣሻንጉሊት መሳሪያ ወይም የእውነት መሳሪያ ግን ለክፉ ዓላማ መጠቀሚያ ያልዋለ ይዞ መገኘት።*

### እንደ መሳሪያ የሚያገለግሉ መጫወቻዎች

*ኣካላዊ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ መጫወቻዎችን ኣሻንጉሊቶ መጠናቸው የሆነ ይሁን ለክፉ ኣላማ (በሚያስፈራራ መንገድ) ማለት ተብዳዩ ሊሂወቱ እስኪሰጋ ወይም ያሰጋኛል ብሎ እስኪያም መጠቀም እና መያዝ ።*

**የሌላ ሰው ንብረት ውስጥ ያለፍቃድ መግባት**

*የትምህርት ቤት ህንጻ ወይም የሆነ የትምህርት ቤት ግቢ ወይም የትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ በሆነ ምክንያት ንብረት ለመስረቅ ባይሆንም መግባት ወይም ተደብቆ መቅረት።*[28]

**የትምባሆ ውጤቶች መጠቀም ወይም መያዝ**[29]

*የህዝብ ትምህርት ቤት ንብረት፣ ኣውቶቡሶች እና ትምህርት ቤት ያዘጋጃቸው እንቅስቃሴዎች ላይ የትምባሆ ውጤቶች መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት።*

---

[27] እውነተኛ መሳሪያ ወይም መሳሪያዎች ተጥቅሞ ዓመጽ መፈጸም ወይም መሳሪያ የሚመስሉ መጫወቻዎች ለክፉ ተግባር መጠቀም ተመልከት።

[28] **ዝርፊያ** ከንብረት መስረቅ ጋር የተያያዘ የሰው ኣጥር ጥሶ መግባት።

[29] የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ቁ. 4215 እና የትምህርት ክልሉ ኣስተዳዳሪ ቅጥ ቁ. 4215SP ተመልከት።

# የወንጀል ተባባሪ ሆኖ መገኘት

የሆነ ተማሪ ሌላ ሰው መታረም የሚገባው የስነስርዓት መተላለፍ ሲፈጽም ከተባበረ ብሕግ በተባባሪነት ያስጠይቀዋል። የሆነ ተማሪ እያወቀ የወንጀል ተባባሪ ነው ተብሎ የሚታሰበው እያወቀ ከሌላ ጋር መታረም የሚገባው የስነስርዓት መተላለፍ ሲፈጽም ማለት፤ (1) በኣካል ተገኝቶ ወይም በሌለበት ወንጀል እንዲፈጸም ካበረታታ፣ ካዘዘ፣ ሌሎችን ከጠየቀ ወይም እንዲፈጽሙ ከጠየቀ (2) ወንጀሉ ማቀድ ላይ ከተባበረ ወይም ከተስማማ ወንጀለኛ ይታሰባል። ኣንድ ተማሪ ሌሎች ገበን እንዲፈጽሙ በንግግር ወይም በቃላቱ ካደፋፈረ ገበን ይታሰባል።[30]

ተማሃሪው ተገዶ የስነስርዓት መተላለፍ እምጃውን ከፈጸመ፣ ትብብሩ ተገቢ ያልሆነውን የስነስርዓት መተላለፍ እምጃውን ከመፈጸሙ በፊት ካቋረጠው ወይም ሁኔታውን ኣስቀድሞ ለትምህርት ቤት ሓላፊዎች ካሳወቀ እንደ ወንጀለኛ ኣይታሰብም።[31]

ተማሃሪው የስነስርዓት መተላለፍ እምጃ ላይ ከተሳተፈ ግን ከዋና ስነስርዓት ተላላፊ እኩም ጥፋቱ ላይ ኣንደተሳተፈ ታስቦ ከጥፋተኛው እኩል ይከሰሳል ወይም ተጠያቂ ይሆናል።

## ከትምህርት ቤት ውጪ የሚታዩ ባህሪያት

ከትምህርት ቤት ውጪ ሌላ ቦታ የሚፈጸም ጥፋት ወይም የስነስርዓት መጣስ ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ጋር የሚተሳሰር ከሆነ ሕጋዊ የስነስርዓት መቀጫ ሊያስከትል ይችላል። የተፈጸመው የስነስርዓት መጣስ ወንጀል ከትምህርት ጋር የተሳሰር ጥፋት ነው ተብሎ እንዲታሰብ የሚከተሉት ጉዳዮችንን ማካተት እና ማሟላ መሆን ኣለበት፤

(1) ጥፋቱ የተፈጸመበት ቦታ (ለትምህርት ቤት ግቢ ወይም ትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ያለው ቀረቤታ)፣
(2) ጣፍት የተፈጸመበት ግዜ እና ዕለት (በትምህርት ቤት ግዜ ከትምህርት ቤት ውጪ፣ ቀጥታ ከትምህርት ቤት በፊት ወይም ቡኃላ፣ የትምህርት ክልሉ መጓጓዣ፣ የምህርት ክልሉ መጓጓዣ ከምግባታቸው በፊት ወይም ከወረዱ ቡኋላ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ)፤
(3) ጣፍቱ ሌላ ተሳታፊዎች ወይም ተጎጂዎች ላይ ያደረሰው ጉዳት (ረብሻው ሌላ ተማሪዎች ወይም የትምህርት ክልሉ ሰራተኞችን ኣሳትፏል ወይም ጎድቷል ወይ)፤
(4) የጥፋቱ ክብደት እና ከሌላ ተማሪ ወይም የትምህርት ክልሉ ሰራተኞች ደህንነት ጋር ያለው ግንኙነት (ለምሳሌ፣ ድብድብ ወይም ሌላ ኣመጸኛ ወይም ኣፍራሽ ተግባራት፣ ሓሽሽን ወይም የተከለከለ ነገር መሸጥ ወይም መሳሪያ ይዞ መገኘት)፤
(5) ከትምህርት ቤት ውጪ የተደረገው እንቅስቃሴ መጠን እና የትምህርት ቤት ኣከባቢ ወይም ደህንነት ላይ ያደረሰው ጉዳት (ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ለመምጣት ሲፈሩ ወይም በሱ ምክንያት ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ስሲፈሩ፣ እንቅስቃሴው የትምህርት ቤት ኣከባቢን ሲረብሽ እና ጸጥታ ለማስከበር እና ተማሪዎች እና ትምህርት ቤት ስራተኞች ለመከላከል ልዩ ጥንቃቄ ወይም እርምጃ መውሰድ ሲያስፈልግ፣ ወንጀሉን ለመፈጸም ስምምነቱ ትምህርት ቤት ተካሂዶ ወንጀሉ ግን ከትምህር ቤት ውጪ ከተካሄደ፣ ለምሳሌ የእጽ መሸጥ፣ ጸብ ወይም ኣመጽ ወይም ወረራ ወዘተ… ወይም ሌላ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ወይም ተማሪዎች ያልሆኑ ወደ ትምህርት ቤት ልደባደቡ የሚመጡ ከሆነ።)

የትምህርት ክልሉ ከትምህርት ቤት ውጪ በተማሪዎች የሚደረግ ንግግር ትምህርት ቤት ውስጥ ከፍተኛ ረብሻ የሚያመጣ ወይም ሊያመጣ የሚችል ወይም ተማሪዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ ትምህርታትቸውን እንዳያገኙ የሚያደርግ ከሆነ እርምጃ ይወስዳል። *ከፍተኛ ረብሻ* ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል በነዚህ ግን የተወሰነ ኣይደለም፤ ትምህርት የሚያደናቅፍ ተግባር፣ የትምህርት ቤት ስራ ወይም ትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች፣ ተማሪዎች ማሃከል ሓይለኛ ኣካላዊ ወይም የቃላት ልውውጥ የሚያመጣ ወይም ምቹ ያልሆነ የትምህርት ኣከባቢ የተማሪዎች የትምህርት ሂደት የሚያውክ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል።

---

[30] ኣንድ ተማሪ ሌላ ተማሪ ወንጀል ሲፈጽም ከተባበረ ወይም እያየ ሳይቃወም ዝም ካለ ወይም ሊያስቆመው ካልሞከረ ወይም ዝም በማለቱ ስምምነቱ ከገለጸ ወይም ተጎጂውን ማስፈራራት ላይ ከተባበረ የወንጀል ተባባሪ ይሆናል። ለምሳሌ፤ ሌላ ተማሪ ሲያንጓጥጥ ወይም ሲያስፈራራ ተጎጂው ኣከባቢ ከኣስፈራሪዎች ጋር ከተሰበሰበ ወይም ተጎጂውን ካስፈራር ዋላ ባይናገሩም ወይም ባይመቱም እንኳን በቀላት በመስማማታቸው ወይም ኣያዩ ዝም በማለታቸው የገበን ተባባሪዎች ይታሰባሉ። ምክንያቱም እያዩ ቦታው እያሉ ታቃውሞኣቸውን ባለመግለጻቸው ተጎጂውን ማስፈራርት ወይም ማንጓጠጥ ላይ እንደተሳተፉ እና እንደተስማሙበት ይታሰባል።

[31] ተማሪዎች በሌላ ተማሪ ስለታሰባ ወንጀል እውቀት ከሌላቸው ዋላ የሰምትን ነገር ለእስተዳዳሪዎች ባይጠቁምም እንደ ወንጀል ተባባሪዎች ኣይታሰቡም።

***መደበኛ ደረጃቸውን የጠበቁ ሕጋዊ እርምጃዎች***

እነዚህ መደበኛ ደረጃቸውን የጠበቁ የተማሪዎችን ስነስርዓት እርምጃዎች የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 3240 ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የተማሪዎች የስነስርዓት መቀጮ ኣጠቃቀም የተመለከተ መረጃ ኣጠቃሏል።

## የትምህርት ኣገልግሎት የመስጠት ሓላፊነት

የትምህርት ክልሉ ተማሪውን እንደ የስነስርዓት እርምጃ (መቀጮ) የትምህርት ኣገልግሎት ሊከለክለው ኣይገባም።

ምንም እንኳን ተማሪዎች ስነስርዓት በማጉደል ምክንያት ከትምህርት ቤት በታገዱበት ወይ በተባረሩበት ወቅት ከክፍል ወይም ሌላ ከትምህርት ጋር የተሳሰር እንቅስቃሴ ወይም የትምህርት ቤት በዓል እንዲወገዱ ቢደረጉም፤ የትምህርት ክልሉ የግድ ለተማሪዎች በዚህ ግዜ የትምህርት ኣገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ኣለበት።

የሚሰጠው የትምህርት ኣገልግሎት ኣማራጭ በሆነ ሌላ ቦታ የሚሰጥ ከሆነ የትምህርት ሁኔታ ከሆነ ከመደበኛው ትምህርት ጋር በይዘቱ ተመሳሳይ፣ ርትዓዊ እና ተማሪው ከትምህርት ገበታው ሳይገለል በመደበኛ ትምህርት ቤት ማገኘት ከሚገባው ትምህርት ጋር የሚመጣጠን መሆን ኣለበት።

## ተማሪው መመለሻ ስብሰባ፣ የመመለሻ ውጥን እና እንደገና ማስገቢያ ፕሮግራም

የተማሪዎች የመመለሻ ስብሰባ ከትምህርት ቤት ለረጅም ግዜ የታገዱ ወይም ጠቅላላ ተባረው የነበሩ ተማሪዎች እንደገና በሚመለሱበት ወቅት ከሁኔታቸው ጋር የሚስማማ ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀው ተማሪውን እንደገና ወደ ትምህርት ገበታ መመለሻ ውጥን ለማዘጋጀት ነው (RCW 28A 600.022)። የተማሪዎ እንደገና መመለሻ ፕሮግራሙ ዓላማ ተማሪው ረጅም ግዜ ከትምህርት ቤት የሚያገል የስነስርዓት እርምጃ ጨርሶ ወደ ትምህርት ቤት በሚመለሱበት ወቅት ተማሪው ትምህርቱ ላይ ውጤታማ እንዲሆን ለማገዝ ነው።

የተማሪው የመመለሻ ስብሰባ የግድ የተማሪ የስነስርዓት እርምጃ ደብዳቤ (ኖቲስ ኦፍ ዲስፐሊናሪ ኣክሽን (NDA)) ቤት በተላከበት እና ለወላጆች ስለስብሰባው በተነገራቸው <u>በሶስት ቀናት (3)</u> ውስጥ መካሄድ ኣለበት።

የተማሪው መመለሻ ስብሰባ ላይ የሚሳተፉ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ኣለባቸው፤

1. ተማሪው ከትምህርት ቤት ለረጅም ግዜ እንዲታገድ ወይም እንዲባረር ያደረገ ነገር ሁኔታ፣
2. የተማሪው ያለፈ የትምህርት እና የስነስርዓት ታሪክ እና
3. ተማሪው ከትምህርት ገበታ እንዲታገድ ያደረገ ኣጋጣሚ ሁኔታ።

የተማሪው ዳግም መመለሻ እቅድ ኣላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- ቤተሰቡ ጠቃሚ የሆነ መረጃ እንዲጨምሩ ወይም ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እና ባህላዊ የሆነ ልዩ ተነኪ የሆነ ሁኔታ የሚያይ እና ባህላዊ ሁኔታዎችን ግምት ያስገባ የመመለሻ ውጥን ለማዘጋጀት፣
- ተማሪው በሚገለልበት ወቅት የሚሰጡትን ኣገልግሎቶች ላይ ለመነጋገር፣
    - o ***<u>የትምህርት ኣገልግሎት የግድ መሰጠት ኣለበት</u>***
    - o ***<u>የስነስርዓት ማሻሻያ ኣገልግሎት ላይ የግድ መነጋገር ያስፈልጋል</u>***
- ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ በፊት ማድረግ ያለበትን ነገሮች መለየት፣ እና
- ተማሪው ወደ ትምርት ቤት በሚመለስበት ወቅት ስለሚሰጡት ኣገልግሎቶች ለይቶ ማስቀመጥ።

ተማሪውን ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ እቅድ የትምህርት ክልሉ በሚያዘጋጅበት ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ኣለበት፤

1. ተማሪው የታገደበትን ወይም የተባረረበትን የግዜ ርዝመት ማሳጠር፣
2. እጅግ በጣም ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች የስነስርዓት እርምጃዎች መኖራቸው እና ኣለመኖራቸው ማጥናት፣
3. የተዘጋጀ እቅድ ኣስፈላጊውን ቅደም ተከተል ይዞ በሚተገበርበት ወቅት ተማሪው ከትምህርት ቤት እንዲታገድ ወይም እንዲባረር ያደረገው ጉዳዩ ማሻሻል ላይ እንዴት ሊያግዘው እንደሚችል ለይቶ ማስቀመጥ፣ እና
4. ተማሪውን ትምህርት ላይ ውጤታማ የሚያደርግ እና ተማሪው ስራውን ሳያቋጥ እየሰራ እንዲቆይ እና ለመመረቅ የሚያበቃው መንገድ የሚያስይዘው እቅድ ማውጣት።

የትምህርት ክልሉ ኣሰራር በተለይ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሁሌም ተማሪው ከትምህርት ቤት ለረጅም ግዜ ታግዶ ወይም ተባሮ ባለበት ወቅት በተቻለ መጠን ነጻ የጸባይ ማሻሻያ የምክር ኣገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ይህ ባጠቃላይ መታገዱ ወይ መባረሩ ያስከተለው ጉዳይ ዓመጽ ያካተተ ከሆነ ነው። የመመለሻ ፕሮግራሙ ሁሌም የመደበኛ ትምህርት ኣገልግሎት እና የትምህርት ክልሉን መመዘኛ ያሚያሟላ የጠባይ ማሻሻያ ትምህርት መከታተልን ያጠቃልላል።

**ኣካላዊ ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች**
ወደ ትምህርት ቤት መመላሻ ፕሮግራም ወይም የስነስርዓት ማሻሻያ ኣአልሎት ከመላካቸው በፊት ሁኔታውን የሚ አመም ስብሰባ መካሄድ ኣለበት።

## የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች

በ2017-2018 የትምህርት ዘመን ለተባረሩ ወይም ለታገዱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የመመለሻ ፕሮግራም በኢንተርኤጀንሲ ኣካዳሚ ኣማካይነት ይሰጣል። ወደዚህ ፕሮግራም የመግባት እድል በያመቱ እንደ በጀት ሁኔታው ይለያያል። በ2017-2018 የትምህርት ዘመን ስለ ፕሮግራሙ የሚመለከት መረጃ ካሉት ብዙ የኢንተርኤጀንሲ ኣካዳሚ የመዝገቢያ ጣቢያዎች ባንዱ ወይም ወደ ሳውዝ ሌክ ሃይስኩል በመሄድ የተቀራቸውን ሰሜስተር ወይም በመታገዳቸው ወይም መባረራቸው ምክንያት ላለፋቸው ትምህርት እገዛ ሊያገኙ ይችላሉ። የሚከታተሉት ትምህርት የጠባይ ማረሚያ ከሆነ እና በተመደበለት ግዜ ባግባቡ ካልተጠናቀቀ ወደሚቀጥለው ሰሜስተር ይተላለፋል።

የታገዱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተመደበላቸውን የጠባይ ማረሚያ ትምህርት በተመደበላቸ ግዜ ባግባቡ ጨርሰው ወደ ትምህርት ቤታቸው/ያገዳቸው ትምህርት ቤት መመለስ ይችላሉ። በደላቸው የጠባይ ማረሚያ ትምህርት ዘየጠቃልል ተማሃሮ ወደ ትምህርት ቤታቸው/ያገዳቸው ትምህርት ቤት ሰሜስተር መጨረሻ ላይ መመለስ ይችላሉ። ታግደው የቆዩ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤታቸው በሚመለሱበት ወቅት መመለሱን ውጤታማ ለማድረግ ከመመለሳቸው በፊት የመመለሻ ስብሰባ እንዲካሄድላቸው እና እንዲሳተፉ ያስፈልጋል። ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ዳግም መመለስ ውጤታማ እንዲሆን የተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ኣግባብ ስብሰባ ቀን ኣስቀድሞ ኣስይዞ የመባረር ውሳኔ ከያዘው ደብዳቤ ጋር መላክ ኣለበት።

ከትምህርት ቤት ጠቅላል የተባረሩ ተማሪዎች ወደ ነበሩበት ትምህርት ቤት እንዲመለሱ ኣይፈቀድላቸውም በተጨማሪም መጀመሪያ ሰሚስተሩ እስኪያልቅ ወደ ዳግም መመለሻው ፕሮግራም ይመራሉ። ከዚያም ወደ ሌላ መደበኛ ትምህት ቤት የምዝገባ መምሪያ በሚያዘው መሰረት መመለስ ይችላሉ። ተማሪዎቹ በተባረሩ ኣስር (10) የትምህርት ቀናት ወደ ዳግም መመለሻው ፕሮግራም መመዝገብ ኣለባቸው። መባረር የተወሰነባቸው ተማሪዎች ጥፋታቸው መመለሻ ፕሮግራም በጥሩ ሁኔታ እንዲከታተሉ የሚያዝ ከሆነ ፕሮግራሙን ከጨረሱ ቡኋላ ወደ መደበኛ ፕሮግራም የምዝገባ መምሪያው በሚያዘው መሰረት ኣሟልተው ይመደባሉ። የመባረር ግዜያቸውን ጨርሰው ሰሜስተሩ መጨረሻ ላይ ወይም መባረሩ የጠባይ ማረሚያ ትምህርት እንዲከታተሉ የሚያዝ ከሆነ የትመደበላቸውን ትምህርት ጨርሰው ወደ ሌላ መደበኛ ትምህርት ቤት ተገቢ መዝገባ እጠናቀው መመለስ ይችላሉ። ተባረው የቆዩ ተማሪዎች ወደ ሌላ ትምህርት ቤት በሚመለሱበት ወቅት መመለሱ ውጤታማ እንዲሆን ከመመለሳቸው በፊት የመመልሻ ስብሰባ መሳተፍ ይገባቸዋል። ኣዲሱ ትምህርት ቤት የመመለሻ ፕሮግራም ኣጠናቆ የሚመለስ ተማሪ ወደነሱ እንደተመደበ እንደተነገራቸው ባስቸኳይ የመመለሻ ስብሰባ ቀጠሮ ሊያስይዙ ይገባል።

## የማሃከለኛ ደረጃ ተማሪዎች

ለጠባይ ማሻሻያ ፕሮራሙ ቡቁ የሆኑ የማሃከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ለመሃከለኛ ደረጃ ተማሪዎች የጠባያ ማረሚያ እርምጃም በሚያዘው መሰረት (ስለብቁነቱ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስን 2017-2018 የትምህርት ዓመት የስነስርዓት መምሪያ (ዲስፒሊን ማትሪክስ) ተመልከቱ) ለኣጭር ዜ ሊባረሩ እና የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪው በትምህርት ክልሉ የስነስርዓት ጽሕፈት ቤት በኩል የስነስርዓት ማሪሚያ ኣአልሎት ሊጠይቅ ይችላል።

ተማሪው ታግዶ ባለበት ወቅት የስነስርዓት መሻሻል ጉዳይ ኣገልግሎት ሰፋ ያለ የጠባይ እና ማህበራዊ ግንኙነት ጥናት ተማሪዎች እና ወላጆችን፣ ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር የሚካሄድ ቃለ መጠይቅ፤ ኣስፈላጊ ከሆነ ወደ ማሕበረሰብ ድርጅቶች መምራትን፤ መረጃ የመልቀቅ ፈቃድ ማዘጋጀት (ሴኩሪንግ ኦፍ ሪሊስ ኦን ኢንፎርሜሽን (ROIs)፣ ከማህበረሰብ ኣገልግሎት ሰጪዎች ጋር መተባበርን፣ በተማሪው ጠንካራ ጎን መሰረት የተዘጋጀ የተማሪውን ወደ ትምህርት ቤት ዳግም መመለስ ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርግ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ኣግባብ ዕቅድ እና ሲመለሱ የሚያስፈልጋቸው ነገሮችን እና የተማሪው የመመለሻ ስብሰባ ቀጠሮ ማስያዝ ያጠቃልላል።

ተማሪዎች ወደ ትህርት ቤት በሚመለሱበት ወቅት የስነስርዓት መሻሻል ጉዳይ አገልግሎት ከትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ከወላጆች፣ ማህበረሰባ አገልግሎት ሰዎች እና ከተማሪው ጋር ሳምንታዊ ወይም ሁለት ሳምንታዊ የሚካሄድ ስብሰባ ያካትታል። ሰፊው የጠባይ ጥናቱ ተማሪው ቀጥታኛ የሆነ ይስችሎታ ስልጠና እንደሚያስፈልገው የሚያሳይ ከሆነ የስነስርዓት መሻሻል ጉዳይ አገልግሎቱ ለችሎታ ማሻሻያው ስልጠና ግዜ መወሰን ያጠቃልላል። የስነስርዓት መሻሻል ጉዳይ አገልግሎት ተማሪው ሙሉ በምሉ ታርሟል ያሚል መደምደሚያ እስኪደረስ ይቀጥላል።

### የኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች

የኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለረጅም ግዜ ከትምህርት እንዲታገዱ ኣይገባም። ስለህ ለኣንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የመመለሻ ፕሮግራም የለም።

ከትምህርት ቤታቸው ጠቅላላ የተባረሩ የኣንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከትምህርታቸው እንዳይተናቀፉ በፍጥነት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ለመደቡ ይገባል።

## በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የትምህርት ቦርድ የጸደቁ መመሪያዎች

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቦርድ እነዚህን መመሪያዎች ሰኔ 2017 ነው ያጸደቀው። የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ በትምህርት ክልሉ የበላይ ኣዛዥ ለህዝብ ትምህርት ቤቶች የተሰጠውን RCW 28A.600.015 ላይ የሰፈረው ሕጋዊ ኣሰራር እና መብቶች ኣክብሮ ይሰራል። በተጨማሪም WAC 392.400 *ተመልከት*። የዚህ ድንጋጌ ቅጂ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 206-252-0820 ወደ የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ደውላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ ወይም በሚቀጥለው የድሕረገጽ ኣድራሻ http://apps.leg.wa.gov/WAC/default.aspx?cite=392-400 ተመልከቱ።

## የት/ቤት መመሪያዎች

እላይ ከተጠቀሱት የትምህርት ክልሉ መመሪያዎች በተጨማሪ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት እራሱ የሚመራበት መመሪያ ኣጽድቆ ለያንዳንዱ ተማሪ ያከፋፍላል። ተማሪው እነዚህን የትምህርት ቤት ሕጎች ሲጥስ የስነስርዓት እርምጃ ይወሰድበታል።

## የተማሪዎች ሕጋዊ መብቶች ኣፈጻጸም ሂደት

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ እምነት የህግ መብት ማለት ሁሉም ተማሪዎች በህጉ መሰረት መብታቸው ተጠብቆላቸው ሁሉም በእኩል ፍትሓዊ ዳኝነት እንዲያገኙ ማድረግ ነው። ይህ ማለት በሆነ ምክንያት ስነስርዓት ያጎደለ ተማሪ ላይ የሚወሰደው የስነስርዓት እርምጃ ያለ ምንም ልዩነት ሁሉም ተገቢ መቀጮ እንዲያገኙ ማድረግ ነው። ተማሪዎች በበኩላቸው ስለ ቀረበባቸው ክስ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እና እራሳቸውን ኣዲከላከሉ እዚህ ላይ ተሞርኩሶ ደግሞ ተገቢ መቀጮ እንዲሰጣቸው ይገባል። የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ውሳኔ የሚሰጡት ጉዳዩን በሚገባ መርምረው እና ኣጥንተው ሲጨርሱ ነው። ተማሪዎች የተወሰነባቸውን የስነስርዓት ውሳኔ ስተት ነው ብለው ካመኑ ውሳኔውን የመቃወም እና ይግባኝ የማለት መብት ኣላቸው።

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች WAC 392-400 የሚገኙትን የኣሰራር መመሪያዎች ኣጽድቆ ተቀብሏቸዋል። እነዚህ መመሪያዎች በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ የተመዘገቡ ተማሪዎች በሕግ የመሰማት መብቶች ኣግባብ እና ይዘት ኣስፍሯል። በተጨማሪም፤ የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ዝቅተኛውን የይግባኝ ኣገባብ እና ጥበቃ ተቀብሎ ኣጽድቆታል። የተማሪዎች ስነስርዓት የሚመለከቱ ሌላ መመሪያዎች WAC 392-145 (ትምህርት ቤት ኣውቶቡሶች) ያጠቃልላል።

## ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ[32]

ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር እና ወኪላቸው ተማሪዎች የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የተማሪዎች ስነስርዓት ግዴታ እና መብት ላይ ስፍረው ያሉትን መመሪያዎች ጥሰው ሲገኙ ለኣጭር ግዜ የማገድ መብት ኣላቸው። ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው ተማሪውን ለእጭር ግዜ ከማገዳኣቸው በፊት የግድ የሚከተሉትን ኣጠቃላይ መመሪያዎች መከተል ኣለባቸው፣ እነዚህ ኣጠቃላይ መመሪያዎች፤

1. ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይ ወኪላቸው ተማሪው ከትምህርት ቤት እንዲታገድ ለመወሰን የተፈጠረውን ሁኔታ የሚያሻሽሉ ወይም የሚያባብሱ ሁኔታዎች በትክክል ማጥናት ኣለባቸው። ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው

32 WAC 392-400-245

ተማሪው ላይ የአጭር ግዜ ከትምህርት ቤት ለተወሰነ ቃናት መታገድ ከመወሰናቸው በፊት ውሳኔው ተማሪውን እና ትምህርት ቤቱን ብዙ ይጠቕመዋል ብለ ማመን እና ክፍል ውስጥ እና ትምህርት ቤት የሚሰጥ ቅጣት ኣልሰራም ብለው ማመን ኣለባቸው።

2. ርእሰመምህር እና ምክትል ርእሰመምህር ከመዋለህጻናት ኣስከ 4ተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ከኣስር ተከታታይ ቀናት በላይ ወይም በድምር ከኣስር የትምህርት ቀናት ወይም በኣንድ ሰሜስተር ወይም ትሪሚስተር እንደየ ትምህርት ቤቱ ሁኔታ ለኣጭር ግዜ መባረር ሊወስኑ ኣይችሉም።
3. ርእሰመምህር እና ምክትል ርእሰመምህር ከኣምስተኛ ክፍል በላይ ያሉ ተማሪዎችን ከኣስራ ኣምስት ተከታታይ ቀናት (15) ወይም ኣሰራምስት የትምህርት ቀናት በድምር በኣንድ ሰሜስተር ወይም ኣስር ተከታታይ (10) ወይም ኣስር የትምህርት ቀናት በድምር በኣንድ ትሪሚስተር እንደየ ትምህርት ቤቱ በላይ ተማሪውን ለኣጭር ግዜ ሊያባርሩ ኣይችሉም።
4. የሆነ ተማሪ የኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት የታኣገደ ምክንያት ያለፈው የቤት ስራ እና ፈተና የሚከተሉትን ሁኔታ ካሟላ ደግሞ እንዲወስድ ይፈቀድለታል፤ ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት በመታገዱ ምክንያት ውጤት ወይም ደረጃ ማጣት የለበትም።
5. የሆነ ተማሪ ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት የታገደ የተወሰደበት የስነስርዓት እርምጃ እንዲቃለልለት በተጨማሪም ወደ ትምህርት ቤት ወዲያው እንዲመለስ መጠየቅ[33] ይችላል። ይህን ጥያቂ ለርእሰመምህሩ በጽሑፍ ወይም በቃላት ማቅረብ ይችላል። ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ ወይም ተቃውሞ ይታሰባል።
6. **ሽምግልና**: የስነስርዓት ውሳኔው በእርቅ እንደፈታት ከተስማሙ ተማሪው ወይም ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ የተጣሰውን ሕግ የሚመለከት የቀረበ ጭብጥ እና የሕግ መርትዖ ላይ ተመስርቶ የተወሰነው የሽምግልና ስምምነት ላይ ተስማምተው ከፈረሙ ስምምነቱ የመጨረሻ እና ጉዳዩ እንደተፈታ ይወሰዳል። ከዚህ ቡኋላ ወላጆች/መጉዚቶች ጉዳዩን በተመለከት ይግባይ ላለማለት ይስማማሉ። ሁለቱ ወገኖች በእርቅ ካልተስማሙ ግን ጉዳይ የሚመለከት ስብሰባ ይቀጥላል፤ የትምህርት ቤት መስተዳድር ውሳኔዎችን ይወስናል።
7. የተማሪው ወላጅ ወይም ተማሪው እርምጃውን ይግባኝ ይበሉ ኣይበሉ የኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ እርምጃው ወዲያው ተግባራዊ ይሆናል።

## ለተማሪ እና ለወላጆች/ሞግዚቶች የኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ውሳኔ ማሳወቅ[34]

ተማሪ ለኣጭር ግዜ ከመታገዱ በፊት ወይም ቡኋላ ስብሰባ እንዲካሄድለት ሙብት ኣለው። በስብሰባው ግዜ ተማሪ የግድ በጽሑፍ ወይም በቃል የሚከተሉት ሊሰጡት ይገባል፤

1. ስለተጣሰው ሕግ ዝርዝር መግለጫ ወይም የተጣሱት የትምህርት ቤት ስነስርዓቶች እና መመሪያዎች ዝርዝር፤
2. ክሱ የሚደግፉ የተለያዩ መረጃዎች ጭማቂ ጽሑፍ፤
3. ስለሚወሰደው የስነስርዓት እርምጃ መግለጫ እና

ተማሪው ኣስተያየቱ እንዲገልጽ እድል መስጠት።ለኣጭር ግዜ መባረር የተወሰነበት ተማሪ ክውሳኔ በፊት የተሰጠውን ስብሰባ ላይ የመሳተፍ ሙብት ብተለያየ ምክንያት ሳይጠቀምበት ከቀረ ለኣጭር ግዜ መባረር ውሳኔ በሌለበት ሊወሰንበት ይችላል።

***ወላጅ/ሞግዚት*** ስለተመደበው የስነስርዓት እርምጃ የቃል እና የጽሑፍ መረጃ በሃያ ኣራት (24) ሰዓት ውስጥ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲሰጣቸው የመጠየቅ ሙብት ኣላቸው። ለወላጆች የሚሰጠው የጽሑፍ መረጃ፡ የስነስርዓት እርምጃ ውሳኔ (*Notice of Disciplinary Action* (NDA)) ተብሎ ይጠራል። የNDA የተለያየ ቋንቋ ትርጉም ኣለ። ይህ NDA የሚከተሉትን ማጠቃለል ኣለበት፤

1. የኣጭር ግዜ መታገድ ምክንያት እና የመታገዱ የግዜ እርዝመት።
2. ከኣጭር ግዜ መታገድ ጋር የተሳሰሩ ሁኔታዎች፣ የተወሰኑ መሟላት ያለባቸው እንዳንድ ነገሮች (ለምሳሌ፣ ወላጅ/ሞግዚት ስብሰባ፣ ዕጽ/ኣልኮሆል ምርመራ ወይም የጠባይ ማሻሻያ እርምጃ ወዘተ...።)
3. የይብባኝ ሙብቶቻተው እና የይግባኝ ሂደት።

የስነስርዓት እርምጃው በተወሰደ ሃያ ኣራት (24) ሰዓይ ውስጥ ሁሉም የኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ውሳኔዎች እና የመታገድ ምክንያቶች የግድ ፓወር ስኩል ውስጥ መስፈር እና በስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት መታየት መቻል ኣለበት።

## የይግባኝ ሂደት: ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም ሌላ ስነስርዓት እርምጃዎች[35]

ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ውሳኔን ይግባኝ ማለት "ቅሬታ" ይባላል። የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች WAC 392-400-240 ውስጥ የሚገኘውን የይግባኝ ሂደት ኣጽድቆ ተግባር ላይ ኣውሎታል። ይህ የይግባኝ ሂደት ይግባኝ ባይ ወገንን ትምህርት ቤት ውስጥ የተወሰደ ስነስርዓት እርምጃ ወይም ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ውሳኔዎችን ላይ ቅሬታውን እንዲያቀርብ እድል ይሰጣል።

---

[33] የስነስርዓት መጓደል ዕርቅ በተመለከተ ኣባሪ ጽሑፍ ሐ ተመልከቱ።

[34] WAC 392-400-250

[35] WAC 392-400-240

ቅሬታ በሚሰማበት ግዜ ይግባኝ ባይ ወገን ርእሰ መምህሩ የስነስርዓት መቀጮውን ስህተት እና ትክክል ያልሆነ እንደሆነ እና እንዲቀይር መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ልጅ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ፍትሓዊ ኣይደለም የተወሰደው ውሳኔ ላይ ስህተት ኣለ ስለዚ መቀየር ኣለበት ብለው ቅሬታቸውን ማሰማት ይችላሉ።

ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ውሳኔው በቀጥታ ይተገበራል። ይህ ውሳኔ ርእሰ መምህሩ የወላጆች ቅሬታ እስኪሰማ ድረስ እንዲቆይ እስካልወሰነ ድረስ ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገዱ በቀጥታ ተግባራዊ ይሆናል።

ይህ የይግባኝ ሂደቱ በትምህርት ቤት ስራተኞች ለሚፈጸም ጥፋት ላይ ቅሬታ ለመስማት ታስቦ የተዘጋጀ ኣይደለም። ወላጅ/ሞግዚት ልጁ ላይ የተወሰደው የስነስርዓት እርምጃ ተገቢ ነው ብሎ ተስማምቶ ግን ኣስተዳዳሪዎች ጉዳዩን የያዙበት ኣካሄድ ተገቢ ኣልነበርም ብለው ካመኑ ቅሬታቸውን ለትምህርት የበላይ ዳይሬክተር ማነጋገር ይችላሉ።

የሆነ ተማሪ፣ ወላጅ ወይም ሞግዚት ተማሪ ላይ የተወሰደውን ስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። እዚ ደርጃ ላይ ማለት ቅሬታ ደረጃ ላይ ይግባኝ በሶስተ የተለያዩ ደረጃዎች ሊካሄድ ይችላል፣

1. ስነስርዓት እርምጃውን ይግባኝ የሚሉ ወላጆች እና/ወይም ሞግዚት/ኣሳዳጊዎች ውሳኔውን **ከሰሙበት እስከ ሶስት (3) የስራ ቀናት** ውስጥ ከርእሰመምህሩን ወይም ወኪሉን ጋር የቅሬታ መስማት ስብሰባ እንዲደረግላቸው መጥራት መብት ኣላቸው። ውሳኔውን የወሰነ የትምህርት ቤት ባለስልጣን ውሳኔ ይግባኝ እንደተባለ መነገር ኣለበት።

   ስብሰባው በሚካሄድበት ወቅት ርእሰመምህሩ ወይም ወኪሉ ይግባኝ ባዩን መጠየቅ እና ይግባኝ ባዩ ደግሞ ለስነስርዓት ውሳኔ ያደረሰው ፍጻሚ ላይ የተሳተፉትን የትምህርት ቤት ስራተኞች የመጠየቅ መብት ኣለው። ርእሰመምህሩ ወይም ወኪሉ የስነስርዓት ውሳኔው መጽደቅ ወይም መሻር እንዳለበት ይወስናል።

2. ስነስርዓት እርምጃውን ይግባኝ የሚለው ሰው በእንደኛ ደረጃ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ካልረካበት፤ *የጽሑፍ እና/ወይም የቃል ቅሬታ*[36] ለሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የስነስርዓት ይግባኝ ጽ/ቤት ማቅረብ ይችላል። ይህ ቅሬታ የኣንደኛ ደረጃ ይግባኝ ቅሬታ ውሳኔ ከደረሳቸው የግድ እስከ ***ሶስት (3) የት/ቤት የስራ ቀን*** መድረስ ኣለበት። የኣንደኛ ደረጃ ይግባኝ እንዲሰማ የተመደበ ይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን በስነስርዓት ይግባኝ ጽ/ቤት ጉዳዩን እንዲሰማ ይመደባል። ይግባኝ ሰሚው ባለስልጣን የምርመራውን ውጤት በኣምስት (5) የትምህርት እና የስራ ቀናት ውስጥ ውጤቱን ያሳውቃል።

3. ስነስርዓት እርምጃውን ይግባኝ የሚለው ሰው በሁለተኛ ደረጃ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ካልረካበት፤ *የጽሑፍ ቅሬታ*[37] የስነስርዓት ይግባኝ ምክር ቤት ማቅረብ ይግባኙ እንዲሰማ መጠየቅ ይችላል። ይህ ቅሬታ ሁለተኛ ደረጃ ይግባኝ ቅሬታ ውሳኔ ከደረሳቸው የግድ እስከ ***ሶስት (3) የት/ቤት የስራ ቀን*** መድረስ ኣለበት። የጽሑፍ ጥያቄው ለተማሪዎች ስነስርዓት ይግባኝ ጽ/ቤት በሚከተለው ኣድራሻ Mail Stop 31-177፣ PO Box 34165፣ Seattle፣ WA 98124-1165 መድረስ ኣለበት።

የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት ይግባኙን የጽሑፍ ጥያቄው በደረሰው *ኣሰር የት/ቤት የስራ ቀናት* ውስጥ የይግባኝ መስማት ቀጠሮ ይስይዛል። ይግባኙ ከተሰማ ቡኋላ የስነስርኣት ይግባኝ ሰሚ ካውንስሉ (DAC) ውሳኔውን ይሰጣል ቀጥሎም ለይግባኝ ባዩ ውሳኔውን *ኣሰር የት/ቤት የስራ ቀናት* ውስጥ በጽሑፍ ብፖስታ ልኮ ውሳኔውን ያሳውቃል።

ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ የተወሰነበት ተማሪ የግድ መቀጮውን ወዲያው መጀመር ኣለበት። ከትምህርት ቤት ማግለል ወይም መታገድ እርምጃ ርእሰመምህሩ ካልቀየረው ወይም ካላሻሻለው በስተቀር ተማሪው ወይም ወላጆቹ/ኣሳዳጊዎቹ ይግባኝ ቢሉም መቀጮው ይቀጥላል። ርእሰመምህሩ ለኣጭር ግዜ ማታገዱ እንዲቀጥል ወይም እንዲቋረጥ የማድረግ ኣለበት። ይህ የርእሰ መምህሩ ፍቃድ እና ይግባኝ ባይ ወገን ይህን ውሳኔ ይብባኝ ሊለው ኣይችልም። በተጨማሪ ርእሰመምህሩ ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ ውሳኔ ኣላሻሸልም ቢልም ምክንያት እንዲሰጥ ኣይገደድም[38]።

---

[36] የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የጽሑፍ ወይም የቃል ለሁለተኛ ደረጃ ይግባኝ (ቅሬታ) ይቀበላል።
[37] የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ካውንስል የጽሑፍ ወይም የቃል ለሁለተኛ ደረጃ ይግባን (ቅሬታ) ይቀበላል።
[38] WAC 392-400-255.

# ለረጅም ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ ከትምህርት ቤት መባረር[39]

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የተማሪዎች ጠባይ እና የተማሪዎች መብቶች እና ሓላፊነቶች የሚለው ደኩሜንት ላይ የሰፈሩትን የስነምግባር መመሪያዎች ሲተላለፍ ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይ ወኪላቸው ተማሪው ላይ ለረጅም ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር ሊወስኑበት ይችላሉ። ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር እና ወኪላቸው ለረጅም ግዜ መተገድ ወይም ጠቅላላ ማባረር ተማሪው ላይ ከመወሰናቸው በፊት የግድ እታች የተዘረዘሩትን ኣንዳንድ መመሪያዎች መከተል ኣለባቸው፤

1. ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር እና ወኪላቸው ተማሪውን ለረጅም ግዜ ማገድ ወይም መባረር ውሳኔ ጉዳዩን የሚከላከሉ እና ሊያባብሱ የሚችሉትን ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ኣለባብቸው። ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው ተማሪው ላይ ለረጅም ግዜ ማገድ ወይም መባረር ውሳኔ ከመወሰናቸው በፊት ውሳኔው ተማሪውን እና ትምህርት ቤቱን ብዙ ይጠቕመዋል ብለ ማመን እና ክፍል ውስጥ እና ትምህርት ቤት የሚሰጥ ቅጣት ኣልሰራም ብለው ማመን ኣለባቸው።
2. ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር እና ወኪላቸው ጉዳዩን ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የተማሪዎች የስነስርዓት መቀጮ ሲያርሙት ካልቆዩ በስተቀ የረጅም ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ ማባረር መውሰድ ኣይችሉም።
3. ሽምግልና: የስነስርዓት ውሳኔው በእርቅ እንደፈታት ከተስማሙ ተማሪው ወይም ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ የተጣሰውን ሕግ የሚመለከት የቀረበ ጭብጥ እና የሕግ መርትዖ ላይ ተመስርቶ የተወሰነው የሽምግልና ስምምነት[40] ላይ ተስማምተው ከፈረሙ ስምምነቱ የመጨረሻ እና ጉዳዩ እንደተፈታ ይወሰዳል። ከዚህ ቡኋላ ወላጆች/መጉዚቶች ጉዳዩን በተመለከት ይግባይ ላለማለት ይስማማሉ። ሁለቱ ወገኞች በእርቅ ካልተስማሙ ግን የረጅም ግዜ መባረሩ ጉዳይ እንደሚቀጥለው ይቀጥላል።
4. ለረጅም ግዜ ከትምህርት ቤት መባረር ወይም ጠቅላላ መባረር የሚጀምረው ጥፋቱ በተፈጸም በኣራተኛው የትምህርት ቀን ነው። ይህ የሆነበት ዋና ምክንያት ወላጆች ወይም ኣሳዳጊዎች የተወሰነውን የስነስርዓት እርምጃ በደንብ እንዲያዩት እና ይግባኝ የማለት ከፈለጉ በቂ ግዜ ለመስጠት ታስቦ ነው። ተማሪው ይግባኙ በመስማት ላይ እያለ የመጨረሻ ውሳኔ ኣስኪሰጥ ድረስ ትምህርቱን መከታተል ይችላል።
5. ባስቸኳ የኣደጋ ግዜ መባረር ጥፋቱ ከተፈጸመበት ቀን ወዲያው ይጀምራል እስከ (10) ኣስር የትምህርት ቀናት ሊሆን ይችላል። ባስቸኳ የኣደጋ ግዜ መባረር የሚወሰነው ጥፋት ያጠፋው ተማሪው ትምህርት ቤት መገኘት ለሌሎች ተማሪዎች ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለኣደጋ የሚያጋልጥ ሲሆን ብቻ ነው[41]።
6. የረጅም ግዜ መባረር ላልተወሰነ ግዜ ከኣስራ ኣንድ (11) ቀናት እስከ ዘጠና ቀናት (90) የኣንድ ተርም (ሰሜስተር) ርዝምመት ሊሆን ይችላል። ተማሪው ቅጣቱን ጨርሶ ወደ ለረጅም ግዜ ወዳ ባረረው ትምህርት ቤት መመለስ ይችላል።

---

7. ከኣንድ ትምህርት ቤት ጠቅላላ መባረር የተወሰነበት ተማሪ ወደዚያ ትምህርት ቤት ላይመልስ ይችላል። ይህም ሆኖ ግን በሲያትል ስኩልስ ድስትሪት ከትምህርት ቤት ጠቅላላ ለተባረሩ ተማሪዎች ሌላ ኣማራጭ ትምህርት ፕሮግራሞች እንደ ወደ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ዳግም መመለሻ ፕሮግራሞች እንደ በኢንተራኤጀንሲ ኣካዳሚ የሚሰጡ ኣሉ። የጦር መሳሪያ (ጠብመንጃ)[42] ይዞ በመገኘት ጠቅላላ ከትምህርት ክልሉ ከተባረሩ ተማሪዎች በስተቀር፤ የሆነ ጠቅላላ የተባረረ ተማሪ የሆነ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ፕሮግራም ላይ ሳይመደብ መቆየት የሚችለው ቢበዛ ኣስር የትምህርት ቀናት (10) ብቻ ነው[43]።
8. የሚወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ ያለምንም ኣድልዎ እና በእኩል እንዲፈጸም የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ተማሪው ለረጅም ግዜ ወይም ጠቅላላ በሚባረርበት የሚወስነው ኣካል ለያንዳንዱ ጥፋት የሚገባ የስነስርዓት እርማጃ ያዘለ የስነስርዓት እርምጃ ኣፈጻጸም መምሪያ ኣሳትሟል።

---

9. የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቦርድ መመሪያ ተማሪው ከትምህርት ስለቀረ ብቻ እንዳይታገድ ወይም ጠቅላላ እዳይባረር ይዛል።
10. ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር እና ወኪላቸው ከቕድመ መዋለህጻናት እስከ ኣራተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ለረጅም ግዜ መባረር ኣይፈቅድም፤ ሆኖም ግን ከመዋለህጻናት እስከ ኣራተኛ ክፍል ያኣሉ ተማሪዎችን ለጭር ግዜ ሊያግዷቸው ይችላሉ።

---

[39] WAC 392-400-260.

[40] የስነስርዓት መጓደል ዕርቅ በተመለከተ ኣባሪ ጽሑፍ ሐ ተመልከቱ።

[41] የረጅም ግዜ መታገድ ከኣደጋ ግዜ መታገድ ጋር ተያይዞ ሊወሰን ይችላል።

[42] የሱፐርኢንተንደንቱ ኣስራር ቅጥ ቁጥር 3248SP ተመልከት።

[43] WAC 392-400-275።

11. ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር እና ወኪላቸው ከአምስተኛ ክፍል በላይ ያሉ ተማሪዎችን ለረጅም ግዜ ሊያባርሯቸው ወይም ሊያግዷቸው ይችላሉ፤ ሆኖም ግን እነዚህ ተማሪዎች ለስነስርዓት መቀጮ ውሳኔው ርዝመት የትምህርት ኣገልግሎት የማግኘት መብት ኣላቸው።
12. ተማሪዎች እና ወላጆች ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ዕቅድ ላይ ስለ ትምህርት የመቀጠል መብት እና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መመለሻ ፕሮግራም በኢንትራ ኤጀንሲ በኩልስ የሚሰጥ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ መረጃ ሊሰጣቸው ይገባል።
13. ተማሪዎች ኣንቀጽ RCW 28A.600.022 በሚሰጠው መብት መሰረት ከተባረረ 20 ቀናት ውስጥ ሊያዝ/ሊመደብ የሚገባው የመመለሻ ስብሰባ የመሳተፍ መብት ኣለው። የተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ዳግም መመለስ ውጤታማ እንዲሆን **የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ** ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ስብሰባ የስነስርዓት እርምጃ ውሳኔ (Notice of Disciplinary Action (NDA)) በሚዘጋጅበት እና ለወላጆች በሚላክበት ግዜ በመጀመሪያዎቹ ሶስት (3) ቀናት ውስጥ እንዲካሄድ ይጠይቃል። ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ስብሰባ ቀን ቀጥሮ ከተያዘ ቡኋላ ደብዳቤው ወደቤት ይላካል። ስለ ስብሰባ ቀን ማሳሰቢያ የመባረር ውሳኔ ከያዘው ደብዳቤ ጋር ይላካል።

---

**ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የተማሪዎች የስነስርዓት መቀጮ መመሪያ የማይመለከታቸው**

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ለመጀመሪያ ጥፋት ጉዳዩን ሊያባብሱት የሚችሉ እና ይህን ውሳኔ እንዲወሰን የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የተማሪዎች የስነስርዓት መቀጮ ግምት ውስጥ ሳያስገባ ተማሪ በቀጥታ ሊያባረር ይችላል።

### ለወላጆች/ሞግዚቶች ለረጅም ግዜ መታገድ ወይም መባረር በሚመለከት ማሳወቅ[44]

ተማሪው ለረጅም ግዜ ከመባረሩ ወይም ጠቅላላ ከመባረሩ በፊት ተማሪው እና ወላጁ/ሞግዚቱ የግድ ስለተወሰነው የስነስርዓት እርምጃ ውሳኔ (NDA) በጽሑፍ መሰጠት እና ተጨማሪ ለረጅም ግዜ መባረሩን ወይም ጠቅላላኣ መባረሩን ይብባኝ ስለ ማለት መብት መረጃ እና የመሰማት መብታቸው የሚመለከት መረጃ መሰጠት ይገባቸውል። ይህ የጽሑፍ ውሳኔ በኣካል ወይም በተመዘገበ ፖስት ሊሰጣቸው ይገባል።

1. ለወላጅ/ሞግዚት እና ተማሪው የሚላከው መልእክት በተቻለ መጠን በሚናገሩት እና በሚገባቸው ቋንቋችሁ ሊሆን ይገባል፤
2. የጽሑፍ ወይም የቃል ውሳኔው ስለተፈጸመው ወንጀል መግለጫ እና ስለተጣሰው የትምህርት ክልሉ ደንብ የሚገልጽ መረጃ መያዝ ኣለበት፤
3. የጽሑፍ ውሳኔው ሊወሰድ ሚታሰበው የስነስርዓት እርምጃ ምን እንደሆነ ማስፈር ኣለበት፤
4. የጽሑፍ ውሳኔው የተማሪው እና/ወይም የወላጆች/ሞግዚቶች የይግባኝ መብቶች መግለጫ እና እንዴት ይግባኝ ሊሉ እንደሚችሉ መግለጽ ኣለበት፤ እና
5. የጽሑፍ ወይም የቃል ውሳኔው ክሱን እንዴት ይግባኝ ማለት እንደሚችሉ መግለጽ ወይም ጉዳዩ እንዲሰማ ለመጠየቅ ያለውን ይግዜ ገደብ መረጃ መስጠት ኣለባት።

ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው ከትምህርት ቤት ለረጅም ግዜ ከመታገድ ወይም ጠቅላላ ማባረር ቡኋላ እንዳንድ ውሳኔዎችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። የመጀመሪያው ውሳኔ ከትምህርት ቤት ለኣጭር ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረሩን ይግባኝ ማለት እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው ነው። ይህ በተቻለ ፍጥነት ቶሎ መወሰን ኣለበት ምክንያቱም ለረጅም ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ ማባረር ውሳኔ ለወላጆች/ሞግዚቶች ከደረሳቸው ቡኋላ ይግባኝ ለማለት ያላቸው ግዜ ሶስት የስራ ቀናት ብቻ ስለሆኑ።

ይግባኝ ላለማለት የወሰኑ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ወላጆች/ኣሳዳጊዎች የኢንተር ኤጀንሲ ኣካዳሚ[45] እና ተማሪው የሚስማማው የትምህርት ዓይነት የሚያገኝበትን መንገድ ሊያፈላልጉ ይገባል። በጠቃላይ ሁሉም ተማሪዎች ኣራሚ የስነስርዓት እርምጃ በተወሰደባቸው ወቅት የትምህርት ኣገልግሎት የማግኘት መብት ኣላቸው።

ጠቅላላ የትባረሩ ተማሪዎች ሌላ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ዓይነት እንዴት እንደሚያገኙ የምዝገባ ማእከሉን (ኢንሮልመንት ኦፊስ) በፍጥነት ማነጋገር ይገባቸዋል። ምክንያቱም ወደ ነበሩበት ትምህርት ቤት ርእሰመምህሩ ኣንዲመልሳቸው ፔቲሽን ካላቀረቡ በስተቀር መመለስ ስለማይችሉ።

ለረጅም ግዜ የታገደ ተማሪ የቅጣት ግዜውን ጨርሶ ከቅጣቱ ጋር ጠባዩ ለማሻሻል የተወሰነበትን የጠባይ ማረሚያ ፕሮግራም እንዳጠናቀቀ የሚጠቁም ማረጋገጫ ሲያቀርብ ወደ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራሙ ወይም ወደ የማባረር ውሳኔውን ወደወሰነው የነበረበት ትምህርት

---

[44] WAC 392-400-265 and WAC 392-400-270።

[45] የኢንተር ኤጀንሲ ስልክ ቁጥር 206 743 3930 ነው።

ቤት መመለስ ይችላል። ከትምህርት ቤት ጠቅላላ የተባረረ ተማሪ ምናልባት አስቀድሞ ይማርበት ወደ ነበረው ትምህርት ቤት ርእሰመምህር ፔቲሽን አቅርቦ ተቀባይነት ካገኘ መመለስ ይችላል።

## ልዩ መመሪያ ጠቅላላ መባረርን ተከትሎ ተማሪውን ወደ ነበረበት ትምህርት ቤት እንደገና ስለ መመለስ

ሁሌም ከትምህርት ቤት ጠቅላላ የተባረረ ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሶ መምጣት ኣይፈቀድለትም። ሆኖም ግን ወላጆች/ኣሳዳጊዎች እና ተማሪዎች ተማሪው ወደ ነበረበት ትምህርት ቤት እንዲመለስ ፔቲሽን ማቅረብ ይችላሉ። የጽሑፍ ፔቲሹ የግድ የትምህርት ቤቱን ርእሰመምህ የሚማጸን ሆኖ ወደ ትምህርት ቤቱ መላክ ኣለበት። ተማሪ ወይም ወላጅ/ሞግዚት ተማሪው ለምን ወደነበረበት ትምህርት ቤት መመለስ እንዳለብት ምክንያቶቻቸውን የግድ ብግልጽ ማስቀመጥ ኣለባቸው። ጠቅላላ የተባረረው ተማሪው እንደገና ወደ ነበረበት ትምህርት ቤት መመለስ እንዳለበት እና እንደሌለበት የሚወስነው የትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር ነው። የርእሰመምህሩን ውሳኔ ይግባኝ ማለት ኣይቻልም።

## ለረጅም ግዜ መታገድን ወይም ጠቅላላ መባረር የሚመለከት የይግባኝ ኣግባብ

የሆነ ተማሪ ለረጅም ግዜ መታገድን ወይም ጠቅላላ መባረር ሲወሰንበት የተማሪው ወላጅ/ሞግዚት ወይም ተማሪው ይህን ለረጅም ግዜ መባረር ወይም መባረር ወደ ትምህርት ክልሉ ጠቅላይ ኣዛዥ ይግባኝ ማለት ይችላል። የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጽ/ቤት ውስጥ ጠቅላይ ኣዛዡ የመደቡት የይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ወኪል ጉዳዩ ይሰማል። የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣናት የስቴት ሕግ እና የትምህርት ክልሉ መመሪያዎች ስልጠና የተሰጣቸው እና ስለ ይግባኝ ኣፋጻጸም መመሪያዎች እውቀት ያላቸው የማህበረሰቡ ኣባላት ናቸው። የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣናት ተማሪው ላይ የተወሰኑትን የስነስርዓት ኣርምጃዎች ኣስመልክቶ ማስታረቅ፣ ማሻሻል፣ የመሻር ወይም መጽደቕ መብት ኣላቸው። የይግባኝ ኣካሄድ የሚከተሉትን መንገዶች ተከትሎ ይካሄዳል፤

### A. የይግባኝ ሂደት የግዜ ገደብ

1. ይግባኝ ባይ ወገን ከትምህርት ቤቱ ኣራሚ እርምጃው ወይም የስነስርዓት ውሳኔው በደረሳችሁ በሶስት (3) የት/ቤት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ይግባኙ ማስገባት እና ጉዳያቸው እዲታይ መጠየቅ ኣለባቸው። ይግባኙ ለይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት በጽሑፍ ወይም በቃል በቴሌፎንም ቢሆን ማቅረብ ኣለባቸው። የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት የቴሌፎን ቁጥር 206-252-0820 ነው።
2. የይግባኝ ጥያቄያችሁ ከትምህርት ቤቱ የስነስርዓት እርምጃው ወይም የስነስርዓት እርምጃ ሃሳብ ውሳኔው በደረሳችሁ በሶስት (3) የት/ቤት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ይግባኝ ካላችሁ፤ ትምህርት ቤቱ የወሰነው ለረጅም ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር ተግባራዊ ይሆናል በተጨማሪም ወላጅ/ሞግዚት ወይም ተማሪው ይግባኝ የማለት መብት ከዚህ ግዜ ቡኋላ የለውም።
3. የይግባኝ ክሱ በተወሰነው ሶስት (3) ቀናት የግዜ ገደብ ውስጥ ከደረሰው የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት የይግባኝ ክሱ ከተቀበለበት ቀጥለው ባሉት ሶስት (3) የትምህርት ቀናት ውስጥ የይግባኝ መስማት ቀጥሮ ያስይዛል።

### B. ወላጅ/ሞግዚት እና የተማሪዎች መብት

ወላጆች/ሞግዚቶች እና ተማሪዎች ይግባኖቻቸው ከመሰማቱ በፊት፣ በሚሰማበት ግዜ እና ከተሰማ ቡኋላ የተለያዩ መብቶች ኣሏቸው። እነዚህ መብቶች በስቴታችን የህግ ባለሙያዎች የጸደቁ እና WAC 392-400 በሚለው ኣንቀጽ ስር የሚገኙ ናቸው። እነዚህ መብቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፣ በነዚህ ብቻ ግን የተወሰኑ ኣይደሉም፤

1. ይግባኝ ባይ ወገን ትምህርት ቤቱ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የሚያቀርባቸውን የሆኑ የጽሑፍ ወይም ሌላ ጭብጦች እንደ የምስክሮች ቃል ያመሰሉ ጉዳዩ ከመሰማቱ በፊት የመመርመር መብት ኣለው። ሚስጢር ለመጠበቕ የተማሪ ስሞች ይሰረዛል (የሚቀርበው ወረቀት ላይ ኣይሰፍሩም)።
2. ይግባኝ ባይ ወገን በመንግስት ሳይሆን በራሱ ወጪ ጠበቃ ይዞ የመቅረብ መብት ኣለው። ይግባኝ ባይ ወገን ጠበቃ ይዞ የሚቀርብ ከሆነ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጠበቃውን ይዞ ይቀርባል። ስለዚህ የስነስርዓት ስሚ ጽ/ቤት ተማሪው ጠበቃ ይዞ የሚቀርብ ከሆነ የግድ ኣስቀድሞ መነገር ኣለበት።
3. ይግባኝ ባይ ወገን ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ምስክሮች መጠየቅ መብት ኣለው። ይህ መብት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መስክሮችን ኣፈላልጎ ያገኛቸው ከሆኑ ወይም ምስክሮች ካላገኘ ወይም ተማሪውን (ምስክሩን) ማቅረብ ለድህንነቱ ያሰጋል ወይም በቀል ሊያጋጥመው ይችላል ብሎ ካመነ የተወሰነ ይሆናል።
4. ይግባኝ ባይ ወገን ስለተፈጠረው የስነስርዓት መጉዳል የራሳቸው ማብራሪያ እና መግለጫ የማቅረብ መብት ኣለው።
5. ይግባኝ ባይ ወገን ይግባኝ ስለተባለው ጉዳይ ዕውቀት ኣላቸው የሚባሉ ወይም ፍጻሜውን ያዩ ምስክሮች ሌሎች ተማሪዎችን ጨምሮ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የምስክር ቃል መስጠት እንዲፈቀድላቸው መጠየቅ ይችላል፤ እና
6. ይግባኝ ባይ ወገን ጉዳዩን የሚደግፍ የሆነ የጽሑፍ ወይም ሌላ ጭብጥ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ማቅረብ ይችላል።

## C. ጉዳዩ ከመሰማቱ በፊት ያሉ የትምህርት ቤቱ መብቶች

የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ወይም ሌላ የትምህርት ቤቱን ጉዳይ የሚያቀርብ ሰው ጉዳዩ መሰማት ከመጀመሩ በፊት ወላጆች/አሳዳጊዎች ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ የሚያቀርቡትን የሆነ የጽሑፍ ወይም ሌላ ጭብጥ የመስማት ወይም ማየት መብት አለው። ተማሪው እና ወላጎቹ/አሳዳጊዎቹ ለይግባኝ ሰሚው ባለስልጣን ለማቅረብ ያዘጋጁትን የሆነ ዶኩሜንት ቅጂዎች (ፎቶኮፒዎች) ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪው መስጠት አለባቸው።

## D. ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ

1. ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ መሳተፊት የሚፈቀድላቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማለት የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ ተማሪው እና ወላጆቹ ወይም ሞግዚት/አሳዳጊው እና የዓይን ምስክሮች ብቻ ናቸው። ተማሪው በጠበቃ ከተወከለ፣ የትምህርት ክልሉ ጠበቃም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች በምክር ለማገዝ ይቀርባል። ሌላ የቤተሰብ አባላት ወይም ወዳጆች መቅረብ አይፈቀድላቸውም፤ ሆኖም ግን ወላጆች ምስክርነት የማይሰጥ አንድ ደጋፊ (አጋዥ) ሰው ይዘው መቅረብ ይችላሉ። ማን መቅረብ አለበት የለበትም የመጨረሻ ውሳኔው የሚሰጠው የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ነው።
2. የፊርማ ወረቀት ይዘጋጃል፤ ሁሉም በጊዜው የተገኙ ሰዎች መፈረም አለባቸው።
3. ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ የሚቀርቡ ሰዎች ትህትና መከባበር የትሞላበት ባህሪያት ለሁሉም ሊያሳዩ ይገባል። ጉዳይ ሰሚው በለስልጣን ጉዳዩን በሚሰማበት ጊዜ መጮህ፣ መሳደብ፣ መራገም፣ መወትወት ወይም ማስፈራራርት ወይም መረበሽ ጉዳይ መስማቱን እንዲያቋርጥ ያደርገዋል። የጉዳዩ መስማት ስብሰባ እዲቋረጥ ያገፋፋው ሁኔታ ላይ በመመርኮስ ጉዳይ ሰሚው ባለስልጣን ሁለተኛ ቀጠሮ ለማስያዝ ወይም እስከዚያ ግዜ ያለውን መረጃ በመመርኮስ ይወስናል።
4. የትምህርት ቤት ባለስልጣኑ፣ ተማሪው እና ወላጎቹ/ሞግዚቶቹ ጉዳዩን በእርቅ ሊፈቱ ከተስማሙ የተፈጸመውን ጥፋት በዝርዝር የሚያስቀምጥ የእርቅ የእርቅ ስምምነት ዶኩሜንት ተዘጋጅቶ በሁሉም በኩል ይፈረምበታል። ተማሪው እና ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ የተፈጸመውን የስነስርዓት ጉድለት የሚገልጹ ሁሉም ጭብጦች እና ህጋዊ ጉዳዮች የሚስማሙባቸው እና ሙሉ በሙሉ ጉዳዩ ተፈትቷል ከዚህ ቡኋላ ይግባኝ የሚያስብል ጉዳይ የለንም የለም ብለው ሲያኑ ብቻ መፈረም ይገባቸዋል። ከሁለቱም ወገኖች አንዱ የተሞከረው የእርቅ እርምጃ በሆነ ምክንያት ተገቢ አይደለም ብለው ካመኑ ጉዳዩን መስማት ይቀጥላል።
5. መስክሮች ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ መስክርነታቸውን ለመስጠት ብቻ ካልሆነ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ምሉ በምሉ መሳተፍ አይፈቀድላቸውም። ምስክርነታቸውን ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ አዳራሹን እንዲለቁ ይጠየቃሉ።
6. የተማሪው በደለኛነት እና ንጹህነት በጉዳይ ሰሚው ባለስልታን የሚወሰነው ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የቀረበ የጽሑፍ እና የቃል ምስክርነት እና ጭብጥ ላይ ብቻ ተመርኩሶ ነው። ጉዳዩ ከሚሰማበት ግዜ ውጪ የሆነ ዓይነት መረጃ ለይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን ማቅረብ አይቻልም።
7. ይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ሕጋዊ ቅደም ተከትሎች ወይም መመዘኛዎች ላይ ተመርኩሶ ውሳኔ ይሰጣል፤
    a. የቀረቡት ማስረጃዎች ሓቅነት፤ በትክክል ጥፋቱ ተፈጽሟል ወይ?
    b. ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት ክልሉ ስነስርዓት: ትምህት ቤቱ በመረጠው መንገድ ተማሪውን የመቅጣት መብት አለው ወይ? ትምህርት ቤቱ ደረጃውን የጠበቀ የስነስርዓት እርምጃ ለልዩ የስነስርዓት መተላለፍ ወይም በትምህርት ክልሉ ውስጥ የተፈጸሙ ጥፋቶች እና የት/ቤት ሕጎች ላይ ተመኩሶ ነው?
    c. ጉዳዩን ማስወገድ፤ በትምህርት ቤት መስተዳድሩ የሚታወቁ ትምህርት ቤቱ ግምት ውስጥ ሊያስገባቸው ሊችል የነበሩ ሌሎች ሕጎች ወይም የስነስርዓት እርምጃዎች ትምህርት እንዲወስድ ያስገደዱት ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
8. ይግባኙን የሚሰማው ሰው የግድ ገለልተኛ መሆን አለበት። ክሱ የተመሰረተበት ጉዳይ ላይ ምስክርነት መስጠት ወይም ምስክር ሆኖ መቅረብ አይችልም።
9. ጉዳይ ሰሚው ባለስልጣን የይግባኝ መስማቱ ሂደት በቴፕ ይቀረጻል።
10. የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ተማሪው ላይ የተወሰነውን በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል ውሳኔ ሊያስታርቅ፣ ሊያጸድቀው፣ ሊሽረው ወይም ሊያሻስለው ይችላል። የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል። ይህ ውሳኔ ለወላጅ/አሳዳዩ ይግባኙ ከተሰማ ቡኋላ ባለው አንድ ሳምንት ውስጥ በተመዘገበ ደብዳቤ ባድራሻዎ ይልካል። ወላጆች የይግባኙ ውሳኔ ለውላጆ/ሞግዚቶች በራሳቸው ቋንቋ በትምህርት ክልሉ ወጪ ተተርጉም ይሰጣቸዋል።
11. የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ውሳኔውን በጽሑፍ ያቀርባል። ይህ የጽሑፍ ውሳኔ ይግባኙ ከተሰማ ቡኋላ በአምስት የትምህርት ወይም የስራ ቀናት ውስጥ ለተማሪ ወይም ወላጅ/ሞግዚት/አሳዳጊ በተመዘገበ ፖስታ ይላካል።

**በአደጋ ግዜ በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር**

### በአስቸኳይ ሁኔታ ለደህንነት ሲባል ከክፍል፣ ከትምህርት ዓይነት ወይም የትምህርት ቤት ስራ መወገድ[46]

የሆነ ተማሪ በአስቸኳይ ሁኔታ ከክፍል፣ የሆነ የትምህርት ዓይነት ወይም ኣንቅስቃሴ ራሱን፣ ሌሎች ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን ወይም ሌሎች ሰዎችን ሊጎዳ ወይም ኣደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ተግባራት ከፈጸመ ወይም የትምህርት ሂደትን የሚረብሽ ከሆነ ወይም ትምህርት ቤት እንዲረበሽ ካደረገ ወይም እንዳደረገ ከተረጋገጠ ሌላ የባሰ ኣደጋ እንዳያደርስ መምህር፣ ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው ተማሪውን ባስቸኳይ ከሚማርበት ክፍል፣ የትምህርት ዓይነት ወይም የትምህርት እንቅስቃሴ ሊያባርረው ወይም ከትምህርት ቤት እንዲባረሩ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህ ኣስቸኳይ የስነስርዓት እርምጃ የሁሉንም ተማሪዎች እና ሌሎች ሰራተኞች ደህንነት ለመጠበቅ ተብሎ የሚወሰድ የአስተዳደሩ እርምጃ ነው። ኣንዳንድ ግዜ የደጋ ግዜ ማባረሩ ከስነስርዓታዊ እርምጃ ጋር ተሳስሮ ሊወሰን ይችላል። ተማሪውን የማስወገድ እርምጃው (ሀ) ኣደጋው ወይም የሚያስፈራው ነገር እስኪወገድ ወይም (ለ) ርእሰመምህሩ፣ ምክትል ርእሰመምህሩ ወይም ወኪሉ ሌላ ተገቢ እርምጃ እስኪወስዱ ሊሆን ይችላል። የኣደጋ ግዜ መባረሩ ከሌላ ኣይነት ኣራሚ የስነስርዓት እርምጃ ጋር ተያይዞ ሊቀጥል ኣይችልም።

### በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር[47]

የትምህርት ቤት ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው ተማሪውን በደህንነት ምክንያት ትምህርት ቤት ቢቆይ ለራሱ እና ለሌሎች ኣደጋ ይሆናል ወይም የተማሪው ትምህርት ቤት መቆየት ለደህንነቱ ያስጋል ወይም ረብሻ ይፈጥራል ብለው በበቂ ምክንያት ካመኑ ተማሪውን ከትምህርት ቤት በቀጥታ ባስቸኳይ ሁኔታ ከትምህርት ቤት ሊያግዱት ይችላሉ። ይህ የእስቸኳይ ሁኔታ መታገደ ከአስር (10) የስራ ቀናት መብለጥ የለበትም። የኣደጋ ግዜ መባረር ውሳኔው ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው እስኪሻር ድረስ ወይም በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ክልሉ የይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት የተማሪውን ደህንነት እና የሌሎች ደህንነት የሚከላከል ውጥን እስኪዘጋጅ ጸንቶ ይቆያል።

ርእሰመምህር፣ ምክትል ርእሰመምህር ወይም ወኪላቸው ተማሪውን ባስቸኳይ ሁኔታ ከተባረረ ቡኋላ ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያው የትምህርት ቀን ከተማሪው ጋር ስብሰባ ኣካሂደው መወሰድ ስላለበት ተገቢ ኣራሚ እርምጃ መነጋገር ኣለባቸው። ተማሪው እንዲባረረ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የወከለው ሰው ተማሪው ተመልሶ ክፍል ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ከመመለሱ በፊት ተማሪው ላይ ስለተወሰደው ኣራሚ እርምጃ ሊነገረው ይገባል።

### በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል ለወላጅ/ሞግዚት የሚሰጥ የጽሑፍ ውሳኔ[48]

ወላጆች ወይም ኣሳዳጊዎች ስለ የኣደጋ ግዜ መባረር ውሳኔው እና ስላላቸው መብት በተቻለ ፍጥነት ማለት ከሃያ ኣራት ሰዓት (24) በማይበልጥ ግዜ ውስጥ በቃል ይነገራሉ። በተጫምሪ የኣደጋ ግዜ መባረሩ የስነስርዓት እርምጃ ውሳኔ (NDA) በኣካል ወይም በተመዘገበ ፖስታ በከሃያ ኣራት ሰዓት (24) ውስጥ መሰጠት ኣለበት።

1. ለወላጅ/ሞግዚት እና ተማሪው የሚላከው መልእክት በተቻለ መጠን በሚናገሩት እና በሚገባቸው ቋንቋችሁ ሊሆን ይገባል፤
2. የጽሑፍ ወይም የቃል ውሳኔው ስለተፈጸመው ወንጀል መግለጫ እና ስለተጣሰው የትምህርት ክልሉ ደንብ የሚገልጽ መረጃ መያዝ ኣለበት፤
3. የጽሑፍ ውሳኔው ሊወሰድ ሚታሰበው የስነስርዓት እርምጃ ምን እንደሆነ ማስፈር ኣለበት፤
4. የጽሑፍ ውሳኔው የተማሪው እና/ወይም የወላጆች/ሞግዚቶች የይግባኝ መብቶች መግለጫ እና እንዴት ይግባኝ ሊሉ እንደሚችሉ መግለጽ ኣለበት፤ እና
5. የጽሑፍ ወይም የቃል ውሳኔው ክሱን እንዴት ይግባኝ ማለት እንደሚችሉ መግለጽ ወይም ጉዳዩ እንዲሰማ ለመጠየቅ ያለውን ይግዜ ገደብ መረጃ መስጠት ኣለባት።

### በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል ይግባኝ ኣፈጻጸም

በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ውሳኔ የሚገልጸው የጽሑፍ መልእክት ላይ የሚገልጸው የተማሪው በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ለደህንነት ማግለል ብቻ ከሆነ፤ ተማሪው ወይም ወላጅ/ሞግዚት/ኣሳዳጊ ይህ የጽሑፍ ውሳኔ ከደረሳቸው እስከ ኣስር (10) የስራ ቀናት ባለው ግዜ ውስጥ ወደ ስነስርዓት ይግባኝ ጽ/ቤት 206-252-0820 ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ይህን የኣስር ቀን የይግባኝ ግዜ ተማሪው ላይ የተወሰደው እርምጃ የኣደጋ ግዜ መባረር ውሳኔ ብቻ ከሆነ ነው። ውሳኔ ከየሆኑ ዓይነት እገዳዎች (መባረር ወይም ለረጅም ግዜ መባረር)

---

[46] WAC 392-400-290
[47] WAC 392-400-295
[48] WAC 392-400-300 እና WAC 392-400-310.

የሚያካትት እና ተያይዞ የመጣ ከሆነ ግን በተለመደው የሶስት ቀን የይብባኝ ግዜ ውስጥ ይግባኝ ማለት አለባችሁ። በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ፖሊሲ መሰረት የይግባኝ ጥያቄው በጽሑፍ (ኢሜል ጨምሮ) ወይም በተሌፎን ማቅረብ ይቻላል።

### A. የይግባኝ ሂደት የግዜ ገደብ

1. ይግባኝ ባይ ወገን ከትምህርት ቤቱ ኣራሚ እርምጃው ወይም የስነስርዓት ውሳኔው በደረሳችሁ በእስር (10) የት/ቤት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ይግባኙ ማስገባት እና ጉዳያቸው እዲታይ መጠየቅ ኣለባቸው።
2. የይግባኝ ጥያቄያችሁ ከትምህርት ቤቱ የስነስርዓት እርምጃው ወይም የስነስርዓት እርምጃ ሃሳብ ውሳኔው በደረሳችሁ በኣስር (10) የት/ቤት ወይም የስራ ቀናት ውስጥ ወደ የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ይግባኝ ካላላችሁ፣ ትምህርት ቤቱ የወሰነው ለኣደጋ ግዜ ማባረር ተግባራዊ ይሆናል በተጨማሪም ወላጅ/ሞግዚት ወይም ተማሪው ይግባኝ የማለት መብት ከዚህ ግዜ ቡኋላ የላቸውም። ይግባኙ በቃል (ቴሌፎን ጨምሮ) ወይ በጽሑፍ ሊሆን ይችላል። የስነስርዓት ይግባኝ ሰሚ ጽህፈት ቤት የቴሌፎን ቁጥር 206-252-0820 ነው።
3. የይግባኝ ክሱ በተወሰነው ኣስር (10) ቀናት የግዜ ገደብ ውስጥ ከደረሰው የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት የይግባኝ ክሱ ከተቀበለበት ቀጥለው ባሉት ኣስር (10) የትምህርት ወይም የስራ ቀናት ውስጥ የይግባኝ መስማት ቀጥሮ ያስይዛል።

### C. ወላጅ/ሞግዚት እና የተማሪዎች መብት

ወላጆች/ሞግዚቶች እና ተማሪዎች ይግባኛቸው ከመሰማቱ በፊት፣ በሚሰማበት ግዜ እና ከተሰማ ቡኋላ የተለያዩ መብቶች ኣሏቸው። እነዚህ መብቶች በስቴታችን የህግ ባለሙያዎች የጸደቁ እና WAC 392-400 በሚለው ኣንቀጽ ስር የሚገኙ ናቸው። እነዚህ መብቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፣ በነዚህ ብቻ ግን የተወሰኑ ኣይደሉም፤

1. ይግባኝ ባይ ወገን ትምህርት ቤቱ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የሚያቀርባቸውን የሆኑ የጽሑፍ ወይም ሌላ ጭብጦች እንደ የምስክሮች ቃል ያመሰሉ ጉዳዩ ከመሰማቱ በፊት የመመርመር መብት ኣለው። ሚስጢር ለመጠበቅ የተማሪ ስሞች ይሰረዛል (የሚቀርበው ወረቀት ላይ ኣይሰፍርም)። ያለውን የይግባኝ መስሚያ ግዜ ጥበት ግምት ውስጥ ኣስገብቶ የጽሑፍ ማስረጃዎች ቅጂ ጉዳዩ ከመሰማቱ ባሉት ሃያ ኣራት (24) ሰዓታት በፊት ላይቀርቡ ይችላሉ።
2. ይግባኝ ባይ ወገን በመንግስት ሳይሆን በራሱ ወጪ ጠበቃ ይዞ የመቅረብ መብት ኣለው። ይግባኝ ባይ ወገን ጠበቃ ይዞ የሚቀርብ ከሆነ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ጠበቃውን ይዞ ይቀርባል። ስለዚህ የስነስርዓት ስሚ ጽ/ቤት ተማሪው ጠበቃ ይዞ የሚቀርብ ከሆነ የግድ ኣስቀድሞ ማሳወቅ ኣለበት።
3. ይግባኝ ባይ ወገን ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ምስክሮች መጠየቅ መብት ኣለው። ይህ መብት የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መስክሮችን ኣፈላልጎ ያገኛቸው ከሆኑ ወይም ምስክሮች ካላገኘ ወይም ተማሪውን (ምስክሩን) ማቅረብ ለድህንነቱ ያሰጋል ወይም በቀል ሊያጋጥመው ይችላል ብሎ ካመነ የተወሰነ ይሆናል።
4. ይግባኝ ባይ ወገን ስለተፈጠረው የስነስርዓት መጉዳል የራሱን ማብራሪያ እና መግለጫ የማቅረብ መብት ኣለው።
5. ይግባኝ ባይ ወገን ይግባኝ ስለተባለው ጉዳይ ዕውቀት ኣላቸው የሚባሉ ወይም ፍጻሜውን ያዩ ምስክሮች ሌሎች ተማሪዎችን ጨምሮ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የምስክር ቃል መስጠት እንዲፈቀድላቸው መጠየቅ ይችላል፤ እና
6. ይግባኝ ባይ ወገን ጉዳዩን የሚደግፍ የሆነ   የጽሑፍ ወይም ሌላ ጭብጥ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ማቅረብ ይችላል።

### D. ጉዳዩ ከመሰማቱ በፊት ያሉ የትምህርት ቤቱ መብቶች

የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች ወይም ሌላ የትምህርት ቤቱን ጉዳይ የሚያቀርብ ሰው ጉዳዩ መሰማት ከመጀመሩ በፊት ወላጆች/ኣሳዳጊዎች ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የሚያቀርቡትን የሆነ የጽሑፍ ወይም ሌላ ጭብጥ የመስማት ወይም ማየት መብት ኣለው። ተማሪው እና ወላጎቹ/ኣሳዳጊዎቹ ለይግባኝ ሰሚው ባለስልጣን ለማቅረብ ያዘጋጁትን የሆነ ዶኩሜንት ቅጂዎች (ፎቶኮፒዎች) ለትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪው መስጠት ኣለባብቸው።

### E. ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ

1. ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ መሳተፊት የሚፈቀድላቸው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማለት የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች፣ ተማሪው እና ወላጆቹ ወይም ሞግዚት/ኣሳዳጊው እና የዓይን ምስክሮች ብቻ ናቸው። ተማሪው በጠበቃ ከተወከለ፣ የትምህርት ክልሉ ጠበቃም የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች በምክር ለማገዝ ይቀርባል። ሌላ የቤተሰብ ኣባላት ወይም ወዳጆች መቅረብ

አይፈቀድላቸውም፤ ሆኖም ግን ወላጆች ምስክርነት የማይሰጥ አንድ ደጋፊ (ኢጋዥ) ሰው ይዘው መቅረብ ይችላሉ። ማን መቅረብ አለበት የለበትም የመጨረሻ ውሳኔው የሚሰጠው የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ነው።

2. የፊርማ ወረቀት ይዘጋጃል፤ ሁሉም በጊዜው የተገኙ ሰዎች መፈረም አለባቸው።
3. ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የሚቀርቡ ሰዎች ትህትና መከባበር የትሞላበት ባህሪያት ለሁሉም ሊያሳዩ ይገባል። ጉዳይ ሰሚው በለስልጣን ጉዳዩን በሚሰማበት ግዜ መጮህ፣ መሳደብ፣ መራገም፣ መወትወት ወይም ማስፈራራርት ወይም መረበሽ ጉዳይ መስማቱን እንዲያቋርጥ ያደርገዋል። የጉዳዩ መሰማት ስብሰባ እዲቋረጥ ያገፋፋው ሁኔታ ላይ በመመርኮስ ጉዳይ ሰሚው ባለስልጣን ሁለተኛ ቀጠሮ ለማስያዝ ወይም እስከዚያ ግዜ ያለውን መረጃ በመመርኮስ ይወስናል።
4. የትምህርት ቤት አስተዳዳሪው፣ ተማሪው እና ወላጎቹ/ሞግዚቶቹ ጉዳዩን በእርቅ ሊፈቱ ከተስማሙ የተፈጸመውን ጥፋት በዝርዝር የሚያስቀምጥ የእርቅ የእርቅ ስምምነት ዶኩሜንት[49] ተዘጋጅቶ በሁሉም በኩል ይፈረምበታል። ተማሪው እና ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ የተፈጸመውን የስነስርዓት ጉድለት የሚገልጹ ሁሉም ጭብጦች እና ህጋዊ ጉዳዮች የሚስማሙባቸው እና ሙሉ በሙሉ ጉዳዩ ተፈትቷል ከዚህ ቡኋላ ይግባኝ የሚያስብል ጉዳይ የለንም የለም ብለው ሲያኑ ብቻ መፈረም ይገባቸዋል። ከሁለቱም ወገኖች አንዱ የተሞከረው የእርቅ እርምጃ በሆነ ምክንያት ተገቢ አይደለም ብለው ካመኑ ጉዳዩን መስማት ይቀጥላል።
5. መስክሮች ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ መስክርነታቸውን ለመስጠት ብቻ ካልሆነ ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ምሉ በምሉ መሳተፍ አይፈቀድላቸውም። ምስክርነታቸውን ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ አዳራሹን እንዲለቁ ይጠየቃሉ።
6. የተማሪው በደለኛነት እና ንጹህነት በጉዳይ ሰሚው ባለስልጣን የሚወሰነው ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ የቀረበ የጽሑፍ እና የቃል ምስክርነት እና ጭብጥ ላይ ብቻ ተመርኩሶ ነው። ጉዳዩ ከሚሰማበት ግዜ ውጪ የሆነ ዓይነት መረጃ ለይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን ማቅረብ አይቻልም።
7. ይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ የሚከተሉትን ሕጋዊ ቅደም ተከትሎች ወይም መመዘኛዎች ላይ ተመርኩሶ ውሳኔ ይሰጣል፤
   a. የቀረቡት ማስረጃዎች ሓቅነት፤ በትክክል ጥፋቱ ተፈጽሟል ወይ?
   b. ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት ክልሉ ስነስርዓት: ትምህት ቤቱ በመረጠው መንገድ ተማሪውን የመቅጣት ሙብት አለው ወይ? ትምህርት ቤቱ ደረጃውን የጠበቀ የስነስርዓት እርምጃ ለልዩ የስነስርዓት መተላለፍ ወይም በትምህርት ክልሉ ውስጥ የተፈጸሙ ጥፋቶች እና የት/ቤት ሕጎች ላይ ተመኩሶ ነው?
   c. ጉዳዩን ማስወገድ፤ በትምህርት ቤት መስተዳድሩ የሚታወቁ ትምህርት ቤቱ ግምት ውስጥ ሊያስገባቸው ሊችል የነበሩ ሌሎች ሕጎች ወይም የስነስርዓት እርምጃዎች ትምህርት እንዲወስድ ያስገደዱት ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
8. ይግባኙን የሚሰማው ሰው የግድ ገለልተኛ መሆን አለበት። ክሱ የተመሰረተበት ጉዳይ ላይ ምስክርነት መስጠት ወይም ምስክር ሆኖ መቅረብ አይችልም።
9. ጉዳይ ሰሚው ባለስልጣን የይግባኝ መስማቱ ሂደት በቴፕ ይቀረጻል።
10. የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ተማሪው ላይ የተወሰነውን በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል ውሳኔ ሊያስታርቅ፣ ሊያጸድቀው፣ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል። የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣን ውሳኔውን በጽሑፍ ያሳውቃል። ይህ ውሳኔ ለወላጅ/አሳዳዩ ይግባኙ ከተሰማ ቡኋላ ባለው አንድ ሳምንት ውስጥ በተመዘገበ ደብዳቤ ባድራሻዎ ይልካል። ወላጆች የይግባኙ ውሳኔ ለውላጆ/ሞግዚቶች በራሳቸው ቋንቋ በትምህርት ክልሉ ወጪ ተተርጉም ይሰጣቸዋል።
11. የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ውሳኔውን በጽሑፍ ያቀርባል። ይህ የጽሑፍ ውሳኔ ይግባኙ ከተሰማ ቡኋላ በአምስት የትምህርት ወይም የስራ ቀናት ውስጥ ለተማሪ ወይም ወላጅ/ሞግዚት/አሳዳጊ በተመዘገበ ፖስታ ይላካል።

## F. በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል የግዜ ርዝመት

የተማሪው በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል ቶሎ ማቋረጥ አለበት ወይም ተማሪው ከተባረረበት በአስር (10) ቀናት ውስጥ ወደ ሌላ ዓይነት የስነስርዓት እርምጃ መቀየር አለብት።

## ለሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቦርድ ይግባኝ ማለት[50]

[49] የስነስርዓት መጓደል ዕርቅ በተመለከተ ኣባሪ ጽሑፍ ሐ ተመልከቱ።

[50] WAC 392-400-310

ወላጆች/ሞግዚቶች የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑን የትምህርት ቤቱን የስነስርዓት እርምጃ፤ ለአጭር ግዜ መታገድ፣ በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ደህንነት ማግለል እርምጃ ካጸደቀው ወላጆች/ሞግዚት በዚህ ውሳኔ ካልረኩ ውሳኔ እንደጋና እዲታይላቸ የመጠየቅ መብት ኣላቸው። የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የትምህርት ቦርድ ለረጅም ግዜ መታገድ እና መባረር የሚመለት ይግባኝ የመስማት እና የመወሰን መብቱን የስነስርዓት ይግባኝ ምክር ቤት ሰጥቷል። የስነስርዓት ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት (DAC)[51] በትምህርት ቦርድ ሓላፍነት የተሰጠው እና ቢያንስ ሶስት በቋሚነት የሚሰሩ ኣባላት ያሉት ነው።

ወላጆች/ሞግዚቶች የግድ ለተማሪዎች ስነስርዓት ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ውሳኔው ከደረሳቸው ቡኋላ ባሉት ሶስት (3**) የት/ቤት የስራ ቀናት** ውስጥ ውሳኔው እንደጋና እንዲታይ የሚጠይቅ የቃል ወይም የጽሑፍ መልእክት መላክ ኣለባቸው። ይህ የጽሑፍ ጥያቄ ይግባን ያሉበትን ምክንያት ዝርዝር (ለምን የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤት ጉዳዩን እንዲያይየው እንደሚፈልጉ መግለጽ) እና የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ጽ/ቤቱ ምን ቢወሰን ይመርጡ እንደነበር ማጠቃለል ኣለበት። ይህን ደብዳቤ ለተማሪዎች ስነስርዓት ይግባኝ ጽ/ቤት፡ Discipline Appeals Office፣ Mail Stop 31-177፣ P.O. Box 34165፣ Seattle፣ WA 98124-1165።

የስነስርዓት ይግባኝ ካውንስሉ (DAC) ጉዳዩ በሚሰማበት ግዜ ጉዳዩን ኣንድ ብሎ ከመጀመሪያ ኣንደማያይ መለይ በእጁ ባለው ጭብጦች ላይ ተመርኩሶ (የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ ውሳኔ)፣ ኣዲስ ጉዳይ መስማት (de novo) እደማያካሂድ እና ምስክርነት መስማት በፍቃድ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

ይግባኝ ባይ ወገን የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑን ውሳኔ መእክቱ ከደረሰው ቀጥሎ ባሉት ሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ካላሉት የተወሰነው ለረጅም ግዜ መመታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር ውሳነ ይጸድቃል።

ይግባኝ ባይ የግድ ጉዳዩ በሶስት (3) የስራ ቀናት ውስጥ እንዲታይለት መጠየቅ ይችላል። ሆኖም ግን፤ የተማሪው ለረጅም ግዜ መታገድ ወይም መባረር የሚከተሉት ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ከሆነ ውሳኔው ጸንቶ ይቆያል፤

1. ይግባኙ እየተሰማ የረጅም ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረሩ ለኣስር (10) ተከታትይ የትምህርት ቀናት ወይም ይግባኙ እስኪወሰን ድረስ ከሁለቱ ያጠረው ኣንዱ ተግባር ላይ ይውላል፤
2. ተማሪው ለራሱ ላይ ወይም ለሌሎች ላይ ኣደጋ የሚያደርስ ከሆነ ወይም ከፍተኛ ረብሻ የትምህርት ሂደት ላይ ያደርሳል ተብሎ ከተፈራ፤ በኣስቸኳይ ሁኔታ መባረር ወይም ለደህንነት ሲባል ማግለል ውሳኔ ይግባኙ በሚሰማበት ግዜም ቢሆን ተግባር ላይ ይውላል፤

የይግባኝ ውሳኔው ከመሰተቱ በፊት የነበሩት ተማሪው ከትምህት ቤት ለኣጭር ግዜ የታገደባቸው ወይም ጠቅላላ ተባረረባቸው ቀናት ውሳኔው ሲሰጥ ከሚሰጠው የኣጭር ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረረ ቀናት ጋር ይታሰባሉ። የሆነ ተማሪ ለኣጭር ግዜ ማባረር ከትምህርት ቤት ከተባረረ ወይም ወይም ጠቅላላ ከተባረረ የይግባኝ ጥያቄው ከመመለሱ በፊት ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ መብት ከተሰጠው ወደ ትምህርት ቤት ከተመለሰ ቡኋላ በመባረሩ ምክንያት ያለፈውን ፈተና ወይም ያለመለሰው የቤት ስራ የሰሜስተር ወይም የትሪሚስተር ውጤቱን የሚጎዳው ከሆነ ወይም ፈተናውን ካልወሰደ ወይም የቤት ስራ ካልመለሰ የሰሜስተሩ ወይም የትሪሚስተሩን ውጤት የሚጎዳ ከሆነ እንዲደግመው ይፈቀድለታል።

## የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት ኣሰራሮች [52]

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የትምህርት ቦርድ በደረጃው ባለው ሃላፊነት መሰረት ሁሉኑንም የይግባኝ ጥያቄዎች የስነስርዓት ይግባን ሰሚ ምክር ቤት (DAC) [53] እንዲታይ ይመራዋል። ተማሪው ወይም ወላጆች/ኣሳዳጊዎች ተማሪው የይግባኝ ጥያቄው በቃል ወይም በጽሑፍ በሶስት የትምህርት ቤት ቀናት (3) ውስጥ ወይም የትምህት ቀናት ወደ የትምህርት ክልሉ የተማሪዎች ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት ካቀረቡ ቡኋላ የስነስርዓት ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤቱ ጉዳዩን በኣስር የስራ ቀናት (10) ውስጥ ስብሰባ ጠርተው ይግባኙን ያዩታል።

የዚህ ስብሰባ ዋና ዓላማ ከተማሪው እና ከወላጆቹ/ሞግዚቶቹ ጋር ለመገናኘት ስለ ውሳኔው ለመነጋር በተጨመሪም የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑን ውሳኔ ሊያስቀይሩ የሚችሉ ሌሎች ተጨማሪ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች እና መረጃዎች ካሉ ለመነጋገር ነው። የልዩ ትምህርት ተማሪዎች እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስለ ስንክልናቸው ወይም ቋንቋቸውን/ባህላቸውን የሚያውቅ ሰው የስነስርዓት ይግባኝ ካውንስሉ (DAC) ምክር ኣንዲሰጥ መገኘት ኣለበት።

---

[51] ፖሊሲ ቦርድ ትምህርቲ 3201 ተመልከት።

[52] WAC 392-400-315 እና WAC 392-400-320 ተመልከት።

[53] ፖሊሲ ቦርድ ትምህርቲ 3201 ተመልከት።

1. ከስብሰባው በፊት የምክር ቤቱ ኣባላት የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ (DAC)ን ውሳኔ ደግመው ያያሉ።
2. ከምክር ቤቱ ጋር በሚደረገው ስብሰባ ላይ ተማሪ ወይም ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ (ወይም ሕጋዊ ኣማካሪዎቹ) የመሰማት እና ከጉዳዩ ጋር ይያያዛል የሚሉት ተጨማሪ መረጃ የማቅረብ መብት ኣላቸው። በተመሳሳይ፤ የትምህርት ቤቱ ወኪል ተማሪው ላይ የተወሰደውን የስነስርዓት እርምጃ ያግዛል የሚለውን ተጨማሪ መረጃ የማቅረብ መብት ኣለው። ስለ ስንክልናቸው ወይም ቋንቋቸውን/ባህላቸውን የሚያውቅ ሰው በተጨማሪ መረጃ ስለ ተማሪው የስነስርዓት ጉዳይ ለስነስርዓት ይግባኝ ካውንስሉ (DAC) ይሰጣል።
3. የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት ተማሪው ላይ የተወሰነውን ለኣጭር ግዜ ማባረር ወይም ጠቅላላ መባረር ውሳኔ የምጽደቅ፣ የመሻር ወይም የማሻሻል መብት ኣለው። ምክር ቤቱ ለወላጅ ወይም ሞግዚት/ኣሳዳጊ እና ተማሪው ውሳኔውን በጽሑፍ ጉዳዩ ከተሰማ ቡኋ ባሉት ኣስር የስራ ቀናት ያሳውቃል። ይግባኙ የሚወሰነው ጉዳዩን በሰሙ እና ጭብጦቹን ባነበቡ እና በጉዳዩ በምስክርነት ያልቀረቡ የምክር ቤት ኣባላት ነው። ከምክር ቤት ኣባላት ሶስት ኣራተኛው በተገኙበት በድምጽ በመስጠት ነው።
4. የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት ውሳኔ ይብባኝ የሚባለው የላይኛው ፍርድ ቤት ነው። የላይኛው ፍርድ ቤት ሌላ ካላዘዘ በስተቀ ተማሪው ላይ የተወሰነው ለኣጭር ግዜ ማባረር ወይም ጠቅላላ መባረር ውሳኔ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ይግባኝ በሚባልበት ግዜ የተግበር ኣይተግበር የሚወሰነው የስነስርዓት ይግባኝ ምክር ቤቱ ነው። የስነስርዓት ውሳኔ ይግባኝ ሰሚ ምክር ቤት ለኣጭር ግዜ ማባረር ወይም ጠቅላላ መባረሩን ፍርድ ቤት እስኪወስነው እንዲያቆየው ጥቃቄ ቀርቦለት ባይቀባለው ምክንያት እንዲሰጥ ኣይገደድም።

## የልዩ ትምህርት ተማሪዎችን የሚመለከት የስነስርዓት እርምጃ[54]

የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ጥፋት በሚያጠፉበት ግዜ የሚወድባቸው የስነስርዓት እርምጃ ባጠቃላይ ለሌሎች ስንክልና የሌላቸው ተማሪዎችን በተመለከት የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የተማሪዎች መብት እና ግዴታዎች ስር የሰፈሩት መመሪያዎች ጋር እንድ ዓይነት ሆኖ ስንክልና ላላቸው ተማሪዎች በፌደራል ቢሮ የዋጣው የማሻሻያ ድንጋጌ (Individuals with Disabilities in Education Act (IDEA) መሰረት ይፈጸማል። ይዘቱ ከዚ ቀጥሎቀርቧል።[55]

### ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ እና ያደጋ ግዜ ማግለል

ትምህርት ቤት ውስጥ መቅጣት፣ ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መታገድ እና ያደጋ ግዜ ማግለል የመሰሉት የስነስርዓት ኣርምጃዎች ኣጠቃላይ ኣፈጻጸም ደንቦች የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ላይም በተማሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆና። የተመደበው ወይም የተወሰደ የስነስርዓት እርምጃ ተማሪው ላይ የቦታ መቀየር የማያስከትል ከሆነ (ማለት፣ ኣስር (10) ወይም ከኣስር በላይ ተከታታይ የትምህርት ቀናት መታገድ ወይም ከትምህርት መከልከል የሚያስከትል ከሆነ ውሳኔው የጠባይ መሻሻይ እቅድ (Behavior Improvement Plan (BIP) ያካተተ ሊሆን ይገባል። መወሰድ ስላለባቸው ነገሮች ቅድም ተከተል ያካተተ የጠባይ ማሻሻያ እቅድ (BIP) ካለ ዕቅዱ የሚያዘው ነገር ተማልቶ ሆኖም ግን ለውጥ ካላመጣ ብቻ የመታገድ ወይም የኣደጋ ግዜ መወገድ ውሳኔ መወሰድ ኣለበት።

### መታገድ/መባረር

የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ላይ የሚከተሉትን ያካተተ ማለት ቦታ መቀየር (ይህ ማለት፣ ኣስር (10) ወይም ከኣስር ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ መታገድ ወይም የሆነ ዓይነት ከትምህርት ቤት ማግለል) ለኣጭር ግዜ ማታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር ቅጣት ለመወሰን በሚታሰብበት ግዜ የሚከተሉት የኣፈጻጸም መመሪያዎች የግድ መመልከት ያስፈልጋል።

- ለኣጭር ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር ለልዩ ትምህርት ተማሪዎች መቀጮው የትምህርት ቦታ መቀየር የሚያጠቃልል ከሆነ (ማለት ከ10 ወይም ከኣስር በላይ የትምህርት ቀናት የያግድ ወይ ተማሪውን ከትምህርት ቤት ያሚያስወግድ ከሆነ) መወሰን። የቦታ መቀየር የማያስከትል ከሆነ መቀጮው መጽደቅ ይችላል። የቦታ መቀየር የሚያስከትል ከሆነ ግን ትምህርት ቤቱ ይህን ጉዳይ የሚያይ ቡድን (ማኒፌስት ዲተርሚኔሽን ቲም (MDT)) ስብሰባ ብዙ ግዜ ተብሎ የሚጠራው ስብሰባ መጥራት ኣለበት።

---

[54] ይህ ክፍል በተጨማሪ ለሴክሽን 504 ተማሪዎችም ያገለግላል። የSIT ቡድኑ የተማሪው የስነስርዓት መጓደል ካለው የ ሴክሽን 504 ስንክልና ጋር የተሳሰረ ነው ኣይደለም የሚለውን ሓላፊነት ለመወሰን የMDT ቡድኑን ይተካዋል።

[55] ስክልና ላላቸው ግለሰቦች የሚመለከት ኣንቀጽ (Individuals with Disabilities Education Act ….” 20 U.S.C. § 7151(c)) ጋር የሚስማማ ቅጣት ይወሰንበታል።

- ለወላጅ/ሞግዚትን ስለ (MDT) ስብሰባው መጠቀም እና ሕጋዊ መብቶቻቸውን ማሳወቅ ማለት ውሳኔውን ሕጋዊ በሆነ መንገድ መቃወም መብቶቻቸውን ማሳወቅ።
- የMDT ስብሰባው ውሳኔ ከተወሰደ በኋላ ባሉት አስር (10) ቀናት ውስጥ ወይም ቡኋላ መካሄድ አለበት። ስብሰባው ላይ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ የተማሪው የመደበኛ እና የልዩ ትምህርት መማህራን፣ ስለ ተማሪው ስንክልና እውቀት ያላቸው የትምህርት ቤቱ ወይም የትምህርት ክልሉ ወኪል እና አንደየ አስፈላጊነቱ ተማሪው ሊሳተፉ ይገባል። ስብሰባው ሙሉ በሙሉ መሰነድ ይገባዋል። የስብሰባ ዋና ዓላማ የታየው የስነስርዓት መጓደል ስንክልናው ያስከተለው ነው ወይስ የተማሪው IEP ባግባብ ባለመተርጎሙ ነው ወይስ ሌላ ምክንያት ለመወሰን እና አስፈላጊ ከሆነ ሌላ አማራጭ የጠባይ ማሻሻያ እቅድ (behavior intervention plan (BIP)) ለማውጣት ወይም ምደባ ለማካሄድ ነው።
- ስብሰባው ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች የተወሰደው ለአጭር ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር እርምጃ ገምግመው እርምጃው በትክክል ስክልና ያስከተለው ወይም IEP አተገባበር ስህተት ሆኖ ካላገኙት ውሳኔውን ሊያጸድቁት ይችላሉ።
- ስብሰባው ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች የተወሰደው ለአጭር ግዜ መታገድ ወይም ጠቅላላ መባረር እርምጃ ገምግመው እርምጃው በትክክል ስክልና ያስከተለው ወይም የተማሪው MDT አተገባበር ስህተት ነው ብለው ካመኑ እርምጃውን ሊሰርዙት ይገባል። ከዚህ ቡኋላ ስብሰባው ለተማሪው ተጨማሪ የIEP ላይ ምን ለውጥ መጨመር አለበት ወይም ተማሪው ምን ተጨማሪ እርዳት ማግኘት አለብት መለየት እና ተስማሚ የትምህርት ምድብ ማግኘት ላይ ሊያተኩር ይገባል።

## አማራጭ ግዚያዊ ትምህርት ምደባ (IAES)

የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች መመዘኛ ያሚሉትን ተማሪዎች በIEP ቡድኑ ውሳኔ መሰረት ተማሪው አማራጭ ግዚያዊ ትምህርት እስከ 45 የትምህርት ቀናት እንዲቆይ ያጋጠመ የስነስርዓት መተላለፍ ከጤናው ጋር ግንኙነት ይኑረው አይኑረ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ ሊመድቡ ይችላሉ

1. ተማሪው ተመንጃ፣ ቢላዋ ወይም ሌላ አደጋኛ መሳሪያ ወደ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት በዓላት ላይ ይዞ ከመጣ ወይም ይዞ ከተገኘ፣
2. ተማሪው እያወቀ ህጋዊ ያልሆኑ ዕጾችን ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት በዓላት ላይ ይዞ ወይንም ተጠቅሞ ከተገኘ፣ ወይም
3. ሌላ ሰው ላይ አደገኛ የአካል ጉዳት ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት በዓላት ላይ ካደረሰ።

## ለተማሪዎች የትምህርት አገልግሎት የመስጠት ግዴታዎች

ወላጆች/ሞግዚቶች ውሳኔው ተቃውመው የይግባኝ ጥያቄውን ከቀረቡበት እለት ጀሚሮ የይግባኝ ጥያቄው መልስ እስኪያገኛ ድረስ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መስተዳድር ለተማሪው የሚሰጠውን የሆነ አገልግሎት ሁሉም ሳይቋረጥ እንዲሰጠው ይገባል። ይህ አገልግሎት የመቀጠል ግዴታ በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ላይሆን ይችላል። በተጨማሪም የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ  በስነስርዓት ጉድለት ምክንያት ለረጅም ግዜ የታገዱ ወይም ጠቅላላ የተባረሩ ተማሪዎች የመባረራቸው ምክንያት ከስንክልና ጋር የማይያያዝ ከሆነ ወይም ለአጭር ግዜ ከትምህርት ቤት ወይም ብድምር ከ10 ቀናት ከትምህርት ቤት የተባረሩ ተማሪዎች የሚገባቸውን አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይገደዳል። የስነስርዓት እርምጃውን የወሰነው የትምህርት ቤት ርእሰመምህር በተጨማሪ መማህራኑ ለተማሪው የቤት ስራውን እንዲሰጡት መቆጣጠር እና ትእዛዝ ማስተላለፍ አለበት።

የስነስርዓት እርምጃው ወይም ውሳኔ ተማሪው ላይ ለአጭር ግዜ መታገድ እና ጠቅላላ መባረር ቢሆንም የልዩ ትምህርት ተማሪው የሚገባውን የልዩ ትምህርት እና ከሱ ጋር የሚያያዙ ነጻ እና ተገቢ የሆኑ አማራጭ ትምህርት ፕሮግራሞች ማግኘት ይገባዋል።

## አወንታዊ የጠባይ ማረሚያ ውጥኖች

የጠባይ ማረሚያ ውጥኖች (ብሄብየር ማነጅመንት ፐላን(BIP)) ወይ ብሔብየር ኢንተርቬንሽን ፐላን አስፈላጊ የIEP አካል እና በመጥፎ ባህሪያቱ ምክንያት የርሱን የትምህርት ሂደት እና የሌሎች ጤነኛ የትምህርት አከባቢን የሚያስተጓጉል ተማሪ ንው። ይህ ፕሮግራም አስፈላጊ የተማሪውን ጠባይ ለማርረም የሚያግዙ ሜላዎች፣ ማበረታቻዎች፣ አወንታዊ እገዛዎች እና እርዳታዎችን ያጠቃለለ ነው። ለልዩ ትምህርት ተማሪዎች የጠባይ ማረሚያ ውጥኖች አንደ አስፈላጊ የስነስርዓት ማረሚያ ልዩ ኢጋጣሚ የትምህርታቸው አካል ሆኖ ሊሟላ ይገባዋል። ፕሮግራሙ ላይ የሰፈሩ አንዳንድ ባህሪያት ሲያጋጥሙ ሁኔታውን ግምት ውስጥ አስገብቶ በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው።

**በ1989 የፌደራል ከኣደንዛዥ ዕጾች ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች እና ማሕበረሰቦች ድንጋጌ ለተማሪዎች እና ለወላጆች የሚጠይቀው ማሳሰቢያ**

*የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ተማሪዎች ኣልክሆል እና ኣደንዛዥ ዕጽ ትምህርት ቤት ግዚ ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ መያዝ፣ መጠቀም ወይም ማከፋፈል ይከልክላል። ይህን ሕግ ማክበር የግድ ነው። ይህን ሕግ የሚጥሱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ለረጅም ግዜ ሊታገዱ ወይም ጠቅላላ ሊባረሩ ይችላሉ። ሕገ ወጥ የሆኑ ዕጾችን ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም እና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ኣልኮሆል ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም ስህተት ነው ብሎም ጤንነትን እና ትምህርትን ይጎዳል። የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የዕጽ እና ኣልኮሆል ምክር ኣገልግሎት ሊያዘጋጅ እና ሊያቀርብ ወይም የዕጽ እና ኣልክሆል ምክር ኣገልግሎት፣ ተሃድሶ ወይም ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ፕሮግራም በማዘጋጀት በኩል ሊረዳ ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ የትምህርት ቤታችሁን ርእሰ መምህር ወይም ካውንስለር ኣነጋግሩ።*

# ኣባሪ ጽሑፍ ሀ

## የቃላት ኣተረጓገሞች

የሚከተሉት በዚህ ዶክሜት የተለያየ ክፍል የመገኙ ቁልፍ ቃላት ትርጉሞች/ኣተረጓጎሞች ናቸው።

**ይግባኝ ባይ ወገን:** የሆነ የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ተማሪ ላይ የስነስርዓት ወይም ኣራሚ እርምጃ ሲወሰድ የክልሉን የይግባኝ ኣፈጻጸም ኣንቀጽ WAC 392-400 ተጠቅመው ውሳኔውን ይግባኝ የሚል ወላጅ፣ ሞግዚት/ኣሳዳጊ ወይም ተማሪ።

**ከተመደቡበት ቦታ መቀየር:** የልዩ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እሱ/እሷ አሁን ከተመደቡበት ትምህርት ክፍል ከአስር (10) በላይ ተከታታይ የትምህርት ቀናት ማዛወር ወይም በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በተከታታይ በድምር አስር (10) ትምህርት ቀናት በላይ ማዛወር ወይም ማግለል። የማዛወር ሁኔታ የሚወሰነው ጉዳይ በጉዳይ አንድ ባንድ እያዩ ነው።

**ስነስርዓት:** ለዚህ ዶኩሜንት ዓላማ ሲባል ሁሉም ዓይነት አራሚ የስነስዓት እርምጃዎች እንደ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ቅጣት፣ ለአጭር ግዜ ማባረር ወይም ጠቅላል መባረር ያጠቃልላል።

**በትምህርት ክልሉ ውስጥ የተፈጸሙ ጥፋቶች:** የትምህርት ሂደትን የሚረብሽ ወይም የሚያቋርጥ ባህሪያት። በትምህርት ክልሉ ውስጥ የተፈጸሙ ጥፋቶች የትምህርት ሂደትን እንዲያግዙ ማለት የትምህርት ቤት የትምህርት ሂደትን እንዲያግዙ፣ መማህራንን እንዲያስተምሩ እና ተማሪዎች እንዲማሩ የተነደፉትን መመሪያዎች መተላለፍ ማለት ነው።

**በአስቸኳይ ሁኔታ መባረር:** ተማሪው ከትምህርት ቤት ባስቸኳይ በስነስርዓት ማጉደል ምክንያት ማባራር ማለት የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ተማሪው ትምህርት ቤት መገኘቱ ለራሱ/ለራሷ ወይም ለሌሎች ቀጥተኛ ወይም ተደጋጋሚ አደጋ፣ ስጋት ወይም ከፍተኛ ረብሻ ሊያስከትል ይችላል የሚል ጥርጣሬ ሲኖራቸው ተማሪውን ባስቸኳይ ማስወገድ ማለት ነው። የአስቸኳይ ሁኔታ መባረር ውሳኔ በይግባኝ ግዜም ጸንቶ ይቆያል።

**ጠቅላላ መባረር:** መባረር ማለት የተለመደው ተማሪ በፈጸመው ጥፋት ምክንያት ተማሪው በሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የሚገኝ ሚማርበት ት/ቤት በጠቅላላ እንዳይመለስ የማግለል ማለት ነው። ተማሪው የተባረርው ከሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ከሆነ፤ ተማሪ በሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ውስጥ የሚገኝ የሆነ ትምህርት ቤት መመዝገብ ወይም የሆነ ፕሮግራም እስከ እንድ ዓመት ድረስ መሳተፍ አይችልም።

**ት/ቤት ውስጥ ማታገድ:** ይህ ትምህርት ቤት ሊወስዳቸው ከሚችል ብዙ አራሚ የስነስርዓት እርምጃ አማራጮች አንዱ ነው።  የረበሸን ተማሪን ከክፍል ማባረር ወይም የተለያዩ የትምህርት ቤት ስራዎች ማገድ ያጠቃልላል። ተማሪዎች የቤት ስራ እና ጠባያቸውን ለወደፊቱ ለማሻሻል በተደጋጋሚ ማህበራዊ ችሎታ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ይህ ከአንድ ፔሬድ እስከ ብዙ ቀናት ሊሆን ይችላል።

**ግዚያዊ ቅያሪ የትምህርት ሁኔታ (ኢንትሪም ኦልተርናቲቭ ኢዱኬሽናል ሴቲንግ (IAES)):** የተፈጠረው የሕግ መጣስ መሳሪያዎችን (በሄራዊ እና ፌደራላዊ ድንጋጌ ባሰፈረው መሰረት)፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የተከለሉ ነገሮች  ወይም አደገኛ የአካል ማቁሰል የሚያደርስ ድብድብ  የትምህርት ቤት ሰራተኞች የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ወደ ሌላ ተገቢ ግዝያዊ ቅያሪ ትምህርት ቤት ለተወሰነ ግዜ እንዲቀይሩ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህ ቅጣት ለሌሎች ተማሪዎች የሚወሰንባቸውን ያህል ከ45 የትምህርት ቀናት የማይበልጥ ሊሆን ይችላል። ግዝያዊ ትምህርት ቤት መቀየር የተመረጠበት ምክንያት ተማሪውን ቦታ ቢቀይርም ከትምህርቱ እንዳይደናቀፍ፣ ተገቢ አገልግሎት ማግኘት እንዲቀጥል እና የተማሪው ያለአንድ ለአንድ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ላይ የሰፈሩትን ግቦች እንዲሳኩ ነው።

**ለረጅም ግዜ መባረር:** ከአስር (10) ቀናት በላይ እና ባጠቃላይ ግን ከዘጠና (90) ቀናት በታች መባረር ያጠቃልላል። የሆነ ተማሪ ለረጅም ግዜ ተባሮ ባለበት ወቅት የትምህርት አገልግሎት የማግኘት መብት አለው።   ትምህርት ቤት ይመለሳል። የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ለረጅም ግዜ መባረር አይገባቸውም።

**ለየት ያሉ የስነስርዓት ሁኔታዋች (ማኒፌስቴሽን ዲተርሚኔሽን):**  በልዩ ትምህርት ወይም የሴክሽን 504 ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች እና የስነስርዓት እርምጃ የሚያስከትል ጥፋት የሚያጠፉ የተማሪዎች ባህሪያት መሃከል ያለ ዝምድና። ጉዳዩ ሲታይ የተፈጠረው ሕግ መጣስተማሪው ካለው አካለ ስንክልና ወይም የትምህርት ቦታ አመዳደብ ስህተት ጋር የተያያዘ ካልሆነ በስተቀር፤ ተማሪ ሌሎች ተማሪዎች በሚቀጡበት አግባብ እና ለነሱ የሚወሰነውን ያህል የስነስርዓት እርምጃ ይወሰድበታል። በልዩ ትምህርት ተማሪዎች የሚፈጸም የስነስርዓት መጣስ ካጋጠመ ጉዳዩ የሚጠናው በትምህርት ቤቱ የአንድ ለአንድ ቡድን (IEP team) ወይም ለየት ያሉ የስነስርዓት ሁኔታዎችን በሚያጠና ቡድን (Manifestation Determination Team) ነው። የሴክሽን 504 ተማሪዎችን የሚመለከት ለየት ያለ ባህሪያት ካለ ሁኔታው የሚጠናው በትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ሁኔት በሚያጠና ቡድን (Student (or School) Intervention Team (SIT)) ነው። ወላጆች የልጆቻቸው ጉዳይ በስብሰባ በሚካሄድበት ግዜ መጠራት እና መሳተፍ ይገባቸዋል።

**ሽምግልና:** በትምህርት ቤቱ እና በተማሪው ወይም ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ መኃከል የተደረሰ የተወሰነ የስነስርዓት እርምጃ ስምምነት ሊቀየር ይችላል። አንዴትስ ሊቀየር ይችላል። ተማሪው ወይም ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ በመፈረም የተጣሰውን ሕግ የሚመለከት የቀረበ ጭብጥ እና የሕግ መርትያ ላይ ተመስርቶ የተወሰነ የሽምግልና ስምምነት የመጨረሻ እና ጉዳዩ እንደተፈታ ይስማማሉ። ከዚህ ቡኋላ ወላጆች/መጉዚቶች ጉዳዩን በተመለከተ ይግባይ ላለማለት ይስማማሉ። ዕጽን እና ሌላ ነገሮች መጠቀም የተመለከተ ጉዳዮችን የሚመለከት የሽምግልና ቅጥ አፔንዲክስ  A። ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከት የሽምግልና ቅጥ አፔንዲክስ  B ታገኙታላችሁ።

**የስነስርዓት እርምጃ ማሳወቅ (ኖቲስ ኦፍ ዲሲፕሊነሪ አክሽን/NDA):** ይህ በፓወር ስኩል በኩል የሚዘጋጅ ስለ ተወሰደ የስነስርዓት እርምጃ ለወላጆች/አሳዳጊዎች የሚላክ ደብዳቤ ነው።

**ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የተማሪዎች የስነስርዓት መቀጮ:** ይህ የተምሪውን ጠባይ ከግዜ ጋር ከግዜ ጋር የሚያሻሽል ጠበቅ ያለ የስነስርዓት እምጃ መሆን ይገባውል። ከግዜ ጋር እየጠነከረ የሚሄድ መቀጫ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ምላሽ፣ ትምህት ቤት ውስጥ የሚውሰድ እርምጃ፣ ትምህርት ቤት ውስጥ መታገድ፣ የእጭር ግዜ እና የረጅም ግዜ መባረር ሊሆን ይችላል። ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የስነስርዓት መቀጮ ተማሪዎች ላይ ለመወሰን ትምህርት ቤቶች ያለፈው የትምህርት ዓመት መጀመሪያ በፊት ወይም 180 የትምህርት ቀናት በፊት የተፈጸመ ጥፋት እንዲያስቡት ኣይገባም።

**ምክንያትታዊ ተቀባይነት ያለው ሓይል መጠቀም:** በትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪዎች፣ መማህራን፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ወይም ነጻ ፈቃደኞች ህግ እና ስርዓትን ለማስከበር ወይም ተማሪው እራሱን፣ ሌሎች ተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት ስራተኞች እና/ወይም ንብረት እንዳይጎዳ ለመከላከል እንዳስፈለጊነቱ መጠነኛ ሓይል መጠቀም። እንደዚህ ያለ ሃይል መጠቀም ለምሳሌ መግረፍ ግን ኣራሚ እርምጃ ኣይታሰብም።

**የተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ስብሰባ:** ለረጅም ግዜ ከትምህርት ቤት ጠቅላል ተባሮ የቆየ ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት በሚመለስበት ግዜ ለሁሉም ደህንነት ሲባል እና ዳግም መመለሱ ውጤታማ እንዲሆን ተማሪዎቹ ከመመለሱ በፊት የመመላሻ ስብሰባ ከተማሪው ጋር ማካሄድ የግድ ነው። ተማሪው፣ ወላጆቹ ወይም ኣሳዳጊዎቹ እና የሚመለከታቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች የዚህ ስብሰባ ኣካል ናቸው። የተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ዳግም መመምለስ ውጤታማ እንዲሆን የተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ኣግባብ ስብሰባ ቀን ኣስቀድሞ ኣስይዞ የመባረር ውሳኔ ከያዘው ደብዳቤ ጋር መላክ ኣለበት። በያንስ የማባረር ውሳኔው በተወሰደ ሶስት ቀን ውስጥ የመመለሻ ቀጠሮ መያዝ ኣለበት። በስብሰባው ወቅት በጽሑፍ የሰፈረ ከተማሪው ሁኔታ ጋር የሚስማሙ ተማሪው ተባሮ ባለበት ወቅት ስለሚሰጠው ትምህርት ዝርዝር የሚገልጽ እቅድ መቅረብ ኣለበት። እቅዱ በተጨማሪ ተማሪው የሚያስፈልጉትን ኣስፈላጊ እገዛዎች ያጠቃለለ መባረሩን ወይም መታገዱን ያስከተለውን ሁኔታ የሚያርም የመመለሻ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል።

**የመመለሻ ዕቅድ:** የትምህርት ክልሉ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የጠባይ ማረሚያ እና መደበኛ ትምህርት ከትምህርት ቤት ኣደገኛ ጥፋት ኣጥፍተው ለታገዱ እና ለረጅም ግዜ የተባረሩ ተማሪዎች በጸደቀው የልዩ ጥፋት ስነስርዓት እርምጃ የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የ2017-2018 የትምህርት ዓመት የስነስርዓት ዕቅድ በሚፈቅደው መሰረት ትምህት ይሰጣል።

**የት/ቤት የስራ ቀን:** በዓላትን ሳይጨምር የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ለስራ ክፍት የሆነበት የሆነ የዓመቱ ቀን ማለት ነው።

**ለትምህርት ቤት ድህነት የሚያሰጉ ነገሮች የሚያጠና ቡድን (STAT):** በሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ  የጤንነት እና ደህንነት ክፍል ስልጠና የወሰዱ መርማሪ ባለሙያዎች ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ኣደገኛ ወይም ነገረኛ ተማሪዎችን ለመለየት የሚሰጥ ኣገልግሎት ነው። ይህ ቡድን ከተማሪዎች ባህሪያት ጋር የሚሄዱ ሁኔታዎችን እና መመዘናዎችን ለይቶ ከወጣቶች ሁከት/ብጥብጥ/ድብድብ እና ዓመጸኛነት ጋር መተሳሰራቸውን እና ኣለመተሳሰራቸን ያጠናል።

**የትምህርት ዓመት ርዝመት ገደብ:** በእንድ የትምህርት ዓመት የተወሰኑ የስነስርዓት እገዳዎች በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ የተወሰኑ ካልሆኑ ወደ ሚቀጥለው ዓመት ወይም ዓመታት ኣይተላለፉ። ከግዜ ጋር የእየጨመረ የሚሄድ የስነስርዓት እርምጃ ተማሪዎች ላይ ለመወሰን ትምህርት ቤቶች ያለፈው የትምህርት ዓመት መጀመሪያ በፊት ወይም 180 የትምህርት ቀናት በፊት የተፈጸመ ጥፋት የትኛውም ያመዝን ትምህርት ቤት ውስጥ የሁከት/ብጥብጥ ስጋት የማያደርስ ከሆነ እንዲያስቡት ኣይገባም።

**ለኣጭር ግዜ መባረር:** ለኣጭር ግዜ ማባረር ከ10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ላልበዛ ግዜ ከትምህርት ቤት መባረር ያጠቃልላል። የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ለኣጭር ግዜ ከትምህርት ቤት መባረር የተወሰነባቸው ተማሪዎች ቅጣታቸን ጨርሰው ወደ ነበሩበት ትምህርት ቤት ይመለሳሉ። ተማሪው ለኣጭር ግዜ ተባሮ ቤት በሚቆይበት ግዜ የቤት ስራ መውሰድ እና ሰርቶ መመለስ ይችላል። ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በተባረሩበት ግዜ የትምህርት ኣገልግሎት የማግኘት መብት ኣላቸው።

**የልዩ ትምህርት ተማሪዎች:** የሆነ ተማሪ በዋሽንግተን ሕግ (WAC) ስር ከተዘረዘሩት የኣካል ጎደለነት መመዘኛዎች ኣንድ ወይም ካንድ በላይ የሚያሟላ እና ልዩ ለሱ የሚስማም ኣካዳሚያዊ እና የጠባይ ማሻሻያ ትምህርት ያሚያስፈልገው ወይም የሚከታተል ተማሪ።

**ለየት ያለ ኣገልግሎት የሚፈልጉ ተማሪዎች:** ልዩ ተማሪዎች የሚለው ምድብ የልዩ ትምህርት ተማሪዎችን እና የሴክሽን 504 ተማሪዎች እና የተወሰነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው (LEP) ተማሪዎችን ያጠቃልላል።

**መታገድ:** ለተወሰነ ግዜ በወጉ ኣሳውቆ ተማሪን ትምህርት ቤት ከመምጣት መከልከል ወይም ማገድ። ይህ ስነስርዓት ለማስጠበቅ ተብሎ ወግ ሳይጠብቁ ከክፍል ማባረር ኣያጠቃልልም። ከትምህርት ቤት የታገደ ተማሪ ታግዶ ባለበት ወቕት የትምህርት ኣገልግሎት የማግኘት መብት ኣለው።

**ኣደገኛነቱ እንዲጠና ማስተላለፍ:**_ይህ ኣርምጃ የሚወሰደው የተማሪው ምንም ኣንኳን ኣስቀድሞ ምክር ቢሰጠውም ወይም ቕጣት ቢወሰድበትም ከትምህርት ቤት ኣደገኛ ለሞት የሚዳግግ ጥፋት ወይም ኣስነዋሪ ጾታዊ ተግባራት ወይም ቁጣ የተሞላበት ዓመጸኛ ባህሪያት እገዛዎች እና የስነስርዓት ማሻሻያ ቢከታተልም እንደገና በኣስቸኳይ ሁኔታ ሲባረር ነው። በጥያቄው መሰረት ጉዳዩን በሚያጠናው የኣደገኛነት እጥኚ ቡድን ጉዳዩ ጥናት ይካሄድበታል። ተማሪው በሰላም የሚመለስበት ሁኔታ የሚያሳይ የድህንነት ውጥን ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ክልሉ ከመመለሱ በፊት መዘጋጀት ኣለበት። የተማሪው በኣስቸኳይ ሁኔታ መባረር ውሳኔ በተማሪው ወይም ወላጆቹ/ኣሳዳጊዎቹ በስቴቱ ሕግ መሰረት ይግባኝ ሊባል ይቻላል።

**ኣባሪ ጽሑፍ ሀ: የኣደንዛዥ እጽ/ኣልክሆል የሚመለከት ሽምግልና**

ስም፤____________________________________________ የተማሪው መታወቂያ ቁጥር፡ ______________

ትምህርት ቤት፤ ____________________________________

ይህ የሽምግልና ስምምነት የተደረሰው በተማሪው እና በወላጆቹ/ኣሳዳጊዎቹ መሃከል ሕጋዊ ያልሆኑ ኣደንዛዥ ዕጾች እና **ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች, በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱፐር ማርከት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች**፣ የኣልኮል መጠጦችን ማከፋፈል እና ህጋዊ ያልሆኑ ዕጾች እና ኣደንዛዥ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች በመያዝ ወይም መጠቀም፣ የኣልኮል መጠጦችን ይዞ በመገኘት እና መጠቀም ወይም ሃሺሽ ወይም ማሪዋና ይዞ ወይም ሲጠቀም በመያዝ ኣስመልክቶ የተምሰረተ ክስ ለመመርመር በተካሄደው ስብሰባ ላይ በመመርኮስ ነው። ትምህርት ቤት የሚከተለው ነጥብ ላይ ይስማማል፤

ሀ. ክሱ እና ዝርዝሩ ይህን ይመስላል፤

- ❑ ምንም ክስ የለም
- ❑ ይህን ክስ የሚመለከት መግለጫ/ኣገላለጽ/መጠሪያ እንደሚከተለው ተቀይሯል፤

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ለ. የ_________________________ መጣስ የሚያስከትለው የረጅም ግዜ መታገድ ለማጉደል፤ ተማሪው በትምህርት ክልሉ ተቀባይነት ባለው የኣደገኛ እጾች መከላከል ባለሙያ ለማማከር ቀጠሮ ማስያዙን እና የባለሙያውን ምክር ተግባር ላይ ለማዋል መስማማቱ ማረጋገጫ ስለቀረበልት ቅጣቱ ወደ ሚከተሉት ቀናት መባረር ተቀይሯል፤

- ❑ ለ_______ ቀናት የኣጭር ግዜ መታገድ ።
- ❑ ለ _______ የረጅም ቀናት መታገድ።

ሐ. ትምህርት ቤቱ በተጨማሪ የተማሪዎች በፓወር ስኩል ያሰፈረውን የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ ጉዳዩን የሚመለከት መረጃ ይህን ስምምነት እንዲያሳይ ሆኖ እንዲታረም እና ተሻሽሎ የቀረበ የስነስርዓት እርምጃ ደብዳቤ (ኖቲስ ኦፍ ዲስፐሊነሪ ኣክሽን/NDA ቅጂ ለወላጆች/ኣሳዳጊዎች በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ለመላክ።

2. ተማሪው/ወላጆች/ኣሳዳጊዎች የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተስማምተዋል:
በወልጆች ወጪ በትምህርት ክልሉ ተቀባይነት ባለው የኣደገኛ እጾች ባለሙያ የሚካሄድ ጥናት ለመከታተል።

- ❑ የበለሙያውን ምክሮች ተግባር ላይ ለማዋል።
- ❑ የትምህርት ክልሉ ከባለሙያውን ጋር መረጃ እንዲቀያየር የፍቃድ መስጫ ፎርሙን በመፈረም መፍቀድ።

3. በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች መተግበር ኣለባቸው፤

__________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________

ትምህርት ቤቱ፣ ተማሪው እና ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ ይህ የሽምግልና ስምምነት የተጣሰውን ሕግ የሚመለከት የቀረበውን ጭብጥ እና የሕግ መርትዖ ላይ ተመስርቶ የተደረሰ የመጨረሻ እና የተፈታ መሆኑን ተስማምተው ስምምነቱ ላይ ፊማቸውን ያኖራሉ። በተጨማሪ ተማሪው ወይም ወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ዳግም ይግባኝ ላለማለት ተስማምተዋል።

እኔ ______________________________ ይህን የሽምግልና ስምምነት ተግባር ላይ ካላዋልኩት፤ የመጀመሪያው ክስ እና ውሳኔ በቦታው ተተክቶ ተግባር ላይ ይውላል።

______________________________

______________________________

የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ተማሪ

______________________________

______________________________

ቀን ወላጆች/አሳዳጊዎች

**ኣባሪ ጽሑፍ ለ: የ ______________________________ ሽምግላና**

የተማሪው መታወቂያ ቁጥር፤ ______________________ ቀን: ______________________________

ይህ የሽምግልና ስምምነት ውሳኔ ላይ የደረስነው ጉዳዩን በሚመለከት ዛሬ ባካሄነው የስነስርዓት ጉዳይ መስማት ስብሰባ መሰረት ነው። ሁለቱም ወገኖች የሚከተሉት የሽምግልና ነጥቦች ላይ ተስማምተዋል።

1. ትምህርት ቤቱ ክሱ እና ክሱን የሚመለከት መግለጫ እንደሚቀጥለው እንዲሆን ተስማምተዋል፤[56]

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

   ____

2. ትምህርት ቤቱ የሚከተሉትን ለማከናወን ተስማምቷል፤

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

   _______

3. ተማሪው የሚከተሉትን ለማከናወን ተስማምቷል፤

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

   _______

4. በተጨማሪ የሚከተሉት ጉዳዮች ይተገበራሉ (የተስማማችሁበት ነጥብ ላይ ኣክብቡ)፤
   - ❑ ተማሪው በየሳምንቱ በ ______________________________ ሳምንታዊ ሪፖርት ያቀርባል።
   - ❑ ተማሪው መልካም ጠባይ ያሳያል። ተመሳሳይ የስነስርዓት መተላለፍ ክፍል ውስጥ ወይም ወጭ ኣይደግምም።
   - ❑ ተማሪው ሁሉንም ትምህት ዓይነት በሰዓቱ በመገኘት ይከታተላል። ተማሪው ክፍል ሲጀምር ትምህርቱን ለመማር ዝግጁ ይሆናል። ይህን ቅድመ ሁኔታ ባያሟላ ግን ______________________________.

እኔ ______________________________________ የዚህ ስምምነት ነጥቦችን ሳላሟላ ብቀር፤ የመጀመሪያው ክስ እና ውሳኔ በቦታው ተተክቶ ተግባር ላይ ይውላል። ተማሪው እና ወላጆቹ/ሞግዚቶቹ ይህ የሽምግልና ስምምነት የተጣሰውን ሕግ የሚመለከት የቀረበውን ጭብጥ እና የሕግ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ የተደረሰ የመጨረሻ እና የተፈታ መሆኑን ተስማምተው ስምምነቱ ላይ ፊማቸውን ኣኑረዋል። በተጨማሪ ተማሪው ወይም ወላጆቹ/ኣሳዳጊዎቹ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ዳግም ይግባኝ ላለማለት ተስማምተዋል።

______________________________________ ______________________________________

ረዳት ርእሰመምህር ተማሪ

______________________________________ ______________________________________

[56] የስነስርዓት እርምጃ ደብዳቤ (ኖቲስ ኦፍ ዲስፒሊነሪ ኣክሽን/NDA ላይ ክሱ እና ኣስተያየቶቹ የማይቀየሩ ከሆነ “ለውጥ የለም” “No changes” ኣስፍሩ። እዚህ የተደረጉ ለውጦች የኤሌንትሮኒክ የተማሪዎች መገብ (eSIS) ላይም መስፈር ኣለባቸው። ተሻሽሎ የቀረበ የስነስርዓት እርምጃ ደብዳቤ (ኖቲስ ኦፍ ዲስፒሊነሪ ኣክሽን/NDA ቅጂ ለወላጆች/ኣሳዳጊዎች በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ መላክ ኣለበት።

ጉዳይ ሰሚ ባለስልጣን ወይም ሌሎች ምስክሮች

ወላጆች/ሞግዚቶች